

ትውልድ
(እውነተኛ ታሪክ)

ይህንን መጽሐፍ ያለአዘጋጁ የጽሑፍ ፈቃድ መልሶ ማባዛትና ተርጉሞ ማሠራጨት በጥብቅ የተከለከለ ነው::

የሽፋን ስዕል
በሰለሞን ዘመዴ (ከነጌሌ ቦረና)





አዘጋጅ አብዲ አብዱላሂ

**ጭካኔ ሳይሆን ፍቅር የሰውን ልብ ይማርካል::**

# ያልታደለው ትውልድ

## እውነተኛ ታሪክ

ዋጋ 500

# መግቢያ

የሰው ልጅ ምንኛ ክቡርና ተወዳጅ ፍጥረት እንደሆነ ማመን ከማመንም በላይ ደግሞ ስለ ሰው ክብር መጽናትና የድርጊቱ ባለቤት ሆኖ መገኘት ክፋት በበዛበት ምድር ታላቅ ምሣሌነት ነው::

ዓለማችን ሁልጊዜ አዳዲስ ነገሮችን ይዛ ብቅ ትላለች:: የተለያዩ ፍልስፍናዎችና ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ከተለያየ አቅጣጫ እየመነጩ በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ የለውጥ ማዕበል ያስነሳሉ:: ሞገዱ የበረታና ኃያል የሚመስለው አዲስ ነገር በሌላ አዲስና የተለየ ክስተት ይዋጣል:: እንዲህ እንዲህ እያለ የሰው ልጅ ብዙ የታሪክ አጋጣሚዎችን አሳልፏል::

ከብዙ ዓመታት በፊት በሰው ልቦና እንደ እውነት ይታሰቡና ይደከምላቸው፣ ይሞትላቸው፣ ይገደልላቸው የነበሩ ሀሣቦች፣ ነገሮች፣ ዕምነቶች በዛሬ ብስለቱ ፊት ቂልነት ሆነው ይታሰባሉ::

ዓለም በሙሉ ከአህጉር አህጉር አቋርጦ ያመነበት ዓርማ የቀረፀለት፣ የጮኸበት ፍልስፍና... ወደፊት ለዓመታት በእግረ-ኅሊናቸው ቀድመው በልቡናቸው ምናብ የጐበኙት የፈላስፋዎች ሕልማዊ ነገር እንጂ በምንሳተፈው የተዛባ ዓለም ሊደላደል የማይችል ተረት መሆኑ እየታመነ የመጣበት ዘመን ደርሰናል::

በኑሯችን ውስጥ በርካታ አስተሳሰቦች ብቅ (ብልጭ) እያሉ ጥልቅ (ድርግም) ይላሉ በወራት ብዜት ያረጃሉ፤ ይሻራሉ:: የሰው ልጅ ግን የአሮጌውና የአዲስ አስተሳሰቦች ባለቤት እየሆነ ነበር:: ዛሬም አለ ክቡሩ... ተወዳጁ የሰው ልጅ::

የዚህች አነስተኛ ጽሑፍ አዘጋጅ ከሁሉም በፊትና በላይ «ሰብአዊነት ለሰብአዊነት» የሚል ጠንካራ ዕምነት አለው:: ፖለቲካዊ አቋሞቻችንና

አስተሳሰቦቻችን ከሰብዕናችን እየቀደሙ በሰውነታችን እግዚአብሔር ያደለንን የከበሩ ሀብታት ፍቅር፣ ትዕግሥት፣ ርህራሄ፣ ቸርነት፣ ማመዛዘን እያመከኑ ወደ አውሬነት እንዳይለውጡን እንጠነቀቅ ዘንድ በጥብቅ ያሳስባል።

ወቅት የሚወልዳቸው ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች ጧት ተነበ ማምሻውን ለዕቃ መጠቅለያነት እንደሚያገለግል ዕለታዊ ጋዜጣ ሲያልፉና ሲጣሉ በምናይበት ዓለም ሰው ባለው የሀሣብ (የመስመር) ልዩነት ምክንያት የሚደርስበትን እስራት፣ ግርፋት፣ ስቃይ፣ መከላሸት፣ በስለት መቆረጥ፣ መስቀል፣ መታነቅ፣ በጥይት መደብደብ ይቃወማል።

በዚህች አነስተኛ ጽሑፍ የተካተተው ታሪክ በነጌሌ ቦረና አካባቢ በኢሕአፓ (ኢህአወሊ) ስር ተደራጅተው ስለተሰው ወጣቶችና ስለ ደርግ መኢሶን ነፍሰ ገዳዮች እንዲሁም ሰቆቃው ስለደረሰባቸው አባላቱና ወላጆች እውነተኛ ገጠመኝ ቢሆንም:-

ዐቢይ ተልዕኮው ቀሪው ትውልድ ዕልቂቱ እንዳይደገም በትምህርት ሰጪነቱ ሊጠቀምበት እንዲችል ነው። በእግረ መንገዱም አቶ ተስፋዬ መኮንን የሚባሉ ግለሰብ «ታሪክን ለባለታሪኮ» በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዳስተላለፉት «... ኢህአፓ... በአብዛኛው የጠዘኔውን ክፍል ያቀፈ.... የነፍሰ ገዳዮች ድርጅት ነው...» በማለት ያሳተሙትን አሳፋሪና ሀሰተኛ ጽሑፍ ለማረምና የወጣቱን በእውነት ለእውነት መውደቅ የአሁኑ ተተኪ ትውልድ በትክክል እንዲያውቀ ለመመስከርም ነው።

ምናልባትም ዛሬ ባለንበት ሁኔታ በወንጀለኞቹና በተባባሪዎቻቸው ላይ የክስ መረጃ ለማቅረብና ቀሪውን ትውልድ በቂም ለማናከስ ሳይሆን የበደለ በመፀፀት ለይቅርታ (ለካሣ) ነፍሱን





እንዲያዘጋጅ። የተበደለውም የቀደመው የስቃይ አሻራ በዚህ ትውልድ ላይ እንዳያርፍ ይቅር ባይ ሆኖ እንዲቀርብና ሕግና ማህበራዊ አስተሳሰቡም ለሰብዓዊ መብት ቅድሚያ እንዲሰጡ ለማሳሰብ ነው።

ውድ አንባቢያን ሕዝቦች በመቻቻል ከልዩነት ይልቅ አንድነትን ከጦርነት ይልቅ ሰላምን በየጉራው ከመጋደል ይልቅ ተደራድሮ መስማማትን እየመረጡ ይታያል። የተከፈሉት የዓለም ቤተሰቦች በሰላም የመገናኘት ፋና በጀርመኖች፣ በየመኖች በዘር መድሎ ሥርዓቷ ዓለም ሁሉ ያወግዛት በነበረችው ደቡብ አፍሪካ ሳይቀር ምሥራቅ ከምዕራብ፣ ነጭ ከጥቁር፣ ራሱን ከራሱ፣ ራሱን ከሌላው እያስታረቀ የሰው ልጅ ዓለምን በእኩልነት፣ በሰላምና በፍቅር ሊጠቀምለት ይጨባበጣል እኛስ?????

በመጨረሻም ፀሐፊው በአካባቢያችን በተካሄደው ጭፍጨፋ ከተሳተፉት ውስጥ ከዋና ዋናዎቹ በስተቀር ከሥር የነበሩትን ዛሬ ሰላማዊ በመምሰል በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን አጫፋሪ፣ ገዳይና ጠቋሚ ግለሰቦች መጥቀስ አለመፈለጉ የወጣቶቹ መስዋዕትነት መድህኒትነቱ ለወንጀለኞችም ጭምር ትምህርት ነውና! በሕይወትም ሳሉ ያዝኑላቸው እንጂ አያዝኑባቸውም ነበረና የከፉ ድርጊታቸውን እንጂ ያደፈ ስማቸውን መጥቀሱን ትቶታል።

**ጭካኔ ሳይሆን ፍቅር የሰውን ልብ ይማርካል።**

**አብዲ አብዱላሂ**

## ምዕራፍ አንድ
## ትግሉ

በ1960ዎቹ የተቀሰቀሰው የመምህራንና የተማሪዎች እንቅስቃሴ የብዙዎቻችንን ትኩረት የሚስብ ሆነ። በወቅቱ የነበረውን የትግል ሂደት በገለልተኝነት የሚመለከት ምሁር ወይም ተማሪ አልነበረም ለማለት ያስደፍራል።

አብዛኛው ወጣት የህብረተሰብ ክፍል ዘመኑ ያበረከተለትን ፍሬ ጣፋጭነት ወይም መራራነት ለመቅመስ በስፋት እየጐረፈ ባለው እንቅስቃሴ ውስጥ ተዋሀደ።

በተማሪው መካከል ለተቃውሞ ... በማህበር መደራጀት ለነፃነት መታገል የሚሉ አንቂ የፖለቲካ ሀሣቦች በዕድገት በህብረት ዘማቾችና ይርጋ ዓለም ለትምህርት ሄደው በመጡ ወጣቶች አማካኝነት በተማሪው ልብ ተዘርተው ያቆጠቁጡ ጀመር።

በሁላችንም ልቡናና አንደበት በግልም፣ በቡድንም የሚታሰበው በአጀንዳም ቀርቦ የሚያነጋግረው ይኸው የትግልና የነፃነት ጉዳይ ሆነ። ቀናት እየገፉ ሲመጡ እንቅስቃሴያችን ስፋት፣ ጥንካሬና ቅርጽ እየያዘ መጣ። ህሊናዊው ሁኔታ ቀድሞ በፈነዳው ነባራዊ ሁኔታ ዙሪያ ይጐነጐን ጀመር።

በዓላማ ተደራጅቶ ለዓላማ መታገል ቅራኔው የወለደው ውጤት ነበርና ከአስተባባሪው አካል የሚፈልቁ ሕዝባዊ ጥያቄዎችና የአቋም መግለጫዎች በሰላማዊ መንገድ ጽሑፍ አዘጋጅቶ በመበተን፣ በስብሰባ ቅስቀሳ በማድረግ ተደጋጋሚ ስራዎች ተከናወኑ። ውጤቱም ሁለት ጐራዎችን አስገኘ። በአንድ ፊት ሕዝባዊው ወገን የቆመለት ላብ አደርና ድሀ ገበሬ (ሰፊው ሕዝብ) በተቃራኒው ደግሞ ደርግና መኢሶን ካምፕ ለይተው ተፋጠጡ።





ኢሕአፓ የሕዝባዊው እንቅስቃሴ መሪ ድርጅት በመሆን ለህብረተሰቡ የሚያስተጋባቸው ጥያቄዎች፣ መፈክሮች በሚያስደንቅ ፍጥነት 596 ኪ. ሜትር ተምዘግዝገው ለደጋፊዎቹ እንደአስፈላጊነቱም ለተቃዋሚዎች ጆሮ ይደርሱ ጀመር። የአዲስ አበባውና የቦረና ነጌሌው ወጣት ለትግል የልብ ንዝረቱ በእኩል ግፊት ይለካ ገባ።

በትምህርት ቤት ስቱደንት ካውንስል አስተባባሪነት አንገብጋቢ ጥያቄዎች ማለትም «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም፣ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ» ወዘተ. በመጠየቅ ለዚሁም ምላሽ እስኪገኝ ተማሪው በሚፈሩትና በሚጠሉት አጥፊዎች ፊት የማንባር ሥጋ ሆኖ ትምህርት በማቆም፣ በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞን በማሰማት የደርግን ልብ ያምሰውና ያውከው ጀመር። እሣትና ጭድ፣ ሆነው በመስከ ወደሚታዩበት የታሪክ ምዕራፍ ለመቅረብ ቀናትና ወራትን መከንዳት ተያያዙ።

## ሜይ ዴይ (1968)

ነጋሉብሩና ከዓለም ጋር «ኢንተርናሲዮናል»ን ልትዘምር ተዘጋጅታለች፡፡ ወጣቱ ለዓለም ላብ አደሮች የትግል አጋርነቱን ለማብሰር፣ ለሕዝቡም መሪ ድርጅቱን (ኢሕአፓን) ለማስተዋወቅ በቁጥሱቱ ትያ በሱድን እየሁን የመዝሙር ጥናቱን፣ የመፈክሮችና ዓርማ ዝግጅቱን ቀደም ባሉት ቀናት አቀላጥፎታል፡፡ ለሠላማዊ ሰልፉ የተዘጋጀት የመብት ጥያቄዎችና የተቃውሞ መፈክሮች በወታደሮችና በፀጥታ ፖሊሶች እንዳይታፈኑ ለማድረግ በላያቸው ላይ ደርበ በሚለብሰው የሚያላብሳቸው መፈክሮች ተለጥፈውባቸው ፍተሻውን በዚህ ስልት ካለፍን በኋላ ወደ አደባባዩ ዕምብርት ዘለቅን፡፡

ዛሬ ፊራርሶ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የታነፀበትና የከተማው አስተዳደር መናፈሻ የተሰራበት ትልቁ አደባባይ በሰይፍ አብደላ ሱቅና በሞናሊዛ ቡና ቤት በኩል ከያቅጣጫው የመጣውን ሰልፈኛና ተመልካች እምቅ አድርጎ ይዟል፡፡ መሐሉ ጣሊያን የገነባው ትልቁ የገበያ አዳራሽ ለትርዒቱ አደባባይነት የክቡራኑ ማማ ሆኖ ተመርጧል፡፡ ቁጥራቸው በበዛና ዘርዘር ብለው በሚታዩ ትልልቅ የጠጠሩና ድንጋይ ቅይጥ ምሰሶዎች ተሸካሚነት በሰፊው አየር ላይ በተዘረጋው ጣሪያ ስር ቅቤው፣ ወተቱ፣ እህሉ፣ ማሩ፣ የሚሸጥበት እርግብ ወፎች ኩሳቸውን የሚያንጠባጥቡበት በከፍታ ጉልቶ የሚታየው ግዙፉ ድንጋያማ የገበያ አዳራሽ ማዘጋጃ ቤቱ ባለበሰው ባንዲራ ምንጣፍና ሰፋ ወንበሮች ደምቆ የባለሥልጣናቱ የክብር መገኛ ሆኖ አይንን ማራኪ ሆኗል፡፡

ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች፣ የፖሊስ አዛዦች፣ የአስተዳደር ሰራተኞችና ሌሎች እጃቢዎቻቸው ደምቀው ተኮልኩለዋል፡፡ ፎቶ አንሺዎችና ካድሬዎች ወዲህ ወዲያ ይጣደፋሉ፡፡ ባለቀይና ነጭ ቅብ





ሄልሜት የደፉ የወታደር ፖሊሶች ዱላዎቻቸውን ይዘው እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይከታተላሉ፡፡

ሕዝቡም እንቅስቃሴያችንን በሥጋት ይከታተላል፡፡ ልጆቹ እንደ አሸዋ በዝተው፣ እንደ ከዋክብት አብርተው፣ በጀግንነት ሲያዜሙ፣ ሲፈክሩ ና በዘዴ የተሸፈነውን አርማና የተቃውሞ መፈክሮች ገላልጠው ይፋ ሲያደርጉ፡-

ባለሥልጣናቱ በውጥረት ውስጥ ገቡ፡፡ የገዛ ዓይናቸውን ማመን አቃታቸው ተያዩ... ሀፍረት ሸንቆጣቸው ... በንዴት ጦፉ... ተቅበጠበጡ፣ በሰይጣናዊ የቁጣ ፈረስ ተፈናጠጡ፤ በአምባገነናዊ ትዕዛዝ በፀጥታ ኃይሎቻቸው ላይ እንደ መብረቅ አምባረቁባቸው፡፡ «... ምንድነው የያዙት?! ... ምንድነው የሚሉት?! ... እነዚህን ጥጋበኞች በትንልኝ!!» አሉ፡፡ ወታደሩ፣ ፖሊሱ ለውጊያ ተቀሰቀሰ፤ መፈክሩና መዝሙሩ ግን በወኔ ቀፀለ፡፡

«መሬት ለአራሹ ከታወጀለት
ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋምለት
ነፃነት ነፃነት የምትሹ
ተዋጉለት አትሸሹ» እያለ ዘመረ፡፡ በስሜት መፈክሩ ተስተጋባ «ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነው! ! የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ» በዚህ ላይ የፓርቲውና ዓለም-አቀፍ የሠራተኛው ዓርማ ከፍ ብለው ተውለበለቡ፡፡

ታላቅ ድንጋጤ... ቁጣ... ድንፋታ... ኃይል «ያዘው ... በለው... ቁም! » ትርምስ ሆነ፡፡ ተማሪው በቆመጥ፣ በሰደፍና በአፈ-ሙዝ ተወገረ! ተበታተን፡፡ በዚህ ጊዜ የተጨናነቀው ተመልካችና ሰልፈኛ በሚገርምና በሚያሳዝን ሁኔታ ከዱላው ሲሸሽ ቀዩ አቧራማ ሜዳ በብዙ ሺ የወለቁ ጫማዎች ተሞላ፡፡ በወቅቱ አንድ ትልቅ የጫማ

መደብር አምጥቶ ቢበትን የዚያን ያህል እንደማይበዛ ፀሐፊው ይገምታል:: አልፎ አልፎ በኢብራሂም ወሎዬ ሻይ ቤት በእህመድ ጋይድ (ቢስ ሱቅ) በሰርበላ ሱቅና በፎቶ ሊበን፣ በፎቶ ሐውልት በረንዳዎች ከሚታዩ ሰዎች በቀር ሕዝቡ እግሬ አውጪኝ ብሏል::

በአደባባዩ መካከል በዱላ እየታገዘ የሚሄድ ኑሮ ኢብራሂም የሚባል እካለ ጉደሉ ልጅ ይታያል! መሄጃው ጠፍቶት:: የሚይዙት ሲያጡ ፖሊሶች ይሄንን መሸሽ የሌለው ልጅ ከበው በዱላ እና በሽፍሽፊ ክፉኛ ደበደቡት:: የጭካኔ እርምጃቸው ቀጠለ:: በአደባባዩና በከተማይቱ ጉዳናዎች የልጆችና የወላጆች የጭንቅ ጩኸት በዛ:: ስብራት ... ውልቃት... ደም:: ደርግ በሜይ-ዴይ ምሱን አገኘ:: የተጠማውን ደም ማሳደዱ ቀጠለ:: እሥራት... ግርፋት... ሥቃይ::

ተማሪው መስዋዕትነትን አሸተተ:: ይህ የመጀመሪያ ጀብዱ የብዙዎችን የትግል ስሜት አረካ:: የቀደምት ታጋዮችን ጥሪ እያስተጋባ ልቡ ሸፈተ! አመፀ

«ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ

እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ...» አለ:: ዛሬ ቀለም እያንጉራጉርም እንጂ ! ብዕር እያዜምም እንጂ የወጣቱ ስሜት አሁን እንደሚነበበው ሳይሆን ያኔ እንደሚነድደው ነበር::

የደሀ ሕዝብ ማህፀን እንደ እሣት የሚፋጁ ትንታጉችን አፈለቀ:: ደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣቱን በተቃዋሚነት መነሳሳት ሲያይ ለጉስቋሎች መታገል ተዐምራዊ ኃይል እንደሚያመነጭ በምሬት ተገነዘበ:: እነዚህን ለጋ የነፃነት ታጋዮች ሞት ደግሶ ማጉረስ እንዳለበት አመነ::





ወታደሩም፣ ፖሊሱም፣ ደህንነቱም፣ ካድሬውም፣ አሸርጋጁ ተመራጩም ከተት ሠራዊት ብሎ በሕዝብ ልጆች ላይ የሞት መጋዙን ደገነ:: ማደን! ማሳደድ የደርግ የዕለት በዕለት ክንውን ሆነ:: ነጌሌ ሞት አርግዛ ታምጥ ጀመር::

የወጣቱም ትግል ከአደባባይ ስሜታዊ እንቅስቃሴ ወደ ተቀናጀ ድርጅታዊ አሰራር በማምራቱ የድርጅቱ ርዕዮት በየህዋሱ መወያያ ሆነ:: የፓርቲው ልሳን «ዲሞክራሲያ» ከዚህ ጋር በፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳው ዓይነተኛውን ድርሻ ትወጣ ጀመር:: ዓላማው ውስጥ ለውስጥ በወጣቱ ደም ስር እየተዋሀደ መጣ:: ለመስዋዕትነት ብዙ ጀግኖች አበቡ፣ አቆጠቆጡ:: ፋሺዝምን ለማውደም ወደፊት!

ከፋሺስታዊው መንግሥት ያገኘነው ምላሽ በስልት እንድናሸምቅ ቢያስገድደንም የቀደመው ተንደርዳሪ አመፃችን የመረጃ ዓይኑን እንዲጥልብን ስላመቻቸ ደህንነቱ ገበሬውን በገጠር በምናደራጀው አባላት ላይ አተኮረ:: በመጋቢት ወር በማላስታውሰው ምሽት ለጋጉላ ገበሬ ማህበር ከገበሬዎች ጋር ስንሰራ አምሽተን ከምሽቱ አንድ ሰዓት ስንመለስ ሹና ገ/ማርያም በምሥጢር ተልካ እኔ አደን አብዲና ኢብራሂም ዓሊ በጥብቅ እየተፈለግን እንደሆነና እንድንሰወር መላኳን ስለገለጸችልን በቀበሌ 06 በአቶ ሺዶ ቤት ለአንድ ሳምንት ተደበቅን::

የአካባቢያችን የድርጅቱ አመራርም የኢሕአፓ ኢሕአሠ በሰሜኑ አህገራችን ክፍል (አሲምባ) ለጀመረው ወታደራዊ ስልጠና ሦስታችንን በመመልመሉ ለዚሁ ተልዕኮ ከጠረፋማዋ ከተማ ኔጌሌ ወደ ደጋማው የሀገራችን ክፍል እንድንሰደድ ግድ ሆነ::

# የአገር ውስጥ ስደት

ከአንድ ሣምንት ቆይታ በኋላ በዱምዱሚ ልጆች የጭነት መኪና ወደ ከብረ-መንግሥት ተጓዝን:: በዚያን ሰዓት የነበረው መተማመንና መረዳዳት፣ ጅርጅታዊ ፍቅርና ዲሲፕሊን ያጉናፀፈን ቅርስ ነበር:: ከብረ መንግሥት ለሦስት ወራት በአንድ የመምህራን መኖሪያ ቤት ቆየን:: በረናም ሆነ ጀምጀም የድርጅታችን ሰዎች ዓላማ ያቆራኛቸውና አንድ ያደረጋቸው ስለሆኑ ያለ ባይተዋርነት አሳለፍን::

በመምህራኑ ቤት በነበርንበት ጊዜ ከድርጅቱ አካል ጋር በነበረን የጠበቀና ተከታታይ ግንኙነት የጽሑፍ ሥራዎች ከአማርኛ ወደ ኦሮምኛ በመመለስና በካሴቶች የቅስቀሳ ስራዎችን በማተም ተሳተፍን:: ሁኔታው ተረጋግቶ አልቀፀለም:: መምህራኑ በነበራቸው አቋም የመንግሥት ክትትል በአካባቢያቸውና በሕይወታቸው ጥላውን ስለጣለ ወንጶንና አዋሳን የመሸጋገሪያ ከተማ በማድረግ ብዙም ሳንቆይ ወደ ሻሸመኔ አመራን:: በዚህ የአራት ወራት ቆይታችን አድራሻችንን፣ ድርጅታችን እንጂ ቤተሰቦቻችን መኖር፣ መሞታችንን አያውቁም:: ሻሸመኔም እንደጀምጀሙ ሁሉ ከድርጅታችን ጓዶች ጋር በአደን አብዲ አማካይነት በመገናኘት ሥራዎችን እንሰራ ነበር::

ቅሌን ጨርቄን የሌለበት ስደት እጣዳፊ ስለነበረ ባለበስነውና በተጫማነው በመውጣታችን ያቹኑ ለማንፃት ካጠብን እስክትደርቅ ድረስ ራቁታችንን መጠበቅ ግድ ነበር:: ያኔ በወንዝ ዳር በፓንት (የውስጥ ሱሪ) ብቻ ተኮራምቶ የነበረ ዕርቃናችን ምስል በቅርብ ትናንት እንደሆነ ሁሉ ዛሬ ጉልቶ ይታየኛል:: አሁን ከምመራው ኑሮ አንፃር ያኔን ስመዝነው በመከራ ውስጥ ሆኜ እንኳን በፍፁም ደስተኛ መሆኔን አስታውሳለሁ::





ሻሸመኔ ካሳለፍነው የአንድ ወር ተኩል ቆይታ ለመውጣት ምክንያት የሆነችንን ቀን በተለይ አስታውሳለሁ:: በጣም የምትገርም ቀን ነበረች:: እኔና ጓደኞቼ በአጋጣሚ በወንዶ ገነት የሥጋ ፋብሪካ ውስጥ ይሰራ ወደነበረ የነጌሌ ልጅ (መሀመድ ጃማ) ሄድን:: ከእሱ ጋር ተገናኝተን ምሣ ከበላን በኋላ ስለ ወቅቱ ሁኔታ ባደረግነው ውይይት በመስመር የተለየ ሰው መሆኑን ተረድተን በማዘን ስንመለስ ከመኪና ይልቅ ጫት እየቃምን በእግራችን ወደ ሻሸመኔ መጓዙን መረጥን:: በዚሁ ዕለት የሻሸመኔ ከተማ ሆቴሎች በዓሊ ሙሳ ጦር ክፉኛ እየታሰሱና እየተበረበሩ ነበር:: እኛ ግን መንገድ ላይ ነን:: ይህ አጋጣሚ ባይሆን ዓሊ ሙሣ ከዘርዓይ ደረስ ሆቴል ሦስት ምርኮኞች ባገኘ ነበር::

አራተኛው መጠለያችን ይርጋ-ዓለም ከተማ ነበር:: ዛሬ የቤቱን አቅጣጫ በውል ባላውቅም መኖሪያው የአንድ ነጋዴ ጉራጌ ቤት እንደሆነ ከትልቁ ልጃቸው ተረድተናል:: በዚህ ቤት ከሦስት ወር በላይ ስንቆይ ከአዲስ አበባ የሚመጡ በራሪ ወረቀቶችን እናባዛለን፣ ባካባቢው የሚበተኑና የሚሰራጩ አረቂቅ ጽሑፎችን እነገለብጣለን፣ በጠቅላላው የተወጠነው የጉዟችን ግብ በየቦታው እየጐላ በመጣው ማሳደድና ውጥረት ሳቢያ ሊመፈም ባለመቻሉ ያለው አማራጭ በአንድ ቦታ ተወስኖ ፋታ በማይሰጥ የድርጅቱ ስራ እራስን መጥመድና ኃላፊነትን መወጣት ብቻ ነበር::

ጊዜው በጣም አስፈሪ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ በአንድ ክፍል ውስጥ በመኖርና ከክፍል ውጪ የፀሐይ ብርሃን እንኳ በደንብ ለማግኘት ባለመቻላችን፣ በትዕግሥት፣ በዲሲፕሊን የተቀጠ ጭንቀትና ብስጭት በቀላሉ በፊታችን ላይ ይነበባል:: የማይገለጽ ሆደ ባሻነት፣ የተጠቂነት፣ የተንከራታችነት፣ ስሜት ውስጥ ውስጣችንን፣ አንጀት አንጀታችንን ይበላናል::

ይሄ ሁሉ ሆኖ የመጻሕፍትን ገጾች እያገላበጥን ማንበብና በንድፈ ሀሣቦችም ላይ መወያየት የየዕለት ክንውናችን ነው:: በዚህ በተለይ ከባድና ከፍተኛ መስዋዕትነትን በሚጠይቅ ጽሉም ወቅት አንድ ቀን በመካከላችን የተፈጠረውን ውይይት ልቤ አይዘነጋውም::

«የብሔሮች መብት እስከመገንጠል» የሚል ማርክሲስታዊ ትንታኔን ያዘለ የስታሊን ጽሑፍ ነበር:: በሀሣቡ ላይ ብዙ ስንነጋገር ቆየን:: በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የዚህ ንድፈ ሀሣብ አፈጻጸም ምን ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ስንነጋገር (ስንከራከር) አደን ብዙ ጊዜ በስሜት እየተዋጠ በኃይል ምላሾችን ይሰጥ ስለነበረ አቀራረቡ አበሳጨን::

እኔና ኢብራሂም ... «ስማ አደን በዚህ ውይይት ላይ የምትወረውራቸውን አምባገነናዊ ቃላት አርም ይሄ አጉል ጀብደኝነት ነው» በማለት በዝርዝር የማላስታውሳቸውን የሚያስከፉ ቃላት አወረድንበት:: አደን ደነገጠ:: ሳይናገር ዝም ብሎ ቆየ፣ ዓይኖቹ በጥያቄ በረበሩን:: አቀረቀረ፣ በዕንባ ተሸነፈ:: ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙሮ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ግራ ተጋባን:: ተያየን ዙሪያችንን ሞት ከቦናል:: ልናግባባው ብንይዘውም ባሰበት::

ለሀዘኑ ምክንያት በመሆናችን ሳይሆን የመብት ማጣታችንና መሰደዳችንም ምክንያት ሆድ አስብሶን እንደሆን እንጃ እኛም አብረነው አጉነበስን:: አደን ዞር ብሎ «እናንተ ለምን ታለቅሳላችሁ? ምን ሆናችሁ? እስኪ ዝም በሉ» አለን :: አንተ ነህ ወደዚህ ውሉ ወደጠፋ ሀዘን ውስጥ የጨመርከን ግን ለምን አለቀስክ? አልነው:: በዚህ ጊዜ አደን ከተቀመጠበት ከመቅጽበት ብድግ አለ::

«... አብዶ እኔ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከእናንተ በፊት እሞታለሁ:: በትክክል ይታየኛል:: ያስለቀሰኝ የአሁኑ ትችታችሁ ሳይሆን ከኔ ሞት





በኋላ ታሪኩን ስትመሰክሩ በዚህ መልክ ጀብደኛና አምባገነን እንደሆንኩ አድርጋችሁ እንደምትገልፁኝ አስቤ ነው ያለቀስኩት» ብሎ ግድግዳውን ተደግፎ አለቀሰ:: አደን ይሄንን ሲል ስለሕዝብ ፍቅር የሚፈስ የንፁሕ ሰው ደም ታየን:: ስለ እውነት የሚነድ ዕምቅ ሀዘን ፈታን እኛም አብረነው አለቀስን::

ከኢብራሂም ጋር ተነስተን ልናጽናናው ሞከርን:: የዚያ አስቃቂ ዘመን ንክሻ ውስጣችንን አዘሎ-ታል መሰለኝ ሦስታችንም በጠባቧ ክፍል ተቃቅፈን ስናነባ በሩ ተንኳኳ:: በመካከላችን ፀጥታ ሆነ፣ ተደገመ:: አሁንም ፀጥታ:: እንደገና ተደገመ፣ በጭንቀት ... ተያየን «ተበላን» በሚል ስሜት:: እንዳችን «ማነህ» አልን «ዓለሙ ነኝ» የሚል ድምፅ ሰማን የቤቱ ልጅ ነበር::

በይርጋ-ዓለም ከተማ መቆየቱ ከቀን ወደቀን አስጊ እየሆነ በመምጣቱ የቀረን ምርጫ አሲምባ ለመድረስ አላስፈላጊ መስዋዕትነት ከመክፈል ይልቅ ወደ ነጌሌ ተመልሰን በገጠር መቆየቱን እንድንመርጥ ሁኔታው ስላስገደደ ድርጅቱ በቀየሰው ስልት ዘመድ እንደሞተበት የሀዘን ልብስና ቆብ ተዘጋጅቶልን እኔና ኢብራሂም ወደ ክብረ-መንግሥት ስንጓዝ አደን ወደ አዋሣ ተመለሰ:: ከክብረ-መንግስትም ነጌሌ ገባን ከሁለት ሳምንት በኋላ አደንም መጣ::

አደን ነጌሌ ሲገባ በመታየቱ እንዲያዝ አሰሳው ተጠናከረ ሆኖም ድርጅቱ ያዘጋጀው ስልት በአርሶ አደሩ ተባባሪነት ታግዞ ልክ እንደ አብዮት ጥበቃ ጓዶች በመልበስና በመታጠቅ በምሽት ቀጠሮ ተሰጣጥተን በተለያየ አቅጣጫ ወደ ገጠር ወጣን::

ገጠር ከገባን በኋላ በነጌሌ አካባቢ አንድ ሁኔታ ተከሰተ:: ይኸውም መንግሥት በግፍ ለአንድ ዓመት ያህል በነጌሌና በአዋሳ **ወህኒ ቤት የወንበዴ** ቀላቢ ነህ በሚል ያንገላታው አቶ አሊ ኩንሶ

አርብ የካቲት 25/1969 በሱማሌ አቦ ሽምቅ ተዋጊዎች በመኖሪያ ቤ እያለ በመገደሉ ሰዎቹን ለመያዝ በተደረገው ከበባና የተኩ ልውውጥ የ፶አለቃ ሸዋ ታጠቅ ወልደጊዮርጊስና የ፲አለቃ ሞገ ዳኛባለው በመሰዋታቸው ተከበው ከተገደሉት ሽማቂዎችም አፍ ጫት በመገኘቱ መንግሥት አጋጣሚውን በመጠቀም «ከተማው ውስጥ ካሉት ፀረ-አብዮተኞች ጋር ተባብረው የፈጸሙት ነው በግንኙነት መንቀሳቀስ ጀምረዋል» በማለት የከተማውን ዙሪያ በሠራዊት ኃይል በማጠር አሰሳውንና ማሳደዱን ቀጠሉ:: ቤተሰቦቼም ወደገጠር ለእጉቴ በላኩት የአደራ መልዕክት ካረፍኩበት መንቀሳቀስ እንዳልችል ዘመዶቼ ተፅዕኖ ስላደረጉብኝ ከእነአደን ጋር በተቀጣጠርነው ቀን መገናኘት ሳይሳካልኝ ቀረ:: እነሱ ግን ከመርሳ ነጌሌ እንደገቡ አደን በሚፈልጉት ጠላቶቹ እጅ ወደቀ:: በመምህር ሙሉጌታ ዘሩ በሚመራ የሮንድ ቡድን ተያዘ እንደተነበየውም ከሦስት ወር በኋላ ከእኛ በፊት ሞተ:: ኢብራሂምም አሳድደውት እንደነበረና እንዳመለጠ ሰማሁ:: ከዚያ ወዲህ እስከ አሁን የት እንዳለ ይሙት ይኑር አላውቅም::

በውጣ ውረዱ የማፈቅራቸውንና የማከብራቸውን ጓዶቼን አጣሁ:: የልቤ ብርታትና ጽናት ከኃይለኛ መሠረቱ ተናጋ:: በቢታታ፣ በገናሌና በመዱወላቡ ለአራት ወራት ያህል ከዘላኑ ሕዝብ ተመሳስዬ ቆየሁ:: በከተማ እስራቱ፣ ግርፋቱና ግድያው እየተባባሰ በመሄዱ ላለመመለስ ወሰንኩ:: የገጠሩንም ቆይታ ከሚሰማኝ ብቸኝነትና ጭንቀት የተነሳ ልቋቋም ባለመቻሌ ወደ ጐረቤት አገር ለመኮብለል ወሰንኩ::





## ስደት ከአገር ውጪ

በገዛ ሀገሬ ሰብዓዊ መብቴን፣ ነፃነቴን ከተቀማሁ ምን አገር አለኝ ብዬ እቀመጣለሁ:: ከአንግዲህ የቀረኝ ነገር ቢኖር፣ ዕምባ ሳይሆን ደም እያለቀስኩ የቀኑን ሀሩርና የሌሊቱን ቁር በመቋቋም የሀያ አምስት ቀንና ሌሊት አድካሚ ጉዞን መጋፈጥ ብቻ ... ወደ ሶማሊያ::

አብረውኝ የሚጓዙ ባላገሮች እግረ ጃቢራዎች ናቸው መንገዱ ይጠቀለልላቸዋል:: እብዶ ከተሜው የመጀመሪያውን ሣምንት ጉዞ እንደምንም ተበራታሁ የሁለተኛው ሳምንት ቀንና ሌሊት ጉዞ እጅግ አድካሚ ሆነብኝ:: በበረሀ ከምቀር ብዬ ተንከላወስኩ:: ጥለውኝም እየሄዱ እያበራቱኝም የሕይወት ሳይሆን የሞት ጉዞ ተጓዝኩ:: ሁለንተናዬ ወላለቀ::

በተለይ የሌሊቱ ጉዞ ምንም እንኳ አናት ከሚበጠርቀውና ጉሮሮ ከሚያደርቀው የበረሃ ንዳድ ቢከልልም ከእሾሁና ጋሬጣው ግን ሊያድን ባለመቻሉ የግራ እግሬን ከፉኛ ተወጋሁ:: እንጨቱ ውስጡ ተሰብሮ በመቅረቱ ሕመሙ እየጠናብኝ ሄደ:: በዚህ ጊዜ ባላገሮቹ ከችግሩ ሊያላቅቁኝ የመረጡት መንገድ ያልሰማሁትና የሚያስደነግጥ ነበር:: እባካችሁ ተውኝ ብዬ እንዳልማፀን ሊያስኬደኝ አልቻለም:: እንዳላችሁት ይሁን እንዳልልም ፈራሁ:: ብቻ አልቀረልኝም በጉት የታጠቀውን ጩቤ መዞ እንጨቱ በገባበት አቅጣጫ በስለት ሰነጠቀልኝ:: እሪ አልኩ እንደምንም ጩኸቴን ታግሰው እንጨቱን አወጡልኝ:: ቀጥለውም አገልግሎቱን የጨረሰ የባትሪ ድንጋይ ከስክሰው ዱቄቱን በሚደማው እግሬ ላይ በመደምደም በቅጠልና በአሮጌ ጨርቅ ጠቀለሉልኝ::

የባላገሮቹ አስደናቂ የቀዶ ጥገና (ኦፕሬሽን) ብዳክምም እንኳ ጉዞዬን እንዳላቆም አረዳኝ። አንድ ቀን ንጋት ላይ ካረፍንበት ተንስተን ስንጓዝ ውለን እኩለ ቀን አካባቢ አንድ ገደላማ ቦታ ደረስን። ሁሉም የውኃ ጉድጓድ ፍለጋ ሽጡን ይዞ ሲወርድ እኔ አለፍ ብሎ ባሻገር ካለው አረባዳ ቦታ ላይ አንድ ልትወድቅ የደረሰች ግግባ በቅሎ አየሁ። ሳይታወቀኝ ድምፄን ከፍ አድርጌ ባትቀድሙኝ ያቺ በቅሎ የኔ ነኝ ባትቀድሙኝ አልኩ። ሁኔታዬን አይተው ሁሉም ሳቁብኝ። ጭንቷን ይዛ ይሄንን የበረሃ ጉዞ መወጣት ባለመቻሏ የተጣለች ወገበ ሰባራ መሆኗን ነገሩኝ። ቢሆንም አልተቀበልኳቸውም። እንደምንም ጉትቼ በአንገቷ ላይ ሽርጤን ካሰርኩ በኋላ ለአንዲት ቀን ብቻ ተጓዝኩባት። እውነትም ሰዎቹ እንዳሉት ክብደቴን ባለመቻሏ ተለያየን።

ድንበር ለማቋረጥ ሦስት ቀን ሲቀረን እግሬ እየተሞሽላለቀ አነባሁ! ተንዘፈዘፍኩ። ባላገሮቹ እንደምንም እግሬን ክፉኛ እየጠዘጠዘ አላራምድ ያለኝ ደምና መግል ያዘለ እብጠት ካፈነዱልኝ በኋላ የመጨረሻዋን ሌሊት የድንበር ማቋረጫ ፈጣን ጉዞ መወጣት ካልቻልኩ እነሱንም በጠላት ዒላማ የማስገባቸው መሆኑን ገልጸውልኝ ይህንን ዕድል ካልተጠቀምኩበት ድካሜ ሁሉ ከንቱ መሆኑን በቁጣ አስረዱኝ።

እንደኛዬን «የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ይከበሩ» የምትለዋልን መፈክር እንደያዝኩ በጓዶቼ መሀል ወድቄ ቢሆን ምኞ የክብር ሞት እንደሆነ ሳስብማ ከየት መጣ የማልለው ኃይል አገኘሁ። ተነሳሁ፣ ጉዞውን ጨርሼ ጐረቤት አገር ሶማሊያ ገባሁ። ለሦስት ሳምንት ያህል በቡልሀዋ ከተማ ቆየሁ። በጉዞው መድከሜንና መድቀቄ የተሰማኝ ባረፍኩባቸው ቀናት ነበር። ቀን ቀን በእውኔ በተቀመጥኩበትና በተጋደምኩበት መንፈሴ ቆንጥር ለቆንጥር፣ ጥሻ ለጥሻ እየተጓዘ ቁና ቁና እስክተነፍስ ያስተክዘኛል። ሌሊት ሌሊት





ደግሞ ቅገሮቱና አስፈሪው ሕልም ከጠላሁትና ከሸሸሁት ደርግ ጉያ ወስዶ ይከተኛል። እግሬ እርቆ ቢሄድም ልቤ ግን የጭንቅና የመከራ ቋት ሆና አደከመችኝ።ብቻ እንደምንም አገገምኩ።

ቀጣዩ ግቤ በኢትዮጵያ መምህር የነበረው ታላቅ ወንድሜ መሀመድ በስደት ቀድሞ ወጥቶ ሞቃዲሾ ስለነበረ ወደ እሱ ሄድኩ። በዚያም ቆየሁ። በስደተኛነቴ ተስፋ ከልቤ ተሟጠጠ። የተከተለኝ ነገር ቢኖር ጭንቀት፣ ሀዘን፣ ፍርሀት፣ ዕምነት ማጣት ብቻ። ፋሺስቶች ከወንድሞቼ ብቻ ሳይሆን ከወገኖቼም ከሀገሬም ለዩኝ በበለጠም ጤነኛና ብርቱ ሰውነቴን ከራሴ ሰረቁኝ (ነጠቁኝ)።

አጋጣሚውም ለአሳር ሲያብር ነው መሰለኝ ታላቅ ወንድሜ በአስጊ ሁኔታ ታመመ። አይናገርም፣ አይንቀሳቀስም። በጠቅላላው ራሱን መቆጣጠር በማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የሞቃዲሾእንግድነቴ አስጨናቂ ሆኖ አከረመኝ ያም አለፈ ወንድሜ በአምላክ ፈቃድ ተፈወሰ።

ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የዘጋሁትን የትምህርት ቤት በር በሞቃዲሾ ከፈትኩ። ወደ ሱማሌ ከሸሸነው መካከል ብዙዎቻችን በኢሕአፓ ምክንያት ቢሆንም ሁለት ወጣቶች ከተቃራኒ ወገን የነበሩና አባታቸው በቀይ ሽብር ብዙ ለጋ ወጣቶችን ያስፈጀ በመሆኑ በስደቱም ሥፍራ የትምህርት ቤት ውሎአችን በጐሪጥ ያስተያየን እንደነበር ሳስብ በአገር ውስጥ የተጠነሰሰው ልዩነት ውጭም በማይተናነስ ስሜት እንደተፈታተነን ትዝ ይለኛል። ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁም በጌዶ ክፍለ ሀገር በገርበሀሬ ከተማ በመምህርነት ተመድቤ ለሦስት ዓመታት አገለገልኩ።

በዚህ ስፍራ በነገሌ ቦረና አብረን የነበርን (መሐመድ አባ ኑር) ለስደቱ ምክንያት የሆነውን ሲያጫውተኝ የሚይዶይ በዓል ሲከበር

ወጣቱ ኢሕአፓን ያስተዋወቀበትና ደርግን ያወገዘበት አለት በመሆ ሰልፉም ሲበተን ሸፍሽፋና ኮምፖርሳቶ በመገኘቱ «የእድገት በሕብረ ዘመቻችንን አቋርጦ የመጣው ያጣውላው መሰንጠቂያው ባለቤት ለተቃዋሚዎቻችን የቁሳቁስ አቅርቦት ስላደረገ ሊመታ ይገባዋል በማለት ስለፈለጉት እንደሆነ ሲገልፅልኝ በተመሳሳይ ምክንያት ስንት ኢትዮጵያውያን በሱማሊያ፣ በጂቡቲ፣ በሱዳን፣ በኬንያ ወዘተ. ይሰደዱ ይሆን? አልኩ።

ምንም እንኳን ከደርግ የጭካኔ ብትር ለማምለጥ ድንገት አቋርጬ ብሄድም በወቅቱ በሶማሊያና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው ግጭት ሳቢያ የነበርኩበት ከተማ በኢትዮጵያ ተዋጊ ጀቶች ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ስለተደበደበ፣ ፊቴን ያዞርኩ እንጂ የሸሸሁ አልመስልህ አለኝ። በተለይ በመጨረሻው ድብደባ በአጋጣሚ በትም/ሥራ ላይ እንዳለሁኝ የመኖሪያ ቤቴ በመደምሰሱ እኔን ለማደን እንደተላኩ ያህል ሆኖ ተሰማኝ።

ከሦስት ዓመት አገልግሎት በኋላ ወደ ሞቃዲሾ ተዛወርኩ። ከዚያም ቆርየሌ በምትባል ከተማ ተመድቤ ትዳርም መስርቼ ለስምንት ዓመታት ተቀመጥኩ። መቃብሬ የተሰማልኝ ሰው የአምስት ልጆች አባት ለመሆን በቃሁ።

በሶማሊያና በኢትዮጵያ ጦርነት ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን በስደት ወደ ሱማሊያ ገቡ። በተለያዩ ቦታዎች የስደተኞች ካምፕ ተመሠረተ። በዚህ ጊዜ ከመደበኛ ሥራዬ ሌላ በትርፍ ጊዜዬ «የሕፃናት አድን ፌዴሬሽን» ከሚባል የአሜሪካን የተራድኦ ድርጅት ጋር መሥራት ጀመርኩ። በዚህ አጋጣሚ በስደተኞች ካምፕ የጓደኛዬን የአደን አብዲን አባት አገኘሁት ታሞም እስከሞተ ድረስ





በልጁ መንፈስ ወደድኩት። የቀብሩንም ሥርዓት በድርብ ስሜት ፈፀምኩ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ለ «ሕፃናት አድን ፌዴሬሽን» በቋሚነት ማገልገል ጀመርኩ። ከመምህርነት ወደ ልማት ሠራተኛነት ተቀየርኩ። ድርጅቱም ለሥራው ብቁ የሚያደርጉኝን የአጭርና የረጅም ጊዜ ልማት ነክ ትምህርቶች በዚምባብዌ፣ በኬንያ፣ በሕንድና በፊሊፒንስ እየላከ እንድማር ረዳኝ።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በዲሰምበር 1990 የድርጅቱ የምሥራቅ አፍሪካ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ወደ አዲስ አበባ እንድመጣ ጥሪ አቀረበልኝ። ዱብ ዕዳ! ...ያ ብዙ ወንድሞቼን ኢ-ሰብአዊ በሆነ መልክ የፈጀና ብዙዎችን ከአገር ያሳደደ መንግሥት ሥልጣን ላይ ነው። ደምደም አለኝ። አገሬን ለማየት ካለኝ ጉጉት ባላነሰ ሥጋትና ፍርሀትም ከበበኝ። ቢሆንም አዲስ አበባ ገባሁ። የመጣሁት ለአንድ ሣምንት ቢሆንም መመለሻዬ ሞቃዲሾ በጎሣዎች መካከል በተፈጠረ መተላለቅ የጦርነት አውድማ በመሆኗ ለሦስት ወራት በመዲናችን መቆየት ግድ ሆነብኝ። ጦርነቱ በቤተሰቤ ላይ የሚፈጠረውን አደጋ ሳስብማ ልቤ በጭንቀት እየተወራጨ ፍጹም ሰላም አጣሁ።

የመጀመሪያ የአ.አ ቆይታዬ ቤተ ዘመዶቼን የማግኘት ዕድሌን ያጣበበ በመሆኑ አልጥምህ አለኝ። ይብሱኑ ያስጨነቀኝ ከድርጅታችን መ/ቤት ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ በትልቁ በጉልህ ቀለም የተጻፈውን «ሞት ለኢሕአፓ» የሚለውን መፈክር ባየሁ ቁጥር አሁንም የምፈለግ መሰለኝ። ፈራሁ። በዚሁ ምክንያት በዋቢሸበሌ ሆቴል የሦስት ወር ቆይታዬ አንዲት የአማርኛ ቃል ሳልተነፍስ ዱዳ መስዬ አሳለፍኩ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተሰቦቼን ለመገናኘት ወደ ነገሌ ስልክ ደውዬ ወላጅ አባቴን አነጋገርኩት:: በሕጋዊው ሳይሆን በቤት ስሜ አብድርቃድር ነኝ ብዬ ስለጤንነቱና ስለቤተሰቡ ሁኔታ ጠየቅሁት:: ላገኛቸው እንደምፈልግም ነግሬው አድራሻዬን ገለፅኩለት:: አባቴ በእሺታ ስልኩን ዘጋ:: የእኔን አዲስ አበባ መገኘት በሕልሙም ሆነ በእውኑ የማይጠብቀው ስለነበረ ከጥሪው በኋላ ተጠራጠረ (ተወነባበደ):: ልቡ በአቅራቢያችን ከቤተሰቦቼ ቅርብ ትውውቅ ወዳላቸው ወደእነ አብድርቃድር ሐዋስ ቤት አዘነበለ:: በቀጥታ ቤታቸው ሄዶ «ልጃችሁ አብድር ቃድር ከአዲስ አበባ ስልክ ደውሏል:: በጣም ሰላምታ ሰጠኝ! እናንተም መጥታችሁ እዩኝ ብሏል» አላቸው:: በእርግጥም ልጃቸው አብድርቃድርም አሜሪካን እንደነበረ ስለሚያውቁ ናፍቆታቸውን ሊወጡ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ ገሮ ወደ አዲስ አበባ መጡ ልጃቸውን ሳይሆን እኔን ሲያገኙኝ ደነገጡ:: ተደሰቱም:: አባቴ በስህተት እንደላካቸው አስረዱኝ:: ተመልሰውም ለቤተሰቦቼ እኔ እንደሆንኩ አረጋገጡላቸው:: ታናሽ ወንድሜ ሁሴን አብዱላሂ ተላከ::

በአድራሻዬ ሲመጣ ይዤው ወደመርካቶ ወጣሁ እንደልብ እንድንጫዎወት:: ስለብዙ ጉዳዮች በማብራራት እንዲያጫውተኝ ጠየኩት በጭውውቱ አሳዘነኝ! አስደሰተኝም! አረጋጋኝ አረበሸኝም:: ለሚቀጥለው ቀን ተቀጣጥረን ወደማረፊያ ሄድኩ በማግስቱ ሳይመጣ ቀረ:: በሁለተኛውም ቀረ:: በሶስተኛውም ቀን እንዲሁ ደነገጥኩ የት ብዬ ልፈልገው? ተጨነቅሁ:: በሰባተኛው ቀን መልዕክት ደረሰኝ ለካስ አዲስ አበባ ለብሔራዊ ውትድርና አፈሳው ተጧጡፎ ኖሮ ሻንጣውን ከነልብሱ ከያዘበት ቤርጐ ሳያወጣ እግሬ አውጪኝ ብሎ መመለሱን ነፈልኝ:: ወይ ጉድ! ይሄ ወታደራዊመንግሥት በጠመንጃ ስልጣን ያዘ፣ በጠመንጃ ባለስልጣን ፈጀ፣ በጠመንጃ ሰበሰበ፣ በጠመንጃ በተነ፣





በጠመንጃ አደራጀ፣ በጠመንጃ አስለፈ፣ በጠመንጃ አፋጀ፣ በዚህ ምክንያት ጭንቅላቱ እንደጠመንጃው ብረት ስለቀዘቀዘ ያገኘውን ሁሉ እያደነ ወደ እልቂቱ መንኰራኩር በመከተት መቀርጠፍና መከተፍ ብቻ ሕይወቱ ሆኗል:: በርካታ የሃገራችንን ወጣቶች በብሔራዊ ውትድርና እያስገደደ ማዝመቱ ሕልውና የሚሆነው መስሎታል:: ያኔ ጥቂቶች ብዙ ሺህ ወጣቶችን ፈጁ ዛሬ ደግሞ ብዙ ሺህ ተገዳጅ እንጋቶች ብዙ ሚሊዮን ሰዎች እንዲጨርሱና እንዲጨረሱ እየተደገሰ መሆኑን ሳስብ አዘንኩ::

በአረፍኩበት ሆቴል አንድ የአዲስ አበባ ደቡብ ቀጠና የደህንነት ባለሥልጣን እያዘወተረ ይዝናናል:: የሚገርመው የሚያጅቡት የመንግሥት ወታደሮች ሳይሆኑ የራሱ ልጆች ናቸው:: ይህ ባለስልጣናቱ ወታደሮቻቸውን እንደማይተማመኑባቸው አረጋገጠልኝ:: በየጊዜው እየመጣ ሲዝናና የሚያወራው ሁሉ ለሕሊናዬ የማይጥመኝ ነበር::

መንጋውን በመስክ ያሰማራ እረኛ ለምልከታ እንዲያመቸው ኮረብታ መርጦ ከነጣቂ ይጠብቃል:: የደርግ ባለሥልጣናት ደግሞ በሕዝቡ መሃል ሆነው ሳይሆን በረጃጅሙ በታነፁ ትላልቅና ውድ ሆቴሎች ተቀምጠው ውስኪ እየተጐነጩና ዳሌ እየደባበሱ ደህንነቱን በአረር እንደሚንከባከቡ ተመለከትሁ::

በተለይ አንድ ቀን በሆቴሉ መዝናኛ ስፍራ ከጓደኛዬ ጋር ተቀምጠን ሳለን አንድ ወጣት ምን እንዳደረገ በውል ባናውቅም በርቀት ፖሊስ ሲደበድበው ተመለከትን:: ልጁ እየተከላከለ «ምን አደረግሁ ጋሼ» እያለ ቢለምነውም ሊተወው ስላልቻለ ከእጁ አፈትልኮ እሮጠ:: ተከተለው:: ልጁ በመኪናዎች መሐል ተሹለከለከ መንገዱን ለማቋረጥ ጥቂት ሲቀረው ፖሊሱ በአውቶማቲክ ተኩስ

ጣለው:: ተዘረረ በአስፋልቱ ላይ የወጣቱ ደም ተንጣለለ ዘገነነኝ፡ መስተንግዶውን ትተን ከቦታው ሄድን:: ይሄ ጠመንጃ በወጣቱ ትውልድ ላይ እስከመቼ እንደሚደገንና እንደሚተኮስ ሳስብ ሕሊናዬ መልስ አጣ:: ኢትዮጵያው ውስጥ ሁሉም ነገር በኃይልና በግዳጅ የሚፈጸመው እስከመቼ ይሆን??? የአመታት ጥያቄ!

ከደርግ ውድቀት በኋላ በዋቢ ሸበሌ የሆቴሉን ሠራተኞች በአማርኛ ሳነጋግራቸው እንደ ተዐምር ነበር ያዩኝ:: ይህ ያልታደለ ትውልድ ከዚህም በላይ መሳቀቅና ውድቀት ደርሶበታል::

ከአዲስ አበባ ተመልሼ በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል አውሮፕላን ሞቃዲሾ ገባሁ:: የነበረው እንዳልነበረ ሆኗል:: የከተማዋ ሕንፃዎች ሙሉ በሙሉና በከፊል ወድመዋል:: ጣራዎች ተሸንቁረዋል፣ ግድግዳዎች ተነድለዋል፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች ተበጣጥሰው ምሰሶዎቻቸው አዘንብለውና ተጋድመው ይታያሉ:: የተቃጠሉ መኪናዎች በየጐዳናው ከስለው (ጠቁረው) ተገትረዋል:: የጢስ ደመና ባሻገር ይታያል:: የመንገዱ ዳርቻ የመቃብር ስፍራ ሆኗል::

ከአየር ሜዳው የተቀበለኝ ጓደኛዬ ከወዲሁ ጥፋቱና መፈራረሱን አይኔም ልቤም እንዲለምደው አሰቃቂውን ገፅታ እያዘዋወረ አሳየኝ:: በከተማው የማውቃቸው አንዳንድ ሰዎች በሕይወት መኖር ለማረጋገጥ ስጠይቀው አብዛኛዎቹ የጐሳው ጦርነት ሰለባ መሆናቸውን አረዳኝ::

ይህ ጦርነት በመጀመሪያ በሶማሊያ መንግሥትና በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ነበር:: የዳሮድ ጐሳ አባላት የዚያድ ባሬን አገዛዝ በመደገፍ ከሌሎች ጐሳዎች ጋር ተዋጉ:: በኋላ ግን የተቃዋሚዎቹ ኃይል እያየለ ወደሞቃዲሾ አካባቢ ሲደርስና ዚያድ ባሬ ሲሸነፍ ጦርነቱ የሁለት አቅጣጫ ባህሪውን ትቶ ባለብዙ ዘርፍ (የእርስ በርስ)





ውጊያ ሆነ:: ዳሮድ ከዳሮድ፣ ሐዊያ ከሐዊያ፣ ኢሳቅ ከኢሳቅ፣ ተዋጉ፣ ተጋደሉ! ደም ተፋሰሱ! አንዱ በአንዱ ላይ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በመፈጸም መዘራረፍና መጨራረስ ሆነ:: በታሪኩ፣ በባሕሉ፣ በኃይማኖቱና በቋንቋው እንደ አንድ ቤተሰብ ይታይ የነበረው ሕዝብ ተቆራቆሰ:: ሰው በዚህ መልክ እራሱን ለሰውነቱ የማያስገዛ የራሱን ዘር አጥፊ አሳዛኝ ፍጡር መሆኑን አለም ሁሉ ለማመን እስኪሳነው ድረስ በሶማሌያ ሕይወት ነጠፈ::

በማግስቱ ሜይ 11/ 1991 ተሚጣ ባለቀች ተስፋ ምናልባት ቤተሰቦቼን ባገኛቸው ብዬ ወደ ቆርዬሌ አመራሁ:: በየመንገዱ ዳር በብዙ መቶ የሚቆጠሩ አስከሬኖች ተፈነጋግለው በማየቴ ዘገነነኝ:: የሰላም ዋጋ ከሁሉ ይልቅ የከበረ መሆኑን የሚገልፅ የደም መሬት ተንጣሏል:: እንባሁ ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ:: የማየው የሀገሩ ምድር ሁሉ ዝርግ መቃብር ሆኗል:: አንድ የተሟላ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በከባድ መሣሪያና በፈንጂ ድምጥማጡ ጠፍቶ የድንጋይ ክምር ሆኗል:: አይኔ ድንጋዩን፣ ስብርባሪ ብረቱንና አመዱን ሲያይ ልቤ ደግሞ ተቆራርጠው ተከረታትፈው ተቃጥለውና ተበጣጥሰው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያንቀላፉ ሕፃናትን አወዳደቅ ተመለከተ:: አይኔ እንባ እያመነጨ ሲያነባና አፌ ሲለጉም ሁለመናዬ ግን ከምድር እስከ ሰማይ ጮኸ:: ይህ ሁኔታ የልጆቼንና የባለቤቴን እጣ ፈንታ ከወዲሁ አረጋገጠልኝ:: ያም ሆኖ ግን ወደ ቤቴ ደርሼ በፍርስራሹ ውስጥ እንኳ የስጋቸውን ቁራሽ ያጥንታቸውን ክስካሽ የደማቸውን ፍሳሽ በእንባ ተሳልሜ ልመለስ የጭንቅ እርምጃዬን ተያያዝኩት:: የቤቴ ግድግዳና ጣራ በጥይት ተደብድቧል:: ወደ ውስጥ ዘለቅሁ:: የፀጥታው ክብደት ሞት በግዝፈት ነግሷል ይለኛል:: ተጣራሁ ባለቤቴ ብቅ አለች:: በአካል

ላውቃት እስኪሳነኝ ተጉሳቁላለች። ልጆቼም እባ… እባ… እያሉ መጡ። ተቃቅፈን ተላቀስን።

በጉሳ ጦርነቱ አደጋ ለረገፉ ሕፃናት፣ አረጋውያን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች የተሰማኝንም እምቅ የሐዘን ስሜት ለማርገብ ያምነኝ አውጥቼ አለቀስኩ። አሁንም፣ አሁንም በድንጋጤና በሐዘን በተደባለቀ ስሜት ተቃቅፈን ተላቀስን። ባለቤቴም ሆነች ልጆቼ በጥይት አልተመቱም። በረሃብ ግን ተደብድበዋል፣ ተጎጠዋል፣ ከሰውነት ተራ ወጥተዋል። እራሴን አረጋግቼ ለግዜው የሚያስፈልጋቸውን አደርጌ ከሦስት ወራት በኋላ በጭነት መኪና በዶሎ በኩል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ አደረግሁ። ቤተሰቦቼ ከሞት በተሻለ ሁኔታ ከሶማሊያ ምድር ድኸው ቢወጡም እየተገፉና እየተጉተቱ ወደ መቃብር የወረዱ፣ በእሳት የጋዩ፣ በአውቶማቲክ መሣሪያዎች፣ በቦምቦችና በከባድ አዳፍኔዎች የረገፉ በርካታ መሰል ወገኖቼን ሳስብ ውስጤ በድንጋጤ በፍርሃትና በሐዘን ተረበሸ። በቀርጫሌ በሕይወቴ የቆመው የሞተውን ቁጥር የሚቀብርበት ጉልበት በማጣቱ አፈሩ ስለሚለሰልስና ኃይል ስለማይፈልግ የኩሬዎችን ግድብ ጃርቻ ወደመቃብር ለፍራንት ለውጡት ተመለከትኩ።

ከዚህ ሁሉ አሰቃቂ ቆይታ በኋላ ከረድኤት ድርጅት ሰራተኞች ጋር ሞቃዲሾን ለመልቀቅ በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል አውሮፕላን ወደ ናይሮቢ ለመመለስ ተጠናቀን አውሮፕላኑ ለማኮብኮብ ሲዘጋጅ ሁለት የሶማሊያ ታጣቂዎች ደርሰው አውቶማቲክ መሣሪያዎቻቸውን ደገኑብን። ፈረንጆቹ በጣም ተጨነቁ። ታጣቂዎቹ ከመሀል እኔን እንድወርድ ጠየቁኝ። አልወርድም አልኩ። ወዲያውም መሸሽ እንደማልችልና ካልወረድኩኝ በአንድነት እንደሚፈጁን ገለጹ። አሻፈረኝ አልኩ። ከሰንት እሣት ያወጣኋትን ነፍስ እንዲሁ ላስረክብ?? የማይሞከር ነገር! ቢጨንቃቸው ፈረንጆቹ ሕዛቡ አታስጨርሰን





ውረድልን» ብለው እያለቀሱ ለመኑኝ። ወረድኩ። ብዙርባን ያዙ አሉኝ። ያዙኝ። [illegible]

ብዙ አሁን ቀኑ ብለሁ ሳትንቀሳቀስ ከአየር ማረፊያው ውጪ በማለት ደግነውብኝ አዘዙኝ። አልንቀሳቀስም አልኩ። በዚህ መሃል አውሮፕላኑ ምድርን ለቆ በረረ። ታጣቂዎቹ በቦርሳዬ በርካታ ገንዘብ ዘርፌ እንደምበር ገምተዋል። ግን አይደለም። የድርጅቱ ሰራተኛ ነኝ ብላቸውም አልተቀበሉኝም። በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የቾግሩ ሁሉ ሜዳ ወደ ሆነው ምሰራች ቀረብኩ። እንደማይተውኝ አረጋገጥኩ። ተስፋቸው ቀጣይም ከሜዳው ውጪ ነው። በዚህ ጊዜ የሞት ጥቂን በልቤ እንዲን የተዘጋጋውን ከነመሣሪያው ተጠመጠምኩበት። ሌላኛው እንዳይመታኝ ጓደኛውን ባለኝ ኃይል እያሽከረከርኩ ወደሱ አዞራለሁ። ጠፍሬ የያዝኩት ጓደኛው ደርሶ እንዳይመታው ይወተውታል። ሌሎች ታጣቂዎች ወደ ሜዳው መሀል እየሮጡ ሲመጡ ይታዩኛል። ተስፋ ቆረጥኩ ደረሱ።

ከመካከላቸው እነ አቶ ሁሴን ሽዶ፣ ጃሀር ዶሌ፣ እና ሌሎች በውል የማላውቃቸው ግን የሚያውቁኝ በመገኘታቸው ፀቡ (አምባጓሮው) በሁለቱ መካከል ሆነ። በመሀል ሌሎች ለወሬ የመጡት እኔን አሸሹኝ። እነዚያ ግን በእኔ ምክንያት ወገን ለይተው በአውሮፕላን ማቢያው የተኩስ ልውውጥ አደረጉ። በተፈጠረው አጋጣሚ ሕይወቴ ከተንጣጠረባት ጥፋት ለጊዜው ብትድንም በሌላ መልክ የሰዎች ሕይወት የሚቀሰፍበት ግጭት በመቀጠሉ ተጨነቅሁ። ለኔ ሲሉ በሌሎች ላይ ቃታ የሚስቡ ወገኖቼን እራሳቸውን ከመጠበቅ በቀር አንዳችም ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል ልውጣ ብል አፍነው አስቀሩኝ። በጣም ደስ ያሰኘኝ ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ ከሁለቱም ወገን የሞተም ሆነ የቆሰለ አልነበረም። ተገረምኩ።

በጠመንጃ ሞት ሲዘራ እልቂት ሲታጨድና ሕይወት ሲጠበቅም አየሁ::

ቢጋጣሚ ከድርጅቱ ብለይም በሰውነቴ ልወጣው የሚገባኝ የቀረኝ አንድ ታላቅ ድርሻ ቢኖር እራሴን ለሰብአዊ አገልግሎት ማቅረብ በመሆኑ ታጣቂዎቹ በፈጠሩት መሰናክል ፓስፖርቴ ግዜው በመተላለፉ እዚያው ሱማሊያ ከሌሎች መሰል ወገኖቼ ጋር በመተባበር በረድኤት ድርጅቶች ስር ለሦስት ወራት በበጐ ፈቃደኝነት ነፃ አገልግሎት ሰጠሁ::

የሰውን ልጅ በምግብና በቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን በሞራል ማገዝ፣ ሕይወቱ የሌሎች ድጋፍ እንዳላት ማረጋገጥ፣ ትልቅ ፍሬያማ ድርጊት መሆኑን ተገነዘብኩ:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ እለት በእለት ይገጥመን የነበረውን ችግር ሳስተውል አንዳች እውነት ውስጠሕሊናዬን ይሰረስረው ነበር::

ሥልጣኔ ለዓለማችን ያበረከታቸው ጠቃሚ ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው በንጽጽር ግን (በአብዛኛው ማለት ይቻላል) አጥፊ ጉት ሰውን ልጅ በሰላምና በፍቅር በመቻቻል የመኖር ሰብአዊ ስሜቱን እየገዘገዘ የሚጥል በእውቀቱ ውስጥ የተደበቀ ድንቁርና መሆኑን፣ በርህራሄው ውስጥ የተደበቀ ጨካኝነት መሆኑን አየሁ:: ሰው ለግሉ፣ ለማሕበራዊ ብሎም ለሀገራዊ ክብሩ ያዘጋጃቸውን መሣሪያዎች የራሱ መደምሰሻና መናጃ ሲያደርግ ተመለከትኩ:: የመሰልጠናችን ግስጋሴ ሁሉ የመጥፋታችን ክምር መስሎ ታየኝ::

በኦገስት 1991 እኔም ቤተሰቤን ተከትዬ ከአሥራ አራት አመታት በኋላ ወላጆቼንና የተወለድኩበትን ነጌሌ ለማየት በቃሁ:: ነጌሌ እንደገባሁ በእውነት ዳግም የተወለድኩ መሰለኝ ተደሰትኩ::





ለሳምንት ያህል ከቤት ሳልወጣ የተራብኩትን የቤተሰቦቼን ናፍቆት ከመከምኩ:: ሁኔታው በዚህ መልክ አልቀፀለም:: ደስታዬ ሀዘን ተቀየጠበት የአለማየሁ ለማ፣ የስዩም ወ/መስቀል የዮናስ ማሞ እና የሌሎችም ጓደኞቼ ወላጆች መምጣቴን ሰምተው ሊጐበኙኝ ወደ ቤታችን መጡ:: በእኔ አንፃር ልጆቻቸውን በማስታወስ ከፍላጐታቸው ውጪ ማልቀስ ተያያዙ አስለቀሱኝ::

የእኔ በመካከላቸው መገኘት በውስጣቸው የተዳፈነውን የሀዘን ስሜት በመቀስቀሱ ተጨነቅሁ:: አብዛኛዎቹ የጓደኞቼ ወላጆች በዕድሜ መግፋትና በድህነት ተጐሣቁለው በማግኘቴ ልገልፀው የማይቻለኝ ትካዜና የመንፈስ መረበሽ አነዋወጠኝ:: ዛሬ የሌሎችን ድጋፍ የሚሹበት ቀውጢ ቀን ሆኗል:: ሁብት ኖሮኝ ችግራቸውን የማቃልል አይደለሁም:: ወይም ከገንዘብ በላይ ልጃቸው ሆኜ ከሁሉም ጋር መኖር አልቻልኩም:: እኔ እራሴ ባለብዙ ቅርንጫፍ ወርካ እየሆንኩ ነው:: ለጓደኞቼ (ልጆቻቸው) ልማዳዊውን የድንጋይ ወይም የእብነበረድ ሐውልት ለማቆም አስከሬናቸው የወደቀበት ስፍራ እንኳ አይታወቅም:: በየጫካው፣ በየዱሩ፣ ነውና የተጣሉት:: ያለኝ የመጨረሻ ዕድል ልጆቻቸውን የተቀሙ፣ በውርደትና በድህነት ማጥ እንዲወድቁ የተገፈተሩ ወላጆችን ይጽናኑበትና ይኮሩበት ዘንድ የበደሏቸውም የሚያፍሩበትና ይቅርታ የሚጠይቁበት የልጆቻቸውን እውነተኛነት የሚመሰክር አንድ ታሪካዊ የመታሰቢያ ሥራ (በሕዝብ ልቦና የሚተከል ሐውልት) መሥራት እንዳለብኝ በውስጤ ወሰንኩ የቀድሞ ጓደኞቼን «ያልታደለ ትውልድ» ትራፊዎች ፍለጋ ተያያዝኩ:: ተገናኘን! «ያንተን የሚመስል! እኔም አለኝ ቁስል » አሉኝ:: እጅ ለእጅ ተያይዘን ከደስታችን በላይ ለምንወዳቸው ቤዛ ብዙኃን ሐውልቱን ማዋቀርና ማነፅ ጀመርን::

## ምዕራፍ ሁለት

## የመከራውን ገፈት ቀማሾች



መምህር ወርቅአለማሁ ንጋቱ (መራር ትዝታ)



መም/ መሰለ ወንድሙ
ትልቅ ባልሆንም...



መም/ ወርቅአገኘሁ ኃ/ጊዮርጊስ
ቆንጆ ሚስትህን ጥለህ...






## መራር ትዝታ

መም/ወርቅ ዓለማሁ ንጋቱ

ስደት፣ እስርና ዱላ እንደ ሀገሬ ልጆች ሁሉ ለኔም ድርሻ ነበርና በተለይ በመጨረሻ ሰዓት የሆነውን፡- ትውስታዬን የጊዜ ደለል ስላልሸፈነው እንዴት እንደነበረ አስታውሳለሁ::

ዕለታዊው የአየር ሁኔታ እራሱ የፖለቲካውን ውጥረት ተከትሎ ይከብዳል:: የዛፍ ቅርንጫፎች እንኳን የነፋስ አቅጣጫን ይዘው ዘንበል... ቀና... ጉንበስ ሲሉ የሚጠቁሙና የተደበቀውን ለመፈለግ እሰሳ የተሰማሩ ይመስላሉ::

በሮችና መስኮቶች በመወርወሪያ ስለከረቸምናቸው ከእኛ ጋር ዝም ነው እጥሮችም እኛው ካልዘለልናቸው «አናስገባም በሩን...» የሚሉ ይመስላሉ:: ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው መራራ ቀንና ሌሊት ቆርጠን:: ያም ሆኖ በተጣበበ እንቅስቃሴ የፓርቲ ጋዜጦች እናነባለን... ኢንፎርሜሽን እንለዋወጣለን... እነማን እንደታሰሩ እነማን እንደተረሸኑ እንማን አገር ጥለው እንደኮበለሉ እንሰማለን... በድርጅቱ ውስጥ ችግር እንዳለም... ዱብ ዕዳ ነው:: ድርጅታዊ ሥራው ግን ቀጥሏል... በሼልተር (መጠለያ) ያሉቱም በውስጥ ችግር ተይዘው በፋሺስቶች እጅ ተዘልዝለው ከመሞት እየሮጡ መውደቅን የመረጡ እንደነ ፈቃዱ ሙላት እየሸሹ በጥይት ተደብድበው መውደቃቸውን እንሰማለን... ከየአቅጣጫው ወደ ጽልመታዊው ወሳኝ ምዕራፍ መቅረባችንን የሚያረጋግጡ ክስተቶች ተበራከቱ:: የሞት ኮቴው ከኋላችን በቅርበት ይሰማል... መቃብሩ ከፊታችን አፉን ከፍቷል... ጣር በግንባራችን ተንጠልጥሏል... የልባችን ቅኝት ግን... ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ... ድል ለኢሕአፓ... ይላል ... የሚገርም መንፈሳዊ ጥንካሬ::





የካቲት 7 ቀን 1970 ዓ.ም በመስከት ቀዳዳ ወደ ውጪ ስመለከት አንድ ጠቋሚ ፖሊሶችንና የታጠቁ የደህንነት ሠራተኞችን አስከትሎ ሲመጣና ቤታችንን ሲጠቁማቸው ተመለከትኩ:: ሳወንድሜ (ሙሉዓለም ጌጋቱ) አሳየሁት እንድንሸሽም ጋበዝኩት... አልፈቀደም:: እኔ ግን በጓሮ አጥር ዘልዬ ወጣሁ ት/ቤት ሄጄ ለታናሽ እህቴ ቤት ውስጥ ቢገኙ ችግር ያስከትሉ የነበሩ ዕቃዎች ምንጋ እንዳሉና የት እንደምታደርስ ነግሬያት ስመለስ 5.30 ሰዓት አካባቢ ከፊቴ ሽጉጥ ተደገነብኝ... ሮጥኩ... ተተኰሰብኝ... አልቆምኩም ማሳደዱ ቀጠለ... እጅ ከመስጠት እየሮጡ መውደቅን መርጫለሁ::

በሩጫ ከግቢ ግቢ ከአጥር ወደ አጥር በመዝለል ሁለት ቀበሌ አካለልኩ የሚገርመው ጥይቱ አጥሩን ሲበታትነው ሲሰነጥረው እኔን ግን አልመታኝም:: በመጨረሻ ተዳክምኩ ብርክ ያዘኝ 6:00 ሰዓት አካባቢ የገባሁበት ግቢ ዙሪያው ተከበበ::

«መሣሪያ ይዟል እንዳያበላሻችሁ» በማለት በስጋት እንደደገኑ የሚደፍር በመጥፋቱ ቆዩ እኔም ትንፋሽ አገኘሁ:: አንድ ወታደር ዘሎ ገብቶ ያዘኝ... ተያዝኩ... ፀጠላቶቼ እጅ ገባሁ::

እጅ የኋሊት ተጠምዝዞ የክላሺንኮቩም ... የሪቮልቫሩም... የማካሮቩም አፈሙዝ ተደግኖብኝ በአጀብ ወደ ምርመራው ማዕከል (አውራጃ ፖሊስ) ተወሰድኩ:::

ወታደር መደቤና ሽንቁ «... ጌታዬ ይኸው ስንት ጥይት አስጨርሶን... ሲተኩስብን ነበረ:: ሽጉጡን የት እንደጣለው እንጃ... ይኸው አምጥተነዋል» ብለው ቋና ቋና እየተነፈሱ የታማኝነቱን ሪፖርት አቀረቡ:: ከምርመራው ክፍል እንደ ተአምር ሊያዩኝ ተንጋግተው ወጡ::






ሁሉም ይናገራሉ... ምን እንደሚሉ በውል አላዳመጠኩም... አንገራጓሊናዬ ግን የመጨረሻ ወደ ሆነው ምዕራፍ ተጉዞ አወዳደቁን ነበኝ... ይዘገንናል... ገፍትረው አስገቡኝ:::

የክፍሉ ሽታ በጣም ይሰነፍጣል:: እነዚህ በንጥቂያ የተመረጠውን የሚበሉ... የተጣራውን የሚጠጡ ... ረብጣ የሚቆጥሩ... የመኢሶንና የደርግ ቡችሎች እንዴት እንደዚህ ክፍሉን ሊያገሙት እንደቻሉ እንጃ... ቀረናኝ:: ... በመካከላቸው ድህ አደጉች ቢኖሩም በረግጠህ ግዛው ሥልጣን... በደም... ከብረዋል::

ይህ ለቅጽበት የተንሸራሸርኩበት ሰፊ የሚመስል ፈጣን ሀሣብ በደህና ቡጢ ተበተነ... ቤቱ ለዘለዓለም በድጋሚ ላየው በማልችል ብልጭታ ተሰወረ... ተደገመ... የቡጢውን ውርጅብኝ ለመሸሽ አቅጣጫ መምረጥ እንኳን አቃተኝ... ሁለመናዬ በጫማ... በዱላም... በጥፊም፣ በጉማሬም እየተደበደበ በመሆኑ ራሴን ስቼ ወደቅሁ::

በወለሉ ላይ የኮቴያቸው ጓጓታ ከሩቅ እንደሆነ ዓይነት ይሰማኝ ጀመር.... ደነዘዝኩ... የሚታየኝ ነገር የለም:: ብቻ አንድ ኃይል ጭንቅላቴን ከመሬቱ ጋር ሲያጣብቀው የሞትኩኝ መሰለኝ::... ፀጥታ...

ከደቂቃዎች በኋላ ስባንን ፀጉሬን ጨምድደው ይዘው በማቅናት ቀዝቃዛ ውሀ እያፈሰሱብኝ ነው:: አየሁ... ገራፊዎቼ እንደተኩላ ወረውኛል::... ዳዊት ያዕቆብ ነው የሚያፈስብኝ... አቶ ታደሰ ቦጋለ «... ልጄ አይዞህ የአብዮት ጠበል ነው ቀና በል እና ጠጣ» ይለኛል... በመቀመጫዬ ወለሉ ላይ ተቀመጥሁ:: በጫማ ጥፊ የተመታው ብልቴ ሀመም ቀስፎ ይዞኛል... በአፌ ደም ይፈሳል... ሻለቃ ከፍያለው «ተፋ!» ይለኛል ተፋሁ... አይቆምም... «ስማ ሽጉጡንና ቦንቡን የት ነው የደበቅኸው??? ... ከእኛ ውስጥስ ማንን ልትገድሉ ነበር... ...



እውነተኛ ታሪክ

በድርጅቱ ውስጥ ድርሻህ ምንድነው??» አጣደፉኝ... ለማንኛ
መልስ ይሰጣል? ... የሞት ሞቴን ኸረ እኔ ምንም አላውቅም አል
... በሳቅ ቤቱን ሞሉት... አቶ ታደሰ በከባድ ጥፊ ወለሉ ላይ ጣ
ጆሮዬ ተደፈነ:: ጉጉ... ከሚል የውስጤ ድምፅ ውጪ አፋች
ሲላወስ... ፊታቸው በቁጣ ሲነድ... አያለሁ እንጂ የሚሉ
አይሰማኝም:: ቀድሞም በሩጫው በጣም ደክሜ ስለነበር ተዝለፍል
ተዘረርሁ::... ዕረፍት... አሁንም በጠበላቸው ቀሰቀሱኝ... አንስተ
ልብሴን አስወልቀው በውስጥ ፓንት (የውስጥ ሱሪ) ብቻ ወንበር ላይ
አስቀመጡኝ::

ሻለቃ ከፍያለው አድገህ የፖሊሱ አዛዥ «ገለል በሉልኝ
እንዲያበላሻችሁ ልገላግለው! ... አታወጣም?!» እያለ በተሸከርካሪ
ሽጉጥ ጥይቶች ሲያጉርስ ሌሎቹ እነ ዘርዓይ «ቆይ
አትግደለው... ይናገራል» እያሉ ይገባበዛሉ... ቁጥራቸው ከ10 በላ
ነው:: እንደዛ ሲገባበዙ ሁኔታቸው ሕፃን የሚያስፈራሩ ይመስላል::
ሻለቃ ከፍያለው ገለል እንዲሉለት ካደረገ በኋላ ወደ እኔ በመጠጋ
«ዘወር በሉልኝ!» ብሎ ደንፍቶ ካገለላቸው በኋላ «አፍህን ክፈት
አለኝ ከፊትኩለት የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ወደ አፌ ከተተ «አትናገርም
አለኝ ለመናገር እንቅስቃሴ ስጀምር መሳው ጥርሴ የረገ
እስኪመስለኝ ሪቮልቨሩን አማስለብኝ...

በመቀጠል ሁለት እጆን የኋሊት ከጠፈሩኝ በኋላ የወገቤ
አቀማመጥ ጭኖቼን ስላጋለጠ በጉማሬው እጀታ (ጉጥ) ክፉኛ
ደበደቡኝ በጣም ጮህኩ... በዚህ ላይ ወ/ሮ ሰለሞን እየተንጠራራ
የእግሮቼን ጣቶች ሲረግጥ እስከ ጭንቅላቴ ይነዝረኝ ጀመር...
ስሰማው የነበረውን ስቃይ ቀመስኩ... ከባድ በደል::

32


እውነተኛ ታሪክ

በልቤ... ነገም ቢሆን መረሽኔ አይቀርም... ምናው እንዲህ
ከምንገላታ በጆሮዬ ሲያፏጭብኝ የነበረው ጥይት ራሴን ብሎ
ቢገላግለኝ... ብዬ ተመኘሁ::

«ወሬ ይላላው» እንዲቀጥል ከፍያለው! ላዊትና ዘርዐይ ወዲያ
ሳይጠግብ አይናገርም... የኢሕአፓን ፖሊፕሊን በደንብ ይዟል» እያሉ
አላገጡ... ተሰቀልኩ... በጠረጴዛና ጠረጴዛ መሀል በአንድ የፍልጥ
እንጨት ተንጠለጠልኩ... እርጌ ካልሲ በአፌ ተጨመረ... መናገር
ስትፈልግ እመልካች ጣትህን አንቀሳቅስ» ብለው እየተፈራረቁ
ወረዱብኝ... በጽሑፍ ልገልፀው የማይቻለኝ ስቃይ... ጉሊናዬ
በእሳትም ውስጥ ሆኖ ይጠይቃል ቢሞት እስኪዘጋ ያስባል... እውነት
እነዚህ ሰዎች አሁን ወደ ቤታቸው ሲሄዱ እንደ ጤነኛ ሰው
ከሚስቶቻቸው... ከልጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር... በፍቅር
መነጋገር... መመገብና አብሮ ሁሉን መጋራት ያውቁ ይሆን??? ...
ወንድሞቻቸውን... እህቶቻቸውን... ልጆቻቸውን ወይም
ሚስቶቻቸውን በፍቅር ቃላት ያነጋግሩ... በፍቅር ዓይን ያዩ... በፍቅር
እጆች ይደባብሱ ይሆን??? .... በፍፁም ሰብአዊ ባህሪያቸው ጥሏቸው
ሄዶ የኢትዮጵያ ትቅደም ዕብዶች... የኢትዮጵያ ትቅደም ጆቦች
ሆነዋል::

የሰው ልጅ በዚህ መልክ ራሱን የሚለውጥ አውሬ ከሆነ
ዓለማችን ወደፊት ያሰጋታል... እኔስ ዛሬውኑ አልቆልኛል አልኩ...
ሰውነቴ በስቃይ ብዛት ቢደክምም አዕምሮዬ ግን በሙሉ ...
እንዲያውም በመጠቀ ኃይልና በፍጥነት ይሰራል:: በጣቴ ምልክት
ሰጠኋቸው... ካልሲው ወጣልኝ... አወረዱኝ... ተነፈስኩ:: «ብላ!
ምንድነው? ተናገር!» አሉኝ መናገር አቃተኝ:: አፌ ብቻ ሳይሆን
ውስጤም ደርቋል... ምራቅ የለም... ከንፈሮቼ በዕብጠት
ተወጣጥረዋል... እንደምንም ወሀ የምትለዋን በምልክት ገለጽኩ::

33





እገጩን ይዘው እንጋጠው ያስመጠን ውህውን ቸለሱብኝ ቶቅ አለኝ... ደም ያዘለው የአከታቱ ልጋግ እንኳን ለእኔም አስጠላኝ... በዚህ ላይ ስለተራቡ በእርግጫና በጉማሬ ካባደቱኝ በኋላ «ለማታ ተዘጋጅ! ሳናንብልህ በፊት ካልተናገርክ በወላጆችህ ፊት ወስደን ኢልማ ሀጠራው!» ብሉ ዳዊት የግብግቡን ምዕራፍ በ7:30 ዘጋልኝ... ያስመሰግነው ይሆን???

ከምርመራው ክፍል ወደ መታጉሪያው ስመሄድ ዳህኩ (ዳዴ አልኩ) በግድ አስነሱኝ «እርግጥ» እያሉ መርገጥ (መቆም) አልሆንልኝም::

ፖሊሶች በድጋፍ ሲወስዱኝ ጧት በሰላም ያደረግን አባቴ ፊቴ እንደዚያ አባብጦ... በደም ተበላሽቼ... በሰዎች ድጋፍ ስወሰድ... በድንጋጤ ደርቆ ሲያየኝ ዓይናችን ተጋጩ:: ስቃዩ ሳይሆን አባቴ አሳዘነኝ:: ዓይኖቹ ተሞሉ ፊቱን አዙሮ ሄደ... ፖሊሶቹ እስር ክፍል እንደወረወሩኝ በሆዴ ተደፍቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ:: በቁርጡ ጥሩ ነው::

ጓዶች ሰውነቴን በቅባት እያሹ አጽናኑኝ:: አበረታቱኝ:: ቀደም ብለው ታስረው ስለነበረ ስለውጪው አስከፊ ሁኔታ ኩርምት ብለው ጠየቁኝ:: በዝርዝር መለስኩላቸው «ብቃ ብልጭ ብላ በአንድ ጊዜ ድርግም ልትል ነው?» በሚል የአስተሳሰብ አድማስ ዙሪያ ተከዝን:: የቀረ ነገር ቢኖር ባለችን ሁሉ ስቃይን ለመቀነስ መደጋገፍ ብቻ!

በዚያች 3 X 4 በሆነች ክፍል የነበረው መተሳሰብ... ልባዊ የሆነ የሀሣብ መለዋወጥ፣ መተዛዘን... ውጪ






ደስ ይላል::... እንዱ ሌላውን እንደራሱ አካል ማየት ክፍል የምታላብሰው መለያ ባህሪ ነው... የኛ ሰፈ ክፍል::

የቀደሙት እስረኞች ማታ ለሚጠብቀኝ 2ኛ ዙር ምርመራ ዝግጅት እንዳደርግ ታክቲኮቻቸውን አዋጡ:: አንዳንድ የማይቻሉ የተዝረዘረኩና የተበሉ ምሥጢሮች በአንድ ከፊሰሱ ሌላው በመካድ እንዳይደበደብ ተሰርስረው በተገናኙ በአራቱም ክፍል የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ይደረጋል:: ግን እየተጠናከረ የመጣው የዱላ ውርጅብኝ ጓዶችን ኢንፎርሜሽን እንዲመግቡ ስላስገደደ ድርጅቱ ቢወድቅም ወጥ ሁሉም ከሚነካካ ሊያውቁ፣ ሊደርሱበት የሚችሉትን ተመረጠ::

ሕመሙ በቆየሁ ቁጥር ተሰማኝ መገላበጥ ተሳነኝ:: ከእንግዲህ ከተደበደብኩ ሰውነቴ እንጉሎ ያዘለውን ጥቁር ደም መፈንዳቴ እንደሆነ ተሰማኝ:: በሆዴ ፀለይኩ::

ማታ ያቺ ጉደኛ ላንድሮቨር ወደ ግቢው ዘለቀች:: ሁሉም ብድግ... ብድግ እያለ ተቀመጠ:: ንጉሤ ወንድሙ «አሁንማ ጠጥተው ነው የሚመጡት ከመሳደብና ሌላ በሥርዓት የሚጠይቁት ነገር የለም... ወይኔ!... የፋሺስቶች እና የባንዳዎች መጫወቻ ሆንን አይደል??» ብሎ በንዴት በቡጢ መታ... እውነትም ሰክረዋል:: «...ዘብ! ውሾቹ እያሉ ጠየቁ በር አስከፍተው ንጉሤን ጠርተው ወሰዱት መለሱት ክፉኛ ተደብድቦ መጣ... ንጉሤ ልበ ሙሉና የስኳዱ ኃላፊ ነበር:: «አባት ሌኒን አንተ የገነባሀት ሩሲያ እኮ ወጋችን» ብሎ አነባ:: ንጉሤ በባህረ ሀሣቡ ጥልቀት የቅርብ





ገራፊዎቼን ሳይሆን የሩቅ ሰንዛሪዎቼን (የሩሲያን ከላሾች፣ ቀልዶቹ ... ነበር ያዘነባቸው::

ዱላው ሀራራ ቢሆንባቸውም ምሽቱን ሌላ ሰው እልጨመረ ... ያም ቢሆን ከአሁን አሁን ይመጣሉ በማለት በመጨነቅና በሀመጠ ... ሳልተኛ ንጋት ላይ ጥቂት እንቀላፋሁ ያውም በቅዠት::

ዓለም ግን የተለመደ ሰላማዊ እዳሩን ይኮመኩማል:: እኛ ... «ሕብረተሰባዊነትን» ያወጀ «ሶሻሊስት» ወታደራዊ መንግሥት ባለበ... አገር... እንኳን ፖለቲካዊ የዴሞክራሲ መብትና ነፃነት ... በተፈጥሮ የማንቀላፋት ዕድል አጥተናል::

በማግሥቱ ረፋዱን ተጠራሁ:: ለባበስኩ ከሁሉም ይልቅ በእሱ ... ክፍሉ ታናሻቸው እኔ ስለነበርኩ የነአውግቸው እርገጤ «አይዞህ ... አትፍሪ!» የሚል የፍርሀቴን ድባብ የሚገልጽ አፅናኝና አበረታች የታላቅነት ድምፅ ተከትሎኝ ወጣሁ:: ፊቴን ወደ ምሥራቅ በመል... መድረሻዬን ተመለከትኩ:: በየቀኑና በየሰዓቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ መሰሎቼ ስቃይ የሚቀበሉበት ክፍል ከመሰብሰቢያ አዳራሹ ... ተገሸሯል:: ያ ቤት እንደበት ኖሮት ቢናገር ከአርባ አመታት በፊት እያቶቻችን በፋሺስቶች የተረገጡበት እና የተገረፉበት ክፍል እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ::

ቤቱን በአምስቱ ዓመት የግዞት ዘመን ጣሊያኖች የሰሩት ነው (በእስረኛ ጉልበት)... ዛሬም የእስረኞች ጉልበት እየተሰበረበት ነው:: የሚያስገርም ታሪካዊ የመመሳሰል አንድነታቸው (የፋሺስቶች) ዘመን ቆጥሮ ተደገመ:: ሁለቱም ፋሺስቶች... እነዚያ ሮማውያን ... እነዚህ ኢትዮጵያውያን::

ልቤ በጭንቀት ተወራጨች:: ዛሬ ከትናንት ይልቅ የሚያረግባቸውን ምልልስ ማድረግ ብችልም... ችግሩ ያለው





በማሰቃየት ከመደሰታቸው ላይ ስለሆነ በእውነቱ የማልቀበለው ጥያቄ ቀደመ::

«ገንዙን የት አገባኸው?! ሽጉጡስ?!» ሊያዙልኝ ይችላሉ ብዬ በገመትኩት መጠን ድምፄን አለስልሼ ተቅለስልሼ እባካችሁ ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም አልኩ:: ዱላው ቀጠለ:: ልብሴን አስወልቀው ወለሉ ላይ በሆዴ አስተኝተኝ ሁለት እጆቼና እግሬን ለአራት ዘርግተው የውጥር ከያዙኝ በኋላ በጉማሬው ቲጥ እየተንጠራሩ መቀመጫዬንና ጀርባዬን በማፈራረቅ ደበደቡኝ:: በጣም አሙሀ ነበር:: እነሱም ይጮሀሉ «ተናገር!... አውጣ!... አንተ የፋሺስት ግልገል! አመን!» አሉኝ:: እናገራለሁ አልኩ:: ዱላው ቆመ:: «ብል ከመጀመሪያ ጀምረህ አውጣ! እንዴት እንደገባህ... ምን እንደሰራህ... ብትደብቅና ሌላው ሰው ቢያጋልጥህ ደግሞ በራስህ ላይ አባዛ እንደጠመመጠምክ ዕወቅ ደምህን ነው የምንጠጣው» አሉኝ::

ዳዊትና ዘርዐይ እውነትም ደም የሚጠጡ አጋንንት መሰለዋል:: አዳነ ዕምባቆም የሚባል ልጅ መሰመለኝ... ዲሞክራሲያ አስነበበኝ... እያልኩ መናገር ስጀምር «የት ቀበሌ ነው??... ቤቱን ታሳየናለህ?» አሉኝ አይ እሱማ ወታደርነት ተቀጥሮ ሄዷል አልኩ... ተናደዱ... ጨሱ... «አሀ... ይቺ የኢሕአፓ ታክቲክ... ማን አባክን ልታታልል ነው??... አንተ የበከትክ አናርኮ...» ከዚያ ወዲያ ዱላቸው ዓይነት የለውም በእጃቸውም... በእግራቸውም... በዱላውም... በሽጉጥ ሰደፉም... ተረባረቡብኝ:: በስስ ብልቴ ላይ ያረፈብኝ ምት ገላገለኝ... ተጠቀለልኩ::

በአፌና በአፍንጫዬ ደም ከመፍሰሱ ሌላ በከፍተኛ ላብ ተጥለቀለቅሁ:: ጐትተው ወደበሩ ጥግ ጣሉኝ በሳንቃው የሚገባውን የውጪ አየር ሳገኝ ከቆይታ በኋላ ተነሳሁ::

አቶ ታደሰ ቢጋለ አስነስቶኝ ለወ/ሮ ተስፋዬ ሮበሌ የማውቀውን ሁሉ ቃሌን እንድሰጥ አዘዘኝ የደበቅሁት ነገር ቢገኝ ግን በገዛ እጄ መቃብሬን መማሴን ገልጾልኝ... እነሱም ሌላውን ጓድ ወደ ማሰቃየት... እኔም ወደ ወታደሩ ኪስ ክፍል... ተፋጠጥን... ወታደር ተስፋዬ በግቡ የፔናልቲ ኤሪያ የመጨረሻውን ቴክኒክ እንደሚያስጨ ሁሉ ጥሩ በሚመስል ትህትና እየተቅለሰለሰ «... አንተ ገና ልጅ ነህ ለምን ትሰቃያለህ ያሳሳቱህ ሌሎች...» አለኝ ሌሎች ጓዶች የሰጡትን ቃል አሳየኝ ፊርማቸውንም «አንተ በእነዚህ ዓይን በጣም ተራ ነህ ስለዚህ ኢህአፓ እንደአለቀላት አውቀህ የበኩልህን እያስታወስክ ንገረኝ» አለ በእርግጥም ለዓላማው ለእውነተኛነቱ ብሰለፍም በድርጅቱ እጅግ በጣም ተራነኝ:: ልደብቅ የማይቻለኝን ነገ ለፀፀት የማይዳርገኝን የተወሰነ ሥራዬንና ግንኙነቴን ስቃዩን ለመቀነስ አመንኩ:: አስመዘገብኩ::

በጭፍጨፋው (በምርመራው) ኢንፎርሜሽን (መረጃ) በብዛት ስላገኙ ካድሬዎች በጥድፊያ ይዋከባሉ... ከቀበሌ ቀበሌ ይበራሉ... ያም... ያም... ያም... ሁሉም እየተነደፈ ነው:: በብዙዎች ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍ ሰሩ::

በወቅቱ በተፈፀመብኝ ኢ-ሰብአዊ ድብደባ ለአንድ ቀን ሽንቴን ከከለከለኝ በኋላ በሁለተኛው ቀን ደም ሸንቻለሁ:: በምርመራ ሰዓት ጭኔ እና ጀርባዬ በመጐዳቱ ለሁለት ዓመታት እየቆሰለ ያዥና ይገለፈፍ ነበር:: የእግሮቼም ጣቶች ለረጅም ጊዜ ደም አዝለው በልዘው ነበር:: ዳኑ:: ኅሊናዬ ግን ዛሬም ደም እንደቋጠረ ህመሙ እንደተሰማው አለ::





## «ትልቅ ባልሆንም ትልቅ ሥራ»


መም/መሰለ ወንድሙ

ኢትዮጵያንና ህዝቧን እንደደራሽ ውሃ ያጥለቀለቃት የለውጥ ማዕበል የእኔንም ሕይወት ጐብኝቶ ነበር:: በተማሪ ንቅናቄ የሙህንለት የመሬትና የመብት ጥያቄ በተሳትፎ ሲተረጐም:: ማስተዋልን፣ መምረጥን፣ መወሰንን እያላመደን መጣ::

«ሕልተከበረለት የድሀው ልጅ መብቱ፣ ምን ልዩነት አለው ሕይወቱና ሞቱ፣» ያልንለትን የደሀ ልጅ፣ «እንዳይሆን ከፊለግህ የልጅ ልጅህ ነባር፣ አንተም ተሰዋና ልጅህ ሞትን ይማር» ብለን በአደባባይ ለመሬቱ ባለቤትነት የሙህንለትን ገበሬ በአካል ለመገናኘት ወደ ከተሜውና ገጠሬው በነጥላዬ ጨዋቃ ዜማ ታጅበን ስንዘምትና አገር በእልልታ ሲቀበለን የነበረውን ወዳጅነት ግለቱ ሳይበርድ በሥራ ላይ ለማዋል በመስክ ስንፈትሸው የተፈጠረው ግጭት እሳት ወለደ:: በአንድ ጐኑ የሚያበስል በሌላ ጐኑ የሚያቃጥል:: ትግል!

ዕድገት በሕብረት የዘመትኩት በሲዳሞ ክ/ሀገር ሀገረማርያም ወረዳ ነበር:: ገበሬውን በማንቃትና በማስተማር 80 የገበሬ ማህበራት አደራጀን:: ገበሬው ከፊውዳሎች እጅ አፈተለከ:: ፊውዳሎች አኩረፉ በገበሬው ላይ ባፈጠጠ ዓይናቸው ዘማቹን ይገረምሙት ስሙንም ያሰምሙት ገቡ «የክርስቲያን ልጆች ከአረመኔ ጋር አብረው የጨዋውን ልጅ ሊያስጨርሱት ነው» እያሉ ወሬ ያናፍሱ ጀመር:: ውጥረት ሰፈነ::

ሻለቃ ታከለ ወልዴ የአውራጃው አስተዳደር እነ አቶ ኤሌማ ኢሌሹን፣ ገመሬ ኤሌማንና ዕውቅ የገበሬ መሪዎችንና ደሀ አርሶ አደሮችን ጐሎልቻ በሚባል ቦታ በአንድ የአልተጠናቀቀ የክሊኒክ ህንፃ





ውስጥ በስብሰባ ላይ እንዳሉ በ27ኛ ሻለቃ ጦር እስከብበ 179 ሰዎች በተወሰነች ሰዓት በመትረየስ አስፈጀ... ጉሉልቻ በደም ታጠበች።

የሀገረማርያም ገበሬ ያለውን መሣሪያ ሰለጠውን ይዞ በጀብዱ ገደል ሸፈተ። የከተማው ቤቶች በእሳት ጋዩ የከተማው የአስፋልት ሬንጅ እንደቅቤ ቀለጠ። ሽብርና ፍጅት ሀገረማርያምን አራዳት።

በዚህ ወቅት ነበር ዘማቹ በየንዑስ ጣቢያው ዘመቻውን ለማቋረጥ አቋም ላይ የደረሰውና እኔም ስለ ትግል የሚያስፈልገኝ የሀሊና ስንቅ ቋጥሬ የወጣሁት። ከዘመቻ መልስ በይርጋዓለም ትም እና ትግል ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈው ጥቂት ተጓዙ። ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የነበረው «የትም/ ከድል በኋላ» ሀሣብ እየገፋ በመምጣቱ በሁለት እኩያ በሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የተከሰተው የመስመር ልዩነት በበለጠ እየጐላ መጣ።

የመማሪያ ክፍል ሰሌዳዎች ጧት የኢሕአፓን አቋም ከነፀባረቁ ረፋዱን ደግሞ የመኢሶንን። ዛሬ የኢሕአፓ ደጋፊ ነገ ደግሞ የመኢሶን ደጋፊ በጠመኔ ይወጋገዛሉ። ቅራኔው ተባ። ሁሉም በየአላማው አደባ። የፕሮፓጋንዳ ውጊያው ወደ ጠመንጃ ዞረ። በዚህ ምዕራፍ ከመንግሥት የወገነው መኢሶን መሲንቆን፣ ቤሪን፣ ጠዷቾን፣ ፌሮን፣ የእስር ማዕከላት በማድረግ ወጣቱን ካጕረ በኋላ አካልን በግርፋት፣ በማቁሰል፣ ቁስልን በወረቀት በማቃጠል፣ በብልት ኮዳ በማንጠልጠል፣ ጥፍር በፒንሳ በመንቀል፣ ምላስ በመቁረጥ አብዛኞዎቹን ካሰቃዩ በኋላ ያለ ፍርድ እነ ከበደ ገ/ሃና ከነወንድምየው፣ አጥዮስ ተ/ማርያምን፣ ታዬ አሣምነውን፣ ቾሩ ወልዴን፣ መኮንንና ሌሎች የዘነጋሁዋቸው ወጣቶችን ረሸኑ።

በመቀጠልም ከተማይቱን በአሰሳ ሲያምሱ በድርጅታዊ ሥራ ላይ እንዳለሁ በመንክር ግርማ የሚመራ አሳሽ ቡድን ያደረገውን ከበባ





በሚገርም ቅልጥፍና ድቅድቁን ጨለማና የቡናውን ተክል በመጣስ በወይማ አቅጣጫ አመለጥኩ። መንክር በቅርቡ ስለሚያውቀኝ የተሰቀለ ጃኬቴን በማግኘቱ ቤተሰቡን በውድቅት አስጨንቆ ዘልፎ ዝቶ በመሄዱ። በከተማዋ ለመቆየትና ለመሥራት ስላስቸገረ በድርጅቱ አማካኝነት ወደ ነጌሌ ተሸኘሁ።

ወደነጌሌ ያደረግሁት ጉዞ በሚያስፈራ የጨለማ ዋሻ ውስጥ የማለፍ ያህል ነበር። ለሰው ልጅ ክብር ያልሰጠ መንግሥት በፍተሻ በንብረት ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ይሄነው አይባልም። ሻንጣ ይዘነጠላል፣ ፍራሽ ይቀደዳል። የማይደረግ ነገር አልነበረም። ነጌሌ ገባሁ።

በ፸አለቃ አፈወርቅ የሚመራ ቡድን ዕቃ ይፈትሻል። አንድ ደብዳቤ አገኙ ከነጌሌ ወደ ይርጋዓለም የተላከ ውዲቴ ገ/ሚካኤል ለአቦዘነች ላሚሶ የላከችው ነበር። ባንዳዎችን ስለመደብደባቸውና ትም/ማቆማቸውን የሚገልጽ። አቦዘነችን በጥፊ አጬሷት እያዋከቡ ወሰዷት። ፍተሻው ጠበቀ። ሻንጣዬ ተበረበረ። ነፃ! ይገፍው የመጣሁት የጓደኛዬ የብረት ሳጥን ግን ቁልፍ ባለመኖሩ ሳጥኑ ወደ ጣቢያ እኔ ወደቤቴ በቀጠሮ ተለያየን።

ጧት ቁልፉ ሲሰበር በውስጡ «ሶሞ ካሜራ፣ መጻሕፍት፣ የስም ቲተር (ማህተም)፣ ደርግን የሚያወግዝ ግጥም ተገኘ። አስተመልኝ አፈወርቅ በሰፊ እጁ በጥፊ ዓይነ ስቤን አጠፋኝ። እርግጫው፣ ቡጢው «የማርያም ጠላት» ሆንኩ ሲበዛብኝ ጣቢያው ወለል ላይ ጭብጥ ብዬ ተኛሁ። ስልክ ተደወለ ወዲያው አቶ ታደሰና ሻለቃ ከፍያለው መጡ የተገኘውን ተመለከቱ ቃሌን እንድሰጥ አዘው ሄዱ።

በ3ኛው ቀን መ/አ ኃይለጊዮርጊስ ደህንነት ቢሮ አደረሰኝ። በ... ታደሰና በረዳታቸው ሰለሞን ከተጠፈጠፍኩ በኋላ ወደ አው... ፖሊስ ተወሰድኩ። ወ/ር ተስፋዬ ሮበሌ (የፖሊስ መርማሪ) በቢ... ካድሬዎች ወዳሉበት ክፍል ይዞኝ ገባ። የመጀመሪያው ዙር ጥያ... በዓይናቸው ጨረር ተፈፀመ። ፊታቸው የሲያል ደጅ መሰለ... እንደገባሁ ሁለት አማራጭ ሰጡኝ «ኢህአፓ ነህ ወይስ አይደለህም... አይደለሁም አልኩ አንዱ በጫማ፣ ሌላው በክርን ሌላኛው በ... አፍንጫዬንና ዓይኔን ክፉኛ መቱኝ። በዚህ ሰዓት የነፍስያዬን ... ጠረጴዛ ስር ገባሁ። ገረማቸው በድል አድራጊነት ተሳሳቁ። ማ... ተሳነኝ። የተጣደፈው ምት አስመለሰኝ። ሁኔታዬ ይብስ ያሰቃኝ... ጀመር አውካኩ «ና ውጣ» አለኝ አሻፈረኝ አልኩ። ፊቴ አበ... የተመታው ዓይኔ ከተፈጥሮአዊ እርግብግቦሹ ውጪ ይንቀጠቀጣል... አንዱ ካድሬ እጄን ይዞ አወጣኝና «አንተ ቀጫጫ በኋላ በግድ... ትናገራለህ አሁን ሂድ ውጣ» ብሎ ደጅ ላለው ፖሊስ አስረከበኝ።

በታሰርኩኝ በ8ኛውና በ15ኛው ቀን በተደረገብኝ ተደጋጋሚ የእግልት ምርመራ። እንዳልክድ እጅ ከፍንጅ ተይዣለሁ እንዳላምን ለጉዳዩ ባለቤት ከሆንኩኝ የሚያስጠፋኝ በመሆኑ ሲበተን ለቀቁ ያመጣሁት መሆኑን አምኜ ቃሌን ሰጠሁ።

በ22ኛው ቀን አውራጃ አስተዳደር ቀረብኩ ቢሮው በቀበሌ ሊቃነመናብርት፣ በገበሬ ተመራጮች፣ በካድሬዎችና በሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ተሞልቷል። ፊት ለፊት የብርጌዱ ጥብቅ አዛዥ ኰሎኔል ረጋሳ ጅማ ጢማቸውን ገምደው በግርማ ሞገስ ተቀያ'ጠዋል ደነገጥኩ። ጉባዔው በመሟላቱ ሪፖርቱ በጽሕፈት ተጠናክሮ ተነበበ። የፍርድ ሀሣብ መስጠት ተጀመረ። እኔ የማላውቀው የገበሬ ተመራጭ « ይህንን አውቆ የሠራ አይመስለኝ ቢ.ያውቅ ኖሮ የሚያስገድለውን ነገር በሣጥን ይዞ አይመጣም ነበር






እሳትና መንግሥት ልጅ ሲያጠፋ ይመክራል፣ በኋላም ይቀጣል ... ለዚህ በቁንጥጫ ይታለፍ» አለ ሌላው «የመደብ ጀርባው ተጠንቶ ታውቆ በእስር ይቀጣ» ብሎ አስተያየት ሰነዘረ። ሌሎችም ሀሣቦች ተሰንዝረው በመሀኒ እንድቆይ ወሰኑ።

በዚህ አጋጣሚ በፍጹም ያልታሰበ ነገር ተከሰተ ወላጅ እናቴ ዘቦቹን እንዴት እንዳለፈች ሳይታወቅ ሰተት ብላ ጉባዔው መሀል ነጠላዋን መሬት ላይ ዘርግታና ተደፍታ «ጌታዬ ድሀ ነኝ፣ በድህነት ... ቆርጥሜ ያሳደግሁት ልጄ ነው። ማሩልኝ» ብላ እግራቸው ስር ወድቃ በዕምባ ለመነች።

ኮሎኔሉ «ብይ አዳምጥሻለሁ ነጠላሽን አንሺ አንቺም ታነሺ» ብለው አቅንተዋት «ምንድነው ችግርሽ?» አሏት «ጌታዬ ጠግቦ በልቶ አያውቅም የደሀ ልጄን ማሩልኝ» ብላ ተማፀነች። ኮሎኔሉ ወደኔ ዞረው «ስማ አንተ ይሄ አብዮት አንተን ምን በደለህ??» አሉኝ አቀረቀርኩ «ልጅሽ እንደድህነቱ አይደለም። ነገም በእጃችን ይገባል አሁን ለአንቺ ስል ውሳኔውን ሽሬያለሁ ይዘሺው ሂጂ በቃ!! እሱ ግን ነገ ይሞታል» አሉ። ካድሬው ዘርዐይ በአዛገፉ ቅር ተሰኝቶ «ጌታዬ ግንም ነጠላዋን ባነጠፈች ነፍስ ገዳይ ይለቀቃል እንዴ??» በማለት ያወለቀውን ባርኔጣ በትከሻው ጥብጣብ ከተተ። ኮሎኔሉ በሚፋጅ አይን ገርምመውት ለወህኒ የተጻፈውን ዋራንት በጫጭቀው ወደ ቅርጫት ጣሉት። ማመንም አልቻልኩም እናቴ እልልታዋን አቀለጠች... ከግቢው ተሰወርን።

በ1970 ዓ.ም ድርጅታችን ሲመታ የነበረኝ ተሳትፎ በመጋለጡ አፈላግ ነበር። በየካቲት ወር የማላስታውሰው ቀን ተሰውሬ ከቆየሁበት መጥቼ እቤት አድሬ ሌሊት ልወጣ ስል ቤታችን





ተከሏል::የድርጅቱን ምሥጢር አሳልፌ እስከምሰጥ ያለውን የአካል ስቃይና የመጨረሻውን ፍርድ ሳስብ ራሴን ማጥፋት ተመኘሁ::

አንድ ወታደር በሩን በርግዶ ገባና ደገነብኝ:: ቢተለበሽ ተርበተበቱ እዚያው የሚገድለኝ መሰለኝ:: ታጅቤ ወጣሁ:: ደህንነት ቢሮ እንደደረስን «ኦ! ተፈላጊው ወንበዴ ከየት ተያዘ?» በማለት አቶ ታደሰ አላገጠ::

ወደ ተጨናነቀው የእስር ክፍል ተወሰድኩ:: የክፍሉ ጠረን እንደለው ማደሪያ አይደለም:: ያልተለመደ ጠረን ይገፋተራል:: በድብደባ የቆሰሉ ወጣቶች በሆዳቸው ተኝተዋል:: የበረቱት ኩርምት ብለው ተቆምጠዋል፤ አብሬያቸው ዋልኩ አደርኩ:: በማግሥቱ ለምርመራ ተጠራሁ::

በአንድ ክፍል አስገብተውኝ በሚቀጥለው ክፍል ሌላ ተመርማሪ ሲሰቃይ እንዳዳምጥ አደረጉኝ:: በስነልቡናዊው ጦርነት ልቤ ራደ ተጨነቅሁ ጠርተው አስገቡኝ በወለሉ ላይ ራሱን የሳተ ወጣት ተዘርሯል አካባቢው በትውከት ተበላሽቷል:: መርማሪው «ይሄንን አናርኪስት አታውቀውም??» አለኝ ባውቀውም አላውቀውም አልኩ «እንድታውቀው ይደረጋል» ብሎ እጅና እግሬን በካቴና አስሮ ከጥፊ ጋር እንድቀመጥ አዝዞኝ ከክፍሉ ወጣ:: ወጣቱን አሻግሬ አየሁት ዘሬሁን ሚዲ ነበር:: ጭንቅላቴ ውስጥ አንዳች ነገር አቃጨለ:: ወዲያው መጡ:: ካንጠለጠሉኝ በኋላ ከትውከቱ ላይ ጥቅሉን ካልሲ አንስተው በአፌ ከተቱ «መናገር ስትፈልግ በእጅህ ምልክት ስጥ» አሉኝና የዱላው ውርጅብኝ ቀጠለ የሠራ አካላቴን አንዳች የሚቆጠቁጥ ንዝረት አኮማተረኝ:: ተጨነቅሁ ነፍስ ሲመጣብኝ እጄን አንቀሳቀስኩ አወጡልኝ «እሺ የምትናገረው አለ?» አሉኝ እረ ምን ልናገር? አልኩ «እናትህ አፈር የበላች ኢሕአፓ በእስኳድነት





የመለመለህ ማነው? ቦንቡንስ ከየት ነው የገዛችሁት?» አሉኝ እባካችሁ እኔም ምንም አላውቅም አልኩ:: ካልሲውን መልሰው ጨመሩብኝ::

የጠጣሁት ሻይ ልቤ ላይ ተንቀዋለለ እንደተንጠለጠልኩ ለበቀኝ ግፊቱ በአፍንጫዬ መጣ ጭንቅላቴ ተቃጠለ ራሴን ሳትኩ:: ስነቃ በተነቃነቅሁ ቁጥር በሚጠብቀው ካቴና ውጥረት እጄና እግሬ አብጧል:: ግንባሬ ቆስሏል ወላልቂያለሁ «እይዞህ ሳይጠይቁህ ታወራለህ በሰፊው እንጨዋወታለን» ብለው ጣቢያ ወስደው ጓዶቼ መሀል ወረወሩኝ::

በ3ኛው ቀን በድብደባ የቆሰለ ገላዬን በድጋሚ ካደሙኝ በኋላ ከታምራት ከበደ ጋር አገናኙኝ:: ታምራት በዱላው ክፉኛ ተጐድቷል «ገረው» አሉት «መሌ ለወታደራዊ ክንፍ እንደመለመልኩህ ነግሬያቸዋለሁ አትደብቅ» ብሎኝ አቀረቀረ:: ወዲያው በርብርብ እየረጋገጡ አስወጡት:: ለብልሀታቸው ይህንን ቃል እንዲናገር ያስገደዱት ስለመሰለኝ አሁንም ዝግ ሆንኩ:: በድጋሚ አንጠልጥለው ጠበጡኝ:: በከፍተኛ ስቃይ ጮህኩ ቆዳዬ ሳይሆን ልቤ የሚተፈተፍ መሰለኝ ደከምኩ:: እዛው እያለሁ በኃይሉ ተስፋዬ ተደብቀው የነበሩ ዘጠኝ ቦምቦች አውጥቶ በመምጣቱ ትኩረታቸውን በመሳቡ አረፍኩ::

ትልቅ ባልሆንም ትልቅ ሥራ ለመሥራት ምኞት ነበረኝ በዚህም የድርጅቱ ሕይወት ሕይወቴ መሆኑን መንፈሴ ቢያምንም በወቅቱ ድብደባና ስቃይ አካሌ ቢደክምም አዕምሮዬ ግን ጓዙን ጠቅሎ ወደ ምርኮ ካምፕ አልገባ ብሎ በተደጋጋሚ ተወገርኩ ምስጢር ላለማውጣት ያለው ፍላጐት ከአካል ጥንካሬ ጋር ባለመመጣጠኑ ሀሳብና ተግባር ተለያዩ::

በጓኛ ዙር ግርፋት ፍዳዬን ካየሁ በኋላ ታምራት በከድ ስሚ «ሌደን በሆሪዞንታል ኮንታክት (በጉናዊ ግንኙነት) የተሰጠህን ዕቃ ስጣቸው» አለኝ የቱን ዕቃ አልኩት «ብአበበች በኩል እንድታስቀምጣ የተሰጠህን ማቴሪያል» ብሎ በንዴት ግድግዳውን በቡጢ መታ ታምራት በፀፀት እየተቃጠለ እንደሆነ ተረዳሁ:: ዕቃውን ላስረክባ ተስማማሁ:: ማታ ተኝቼ ውስጠ ባዶነት ተሰማኝ በምሬትና በሆደ ባሻነት ስሜት አለቀስኩ::

ጧት ከአበበች ካሣ ጋር አገናኙን:: ከፋኛ ተደብድባለች ዓይኗ በደም ቀልቷል:: ታላቅ መንፈሳዊ ጥንካሬ ግን በፊቷ አለ «አንቺ በይ እስቲ በቋንቋችሁ አነጋግሪው» አላት አቢቲ ኮስተር ብላ ካየችኝ በኋላ «መሌ የድርጅታችን መዋቅር ፈራርሷል:: የተጋለጠውን አትደብቅ:: አልቻልንም ፈሽፋሽ የንዑስ ከበርቴ ባሕሪያችን አይሎብን ለከበረ መስዋዕትነት ያልበቃን ከንቱዎች ሆነናል» አለችኝ ፍርጥም ብላ:: በዚህ ጊዜ ዳዊት «ዝም በይ አንቺ ሸርሙጣ የታሪክ አተላ ማን አባሽ ላይ ነው የምትዝቺው!» ብሎ በጥፊ አቃጠላት:: ተንገዳግዳ ቆመች በሳግ ባታለቅስም ዕምባዋ ግን በእልህ በፊቷ ይወርድ ነበር ጥንካሬዋ ገረመኝ::

የደበቅሁትን ዕቃ ጥይቶች፣ አውቶማቲክ ሳንጃ፣ ፓምፍሌቶች አስረከብኩ:: በቂ ስላልመሰላቸው እነ አቶ ታደሰ ቤታችንን እመሰት በመጨረሻ እያዳፉ ሲያስወጡኝ ዘርዐይ ብሩክ «ስማ አንተ ፀረ-ሕዝብ ደግመህ የማትመለስባትን ቤት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበት» አለኝ:: ለቤተሰቦቼ ሞቴን ማረጋገጡ ነበር:: የቶርቹና የምርመራው ወንፊት ሁላችንንም እያጣራ በወህኒ አከማቸን:: ከውስጣችን ሃያ አምስቱ ሚያዝያ 3/70 ዓ.ም ተረሸኑ::





ሞት ረግጦኝ ሳይሆን ተራምዶኝ አለፈ:: ከዚያም ወዲህ በዳግማዊ ኢሕአፓነት ተጠቁሜ በእሱት ተቃጥያለሁ የተሰመደውን ስቃይ ተቀብያለሁ በዚህ ምክንያት ዛሬም ተጠራጣሪነትን በውስጤ አምቄ ኑሮን በብቸኝነት የምመራ መከረኛ ፈጡር ሆኛለሁ::

## «ቆንጆ ሚስትህን ጥለህ?»

መም/ወርቃገኘሁ ኃ/ጊዮርጊስ

ሚያዝያ ወር 70 ዓ/ም በጣም አስፈሪ ጊዜ ነበር:: በዚያ ወቅት ተማሪ፣ በተለይም መምህር ሆኖ መገኘት እንደ ዋነኛ የመንግሥት ተቃዋሚነት (ፀረ-አብዮተኛ) መለያ ሆኖ ይታይ ስለነበረ በሹማምንቶችና በቡችሎቻቸው ዓይን በየዕለቱ መገርመም ተላምደናል:: ከሥራ ቦታ ወደ ቤቴ በማምራት ላይ እያለሁ አንድ የማውቀው የአብዮት ጥበቃ ጓድ መሣሪያውን አንግቶ ተፍ! ተፍ! ሲል አነጋገርኩት::

«...አባክህ እነዚህ የአናርኪስት ወላጆች ሕግ ተላልፈው በየጓዳው ልቅሶ እየተቀመጡ ስለሆነ ሌሎች ጓዶችን ጨምሬ በተጠናከረ ሁኔታ እንድንከላከል በሊቀመንበሩ ታዝዤ መሄዴ ነው» አለኝ::

ጭንቅ ነበር:: በዚያ ወቅት ወላጆች ለሞቱ ልጆቻቸው ማልቀስ አይፈቀድላቸውም ነበር:: በዚህ ምክንያት ሃዘናቸውን ለመወጣት የማይፈጥሩት ምክንያት አልነበረም:: የሟቿ የግርምት አለም አባት የ፲አለቃ ደገፉ ይህንኑ አፋኝ እገዳ ለመወጣት የተጠቀሙበት ዘዴ ከሁሉ ለየት ያለ ነበር:: የቤታቸው ዙሪያ በአብዮት ጠባቂዎች የተከበበ ስለነበር ሰዎቹን ለማዝናጋት ሬዲዮናቸውን ከፍተው በመስኮት ላይ ያኖሩታል:: ሬዲዮኑ መፈክሩንና ዘፈኑን እየቀየጠ ሲያወርደው ታጣቂዎቹ «ይሄ አባት ጦር እንኳን ሊያለቅስ እንዲያውም ዘፈን ከፍቷል::» በማለት ጥለው ገለል ስላሉላቸው በብልኃት እርማቸውን እንዳወጡ አንዱ ጓደኛዬ አጫውቶኛል::

አረመኔዎቹ ሀያ አምስቱን ወጣቶች ፈጅተው በርካታ አዛውንት ወላጆችን «ይበቀሉን ይሆናል» ብለው በመፍራት በእስር ቤት





ከማጉራቸው ሌላ ያም በቂ አይደለም በማለት በየትም/ቤቱና በየድርጅቱ «የጽዳት ዘመቻ» በማለት ከድርጅቱ (ኢሕአፓ) ጋር የሩቅ ዝምድና ያላቸውን ሁሉ ያግበሰብሱ ጀመር:: በዚህ ዘመቻ እኔም ታሰርኩ::

በተቋቋመው አዕጂ የምርመራ ቡድን ውስጥ አቶ ዳዊት ያዕቆብ አለበት ይህ ግለሰብ ከዚህ ቀደም «ሰፊው ሕዝብ» የሚል ቁጥር 48 ከዘመቻ መኮብለልን የሚቃወም አቋምን የሚያብራራ ሃሣብ ያለበት ጽሑፍ የመኢሶን ጋዜጣ ቢሻር ሊበን በሚባል ወጣት በኩል ልኮ ሊመለምለኝ ያደረገው ሙከራ በነበረኝ ተቃራኒ አቋም ሊሳካለት ባለመቻሉ ለበቀል በግላጭ አገኘኝ::

እንደማናቸውም በፓርቲው ዙሪያ እንደተሰባሰቡ አባላቱና ደጋፊዎቹ ንድፈ ሀሣባዊ ጥናት (ዲያሌክቲካል ማቴሪያሊዝም) ና ዴሞክራሲያን እያነበብሁ የራሴን አነስተኛ ድጋፍ ከምሰጥ በስተቀር ድርጅቱ ፈርሶ ከላይ እስከታች በተጋለጠው መዋቅር ውስጥ በምንም እንደሌለሁ (እንዳልተገኘሁ) እያወቀ «ትልቁ ኢሕአፓ ነው» በማለት እግንና አቀረበኝ:: ለመከራ ቀረብኩ::

እሬ በአሮጌ ጨርቅ ተጠቅጥቆ በጠረጴዛ ላይ ተሰቅዬ ያለ ርህራሄ ተገረፍኩ:: እግሬ ነፈረ:: በማግስቱም ደገሙኝ:: ጭካኔያቸው ወሰን አጣ::

የጠገበ ድመት ከነሕይወቷ ያገኛትን አይጥ ከመብላቱ በፊት እያስቃየ እንደሚጫወትባት በማን አለብኝነት ስሜት በአካሌና በሞራሌ ላይ ተጫወቱብኝ:: ወደ እስር ክፍሌ ስመለስ ጓዶቼ የእኔን ሁኔታ በማየት ተደናገጡ:: እህል መብላት አቃታቸው ተጨነቁ::

በመቀጠል መም/ ፋንታ ክፉኛ ተደብድቦ በደም ተበክሎ መጣ:: ሟት ለሽንት መውጣት ባለመቻሉ በሦስት ሰዎች በሸክም ሲሄድ ያዩ

ቤተሰቦቹ አካባቢውን በጩኸት እናወጡት:: ካመጡት ቆርስ ጋ ተባረሩ::

ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መም/ ወልደዮሐንስ ፍሬንጂ፣ መም/ መኮንን ሀሲሶ፣ መም/ ፍቃዱ ደስታ ተመሣሣይ ቅርጻ ተፈፀመባቸው:: ለሦስተኛ ዙር ግርፋት ቀርቤም የግራ እጀ አመልካች ጣት ጥፍር ተገንጥሎ እስኪወድቅ ደበደቡኝ በተጨማሪም በአካባቢው ኳስ ሲጫወቱ የነበሩ ታዳጊዎችን ሰብስበው እምጥተው እጃቸው እስኪደክም በጥፊ እንዲመቱኝ አስገደዱ:: በተማሪዎቼ ተጠፈጠፍኩ::

የአራተኛው ዙር ምርመራ «ሐወንበዴው ዋቆ ጉቴ ጋር ግንኙነት አለህ» በሚል ነበር:: ከዱላው ውርጅብኝ ሌላ እንዲ ሲጠይቀኝ ሌላው ይሰድበኛል:: አንደኛው ሲያባብለኝ ሌላው «ይገዷል በመኪና ይጐተት» እያለ ይደነፋል:: በዚህ መሀል የሴቶች ድርጅት ሊ/መንበር ጌጤ አምበርብር «ሰማ ወንድሜ ሆይ! አንተ ይቺን የመሰለች ቆንጆ ሚስትህን ጥለህ ከምትሞት ለምን ተናዝዘህ ይቅርታ አትጠይቅም??» አለችኝ ምኑን እንደምናዘዝ መልሼ ጠየቅኳት:: ቶርቹ ቀፀለ:: ራሴን ሳትሁ በዚህ ድብደባ ዛሬ በአንድ ሚ/ር መ/ቤት አብሮኝ የሚሰራ ሰው የያኔው የወጣት ድርጅት ተወካይ ቶሞ ገርፎኛል::

ይህ ሁሉ ሲሆን መከራ እንጂ ሞት እጄን ወደ እኔ አልዘረጋም ነበር:: ከሕሊናዬ የማይጠፋው ግን በዳግማዊ ኢሕአፓ የተረሸኑ ወጣቶች በመጨረሻዋ ዕለት (ማታ እና ሌሊት) እንዴት እንዳመጧቸውና ንጋት ላይም ምን እንደፈፀሙባቸው በዓይኔ ስለተመለከትኩ ከፊል ሰውነቴ አብሯቸው ወደ መቃብር ወርዷል:: (ዝርዝሩን በሰማዕታት ገጽ ይመልከቱ)





ባለቤቴ ማመልከቻዋን እየያዘች በየባለስልጣናቱ ቢሮ ደጅ በመጥናቷ በአቶ ጕዳና ቱኒ ትዕዛዝ እንድፈታ በመሆኑ ከፍያለውና ታሰደ አበዱ ለ5ኛ ጊዜ እንዳልሞት እንዳልሸር አድርገው ቀጠቀጡኝ:: ራሴንም በሽጉጥ ሰደፍ ፈነከቱኝ:: ጆሮዬም ተጐዳ በድብደባው ምክንያት እስከ አሁን አንድ እግሬ በሽተኛ ነው::

በመጨረሻም ጥቅምት 15/71 ዓ.ም ዘርአይ ብሩክ ሶሪ እኔና ሙሉ በቀለን በዋዝ መኪና መጥቶ ወሰደን:: ሻ/ባሻ ጌታሁን አበዱ በሕዝብ ፊት አቅርቦን «የአብዮቱን መሀሪነት» ከሰበከ በኋላ ለህያ እምስቱ ሞት የህዝብ ማጽናኛ (ማካካሻ) ሆነን ከኢዲዩና ከኢሕአፓ ጀሌነት እንድንነፃ አስጠንቅቆ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ለቀቁን::

ዛሬ በሕይወት ኖሬ የአራት ልጆች አባት ብሆንም ባለሁበት የሥራ መስክ ለትምህርትና ለተለያዩ የውስጥ ዕድገቶች በመወዳደር ለዓመታት ያደረግሁዋቸው ጥረቶች ሁሉ «ፀረ-አብዮተኛ የነበረ» በሚል ሰበብ ተቀብሬ እንደኖርኩ ባሰብኩ ቁጥር «ቀይ ሽብር» በ70 ዓ.ም ቢያቆምም ሰዋራው «ቀይ ሽብር» በ83 ዓ.ም የቆመ ይመስለኛል::

## ምዕራፍ ሦስት

### አሻራው በቤተሰብ ዙሪያ



ወ/ሮ አበበች ተረፈ



ወ/ሮ ስንቅነሽ አስፋው



ወ/ሮ አስካለ መኩሪያ



፲አለቃ ካሡኝ ዘለቀ



ወ/ሮ ስንቅነሽ ደስታ



ባ/ባሻ ክፈለው ገዳ





## «የሕዝብ ልጅ ነኝ»

**ወ/ሮ አበበች ተረፈ**

በሀገራችን ዳር እስከ ዳር ይሳቡ የነበሩ ቃታዎች ዒላማቸው ምንም በማያውቁ ንፁሐን ላይና በወላጆችም ላይ ነበር:: በጊዜው ልጃቸው በኢሕአፓ አባልነት ወደ ተገደለባቸው እናት ወ/ሮ አበበች ተረፈ ቤት (ቀበሌ 04) አመራሁ::

ከሰላምታ በኋላ ከዓመታት በፊት ስለተፈጸመው ሁኔታ ማውጋት ጀመርን እንገፈገፋቸው:: «... ልጅ እንዲህ ከሰውነት ተራ የወጣሁት... በሽተኛ ሆኜ የቀረሁት ከልጅ ሞት በኋላ ነው:: ያንን ዘመን ያንን ጊዜ ማሰብ አልፈልግም:: እሸሸዋለሁ... በጣም ሸሸዋለሁ ነገሩ ግን ይከተለኛል:: አልተወኝም እስቲ አሁን ለምን አነሳህብኝ?» ብለው ጠየቁኝ... ከገለፃዬ በኋላ ተግባባን ፈቃደኛ ሆኑ::

በረጅሙ ተነፈሱ.... አሰቡ.... «መቼም መሰለን ታውቃለህ ልጅ ጉበዝ ... ልባም ነበር:: በእጃቸው ቢወድቅም ደፋር ነበር:: ይሄውልህ እሱ በልጅ እንደበቱ ያለኝን ነገር እኔን ለጉድ ጎለቶ እያሳየኝ ነው:: «... እቡ! አንቺ እኮ ብትወልጂኝም... ለፍተሽ ብታሳድጊኝም... ብታስተምሪኝም ... አንቺን ብቻ ልጦር፣ ዘመዶቼን ብቻ ልጠቅም ሳይሆን የተማርኩት ለሀገርና ለወገን ነው:: እኔ እኮ ከእንግዲህ የሕዝቡ ልጅ ነኝ» አለኝ::: ስለ ኤርትራም ውጊያ ሲናገር:-

«... እቡ! አይምሰልሽ ደርግ የሚያወራው ሁሉ ሀሰት ነው እነሱ አገዛዙኝ ጭቆናውን በመጥላት እንጂ ሌላ አይደለም የኤርትራን ጉዳይ መድፍና መትረየስ ሳይሆን እርሳስና ደብተር ያቆመዋል» ብሎ አስረዳኝ እውነትም... ብለው በመገረም ትውስታቸውን በትካዜ ካጀቡ በኋላ

«... ወይኔ ልጄ አብሬው አበድኩ... ድምፁን ተከትዬ ባዘንኩ... አልሆንልኝም:: መሬቱን ቧጠጥኩ... ለስንቱ ታቦት ተሳልኩ... በተጋዘበት ሁሉ በሰው አገር ተሰደድኩ:: በመጨረሻ ቀመኝ... ልጄን... መስለ እኮ እንደሚሞት ያውቅ ነበር:: አንድ ጊዜ ሰለ እየፈራ በየጊዜው ስለምወተውተው «እማዬ ዓላማ እኮ ነው! ጥሞት እንኳ እንዳትፀፀቺ የኛ ደም ዛሬ ወንጀል እንደፈፀምን በከንቱ ቢፈሰው ነገ ማርና ወተት ሆኖ የፈሲጋል...» አለኝ:: «ዶቺ እንደበት ተዘጋጁ» ብለው አለቀሱ:: ስሜቱን መቆጣጠር አቃተኝ...

«... ወይ ልጄ! ... መስዬ አረቄ ቀቅዬ ጠላ ጠምቄ ያሳደግሁት የደሀ ልጅ እንደ ውሻ ሜዳ ላይ ተጣለ...» ሀዘኑ ረታቸው እነሱ:: ውይይቱን እንድንቀጽል አጽናንቼ ታሪኩ ተደፍኖ መቅረት እንደሌለበት አሳምኜ ተስተካከሉ::

«ልጄ አንድ ዕለት ምን ሆነ መስለህ ምግብ ይገፍለት ሄጄ ዓይኑን ለማየት ስስቼ... ገፁን ለማየት ፈርቼ... አጉንብሼ ዕንባዬ እየወረደ ቀለቡን ሳቀብለው ፖሊሱ «ምን ያለቅሳሉ አገር ሲሸጥ እኮ ነው የታሰረው» አለኝ:: እንዲው ፍርሀት አልፈጠረበትም «ቢማ ቢገባህ የምንታገለው ለህዝብ ነው፣ ለአገር ነው ብታስተውል ለአንተም ነው:: ሆዳም!» ብሎ ተናገረው ፖሊሱም ተቆጣ... ተወራጨ... እኔን አንቱ ያለኝ «አንቺ» ብሎ በአፈ-ሙዝ እየገፋ አስወጣኝ... እሱንም ወደ በረቱ... ወይ ልጄን እንዲህ ሲቀር ለሚቀረው ለፍሬ ሳይበቃ... እንደወጣ ቀረ... ለአገር ተርፋለሁ ሲል... ለሕዝብ እሆናለሁ ሲል... አገርና ሕዝብ የልቡን ሳያውቅለት... በጥይት ተቃጠለ:: መስዬ ልጄ... እኔ እኮ ደም ማልቀስ ነው የቀረኝ እምባዬ እንደሆን አልቋል...





... አንዱ ዲላ... አንዱ ክብረ-መንግሥት... አንዱ ቦረና ዋና ኢሕአፓ ነው ብለው እንዳገላቱት ... እንዳሰቃዩት... አንድ ቀን እንኳን ለቡ ረግቶ ቀዝቃዛ ውሀ ሳይጠጣ አውጥተው ደፉት:: ... ነሐሴ 11 ቀን የቡሄ ዳቦ ይገፍለት ልሄድ ደፋ ደፋ ስል ውዬ ... ሌሊቱን ለ12 አጥቢያ ገደሉት:: አለቀሱ... «ከዚያማ ምን እልሀለሁ ይሄ ቤት ዙሪያው ተከበበ ሦስት ቀን ሙሉ ሰው እንዳይገባ ሰው እንዳይወጣ... እንዳናለቅስ:: የፈሰሰ ዕምባ ወደ ዓይን ተመልሶ ይግባ ብሎ ማዘዝ ነው የቀራቸው:: ሰው ሁሉ ሸሸን... ጐረቤቱ አብረን እንዳልበላን ... አብረን እንዳልጠጣን ገሸሽ አደረገን:: እሣት እንኳን ከቤታችን አይጫርም ... የኢሕአፓ ቤተሰብ ተብለን... በእሣት ይጋባ ይመስል ... እኛ ምን ያልሆነው ነገር አለ... ምን ያልተባልነው አለ... ለማንም አረመኔ መወዳጃና መሿሿሚያ ሆንን... ይሄው አለፈ::

በጣም የሚገርምህ ትንሹ ይሄንን መሳቀቅ አይቶ ያለዕድሜው ተብከንክኖ «... እማዬ እኔ ወታደርንት እቀጠራለሁ:: እኔም መሞቴ ስለማይቀር አንቺም ታፍነሽ ከምትጨነቂ ወታደር ሆኜ ከሞትኩ እታልቅሺ ብሎ የሚከለክልሽ ስለሌለ ከዘመዶችሽ ጋር ሆነሽ ታለቅሽለሽ...» አለኝ:: የሚቹ የመሰለ ታላቅ ወንድም እዳነ ጥላሁን ይባላል መሀንዲስ ነበር ውጪ ሀገር ሁሉ ተምሮ የመጣ 7 ዓመት ሙሉ በእስር አንገላትተው ፈቱት... እንደ እምቦሳ የሚቦርቅ... ሜዳ የማይበቃው ቆፍጣና ልጅ ከእንግልቱ ወዲህ ሁሉ ነገር ቀፈፈው... ጭምት ሆነ... የሰው ድምፅ ጠላ... ነጋ መሸ መፅሐፉን ይዞ ማቀርቀር ብቻ... እኔ ፈራሁት... ፈራሁለት... ከዛሬ ነገ ወስደው እሱንም ይገሉብኝና ጅባታ ብዬ እቀመጣለሁ ስል...

መቼም ትዕግሥት ጥሩ ነው ታግሶ ቀን ቆጥሮ ... እያያዙን... አካሄዱን አይቶ አንድ ቀን ይኸው እዳነ ያልኩህ ልጄ «... አቡ! ይሄ አውሬ ምክንያት ካገኘ አይተወኝም:: አንድ ቀን ያጠፋኛል:: እኔ ወደ

ውጪ መሄድ ፈልጌያለሁ... አቡ! እንቺን እናቴን ጠልቼ ሳልተቼ... አገሬንና ወገኖቼን ሳልፈልግ ቀርቼ ሳይሆን... አስተዳደሩን በመጥላቴ ብቻ ነው... የአገሬን ሀብት አልዘረፍኩም ሕዝቦቿንም አልበደልኩም። ነገ ምናልባት የተሻለ ዘመን ከመጣ እመጣ ይሆናል።» ብሎኝ ልጄ ሳይወድ በግድ ወደ ውጪ ሀገር ሄደ አሁንም እዛው ነው። ይጽፍልኛል። ድምጡን አላጠፋብኝም። ይረዳኛል።

ሌሎቹም እንዲሁ ይህቺን ደግመሬት፣ እትብታቸው የተቀበረባትን ምድር በወንድማቸው ሞትና በደረሰባቸው በደል ጠልተው ዜግነታቸውን ለውጠው እስከመኖር ድረስ ቆርጠው ተሰደዋል። ያ! ... አረመኔ ያ ዳዊት ያዕቆብ የሚሉት ካድሬም እዚሁ ልጆቻችንን የጨረሰ እዚያ ቼኮዝሎቫኪያ የሚባል አገር (ፕራግ) እንዳለ ልጆቼ ጽፈውልኛል... ዕድሜ ለመንግሥቱ ኃ/ማርያም እያለ ይንደላቀቅ በፈረንጅ አገር ጠያቂ በሌለበት... አንድ ቀን እሱንም የልጆቻችን ደም ያስፈርድበት ይሆናል» ብለው ያንን ዘመን ከረገሙ በኋላ በንጽጽሩ ዛሬን አስበው...

«... መቼም ለዚህ ያበቃን አምላክ የተመሰገን ይሁንና ተደብቀን ስሙን ለመጥራት የምንፈራው ኢሕአፓ እውነተኛ ነበር... እውነተኛ ነው ... ተብሎ ታሪኩን ለምሥክርነት እንዲህ መጠየቃችን እራሱ ትልቅ ዕድል ነው... አንተንም ደርግና መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሳይሆኑ በዳኝነት ያተረፋህ እግዚአብሔር ነው። ይሄንን እንድታይ... እኛ ተረስተን ተሰብረን የወደቅነውን... ከየስርቻ ፈልገህ ... አለሁ... እመሰክራለሁ... ኑ! እንመስክር እንድትል ያበቃህ አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን።» ብለው መሬቷን በእጃቸው ዳብሰው... እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው «... አቤት! ... አቤት! ቸሩ መድኃኒዓለም» ብለው መሬቷን ሳም አደረጓት። ይገርማል ኢሕአፓ





የውጣቶችን አዕምሮ ብቻ ሳይሆን የወላጆችንም ልብ አብስሏል... እጅግ በጣም ጎማችና እንደበተ ርቱዕ እናት ናቸው። ተሰነባበትን።

## «ውሾቼም ተቀጡ»

### ይባላሉ የቀበሌ 03 ነዋሪ ወ/ሮ ስንቅነሽ አስፋው

ወደ እኚህ እናት ቤት እንዳመራ ያነሳሳኝ በዚያን ቀውጢ ሰዓት ቤታቸው ከከተማው ወጣ ብላ በራሷ ግቢ የተከለለች ፍፁም ፀጥተኛ ስለነበረች ለድርጅታዊ አሠራር የምታመች ሁና በመገኘቷ ብዙ ጓዶች አጉንብሰው የገቡባት... በሀገርና በወገን ጉዳይ ሰፊና ጥልቅ ሀሣብ የተለዋወጡባት፣ ክራራቸውን ቃኝተው የስፊውን ሕዝብ የስቆቃ እንጉርጉሮ፣ ጥንካሬውንና አርበኝነቱን ያዜሙባት በመሆኗ የሚያጋሩኝ ትዝታ እንደሚኖር በመተማመን ነበር::

«... እንደዚሁ ሰው ሆነን በስርዓት ሰርተን፣ በልተን፣ ጠጥተን ወጥተን፣ ገብተን የምንኖር አይመስለኝም ነበር... እኛ እኮ በደርግ ዘመን በቁማችን ሞተን ነበር... የወደቀ ሬሣ እንኳ ወደ ጉድጓድ ይጣላል:: እኛን ግን በድናችንን የሚጥለን የሚቀብረን አጥተን ሰውነታችን ተረስቶ...» በማለት ወጋቸውን ቀጠሉ:: «... እዚህ ቤት ብዙ ልጆች ይመጡ ነበር ከነዚያ ውስጥ ስምንቱ ተረሽነዋል:: እነዚያን የመሰሉ አበባዎች ልጅነታቸውን እንኳ ሳውቁበት እግዜር የአዋቂ ልቦና ሰጥቷቸው ለወገን እንዳሰቡ... ምን ያደርጋል?! ... እንዳይሆን እንዳይሆን ሆነ» ብለው በቁጭት ጉልበታቸውን በመዳፋቸው ደበደቡ::

አንድ የፑሽኪን አባባል ትዝ አለኝ «...ሰዎች እንደ ማዕረጋቸው ሳይሆን እንደአስተሳሰባቸው ቢከበሩ ኖሮ ይህ ዓለም የተገላቢጦሽ በሆነ ነበር» የቃሉ እውነትነት ገዝፎ ታየኝ ተራው ህዝብ ለእውነት ሲጋደል ሹማምንቱና አለቆች በዘረፋና በግድያ ተሰማርተዋል:: ይገርማል::






በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የደረሰውን ስቀቀን ሲገልፁ «... እድሀ ልጆቼ ጉሮሮ ብዬ የዘራሁት በቆሎ አሸት ሳይቀር የኢሕፓ መደበቂያ ነው ተብሎ ተጨፈጨፈብኝ እዚህ ከጉኔ ያለው ጉረቤቴ ወታደር ነው «... አንቺ! ልጆችሽ ወታደራዊ መንግሥት የሚቃወሙ ወንበዴዎች አንቺ የኢህአፓ ወላጅ!» እያለ ሞቅ ባለው ቁጥር ስለሚናገር ልጆቼ ደግሞ በተራቸው ማታ ማታ እዚህ እምታየው ጣራ ላይ የድንጋይ ናዳ ያወርዱብኛል:: ማነህ? ... ለምንድነው? ብሎ መጠየቅ? ምንቆርጠኝ የማይሞከር ነገር ... «የኢሕአፓ መሰብሰቢያ» ተብሏ! በመጨረሻ የሚያደርጉት ቢጠፉቸው በአጥር ጥግ ያሰርኳቸው ውሾቼ ላይ ፍልውሀ አምጥተው ደፋባቸው:: እነሱም የኢህአፓ ውሻ ተብለው... ይገርምሀል ዉ... ዉ... ዉ... እያሉ ሲሙሁ ወፐቼ ላይ ከሰውነታቸውና ከመሬቱ እንፋሎቱ ይተናል:: አለቀስኩ:: ለማን አቤት እላለሁ? ቀበሌ ሄጄ ፍረዱኝ ብል አርፊሽ ተቀመጪ ተባልኩ:: ግልምጫ ጠግቤ ወደ ቤቴ ተመለስኩ::

አብስሎ መብላት አስጠላኝ... አልጋው አስጠላኝ... መቀመጫው አስጠላኝ... መሬት እንድትውጠኝ ተመኘሁ «... ወ/ሮ ስንቄ «የነአቢቲ እናት» በተባልኩበት... በተከበርኩበት አውራ ከድንጉላ በወለድኩባት አገር እንደ እንትን እንኳን በእጅ በእንጨት ሊነኩን ተጠየፉን:: ... ልቤ ከልጆቼ ስቃይ አልላቀቅ አለኝ:: ሰውነቴን ጠላሁ... አልታጠብም... ልብስም አልቀይርም:: ልቤ በሀዘንና ጭንቀት፣ ሰውነቴና ጨርቄም በዕድፍ ተበላ:: ከሰው አልገናኝ... ክርስትና ቢባል... ልደት ቢባል... ሠርግ ቢባል አልሄድም:: አብረን ከኖርነው ሕዝብ በመፈክር ከነልጆቻችን ተረግመን እንድንለይ ተደርጓል!

«...እስቲ አሁን እነ አቶ ታደሰ ቦጋለ እነ ዘርዐይ ብሩክ ሰሪ፣ እንሽለቃ ከፍያለው፣ እነዳዊት ያዕቆብ እውነት ከእናት ማህፀን ተወልደዋል??? ወይስ ከሰማይ ዱብ ያሉ ቁጣ ናቸው??? ... ያ!





የምታነቡት ወረቀት እየተቆፈረ ሲጉለጉል ሲወጣ ዘርዐይ «... ስሚ አሁን ይሄ ልጅሽ ቢገደል ይቆጭሽል??» ብሎ አፋጠጠኝ... በጥያቄ አደናበሩኝ «አይ... ጥፋት ካለበት ግደሉታ» አልኩ ተከምረው ተንጉራደውብኝ እንደበቴ በልጀ እንዲፈርድ አስገደዱኝ አይ ቀን ... አይ ይቺ ምላስ... ብቻ ለፈጣሪዬ «እሱው ያውቃል፣ በሱው ያልቃል» እንዳልኩ «ያ የማይነጋ ሌሊት... ያ የማይመሽ ቀን ... ያ የማይገፋ ጭንቅ አልፎ መከራም ቢሆን ተቀምጠን ለማውራት በቃን መቼስ ተመስገን ነው» በማለት በትካዜ ራቁ::



## ለማንኛቸው ላልቅስ??

### ወ/ሮ አስካለ መኩሪያ (ጉመን ሠፈር):-

እኚህ ሴት አንድ ዓይናቸውን ጋርዷቸዋል:: አካባቢው በሀዘን መጉሰቆላቸውን ያውቃል:: ሁለት ልጆቻቸውንና ባለቤታቸውን አጥተዋል:: ጭውውታችንም ወደዚሁ አስከፊ ዘመን የሚመልስ ነበርና የተዳፈነውን እሳት ለመሞቅ (ለመዘንብ) በጥንቃቄ አመጣጡን አስረዳኋቸው::

«... ልጀ ባለቤቴን (ተ/ማርያምን) መውጫ መግቢያ ነሱት:: እሱ ልጁን ላጣ... እሱ ፍሬውን ለተነጠቀ «ልጅህ ኢህአፓ ሆኖ አገር ሊሸጥ ሲል ተገደለ... ልጅህ እኛን ሊጨርሰን...» እያሉ መቆሚያ መቀመጫ አሳጡት:: ቆፍጣናውን ጦር ሠራዊት እንዲሁ አንገቱን እንዳስደፉት የልጁ ነገር ሆድ ሆዱን እንደበላው ወደ ግንባር ለደዱት:: ሞተላቸው:: ምን አሉኝ መሰለህ «... ባልሺን የገደለው ኢሕአፓ ነው:: የልጅሽ ጓደኛ» አሉኝ በካምፑ ውስጥ ባሌና ልጀ ስማቸው የሰበካ ጩው (ማጣፈጫ) ሆነ:: ልቤን አማቱኝ... ለማንኛው በማንኛው ላልቅስ?? ለባሌ በልጀ ወይስ ስለልጀ በባሌ??... ይግረምሽ ብሎ ትልቁም ልጀ ተደገመ:: ይሄውልህ ዓይኔ በእዬዬ ጠፍቶ ቀረ:: የእኔ እኮ ለብቻ ነው:: ሁሉን ተቀማሁ በሰው አገር እረዳቶቼንም ብርሃኔንም አጥቼ ሞቴን እየጠበቅሁ ነኝ::» ብለው እንባቸውን በመንታ በመንታ አወረዱት

ዓለም ይስማው::

## «ልጄንም ቅርሴንም»

**የ/ፖ እለታ ካሡኝ ዘለቀ (ቀበሌ 03)፡-**

ጡረተኛ አባትና በእርሻ ሥራ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ናቸው። ከ17 ዓመታት በፊት በራሳቸውና በልጃቸው ላይ የተፈጸመውን ዘረፋና ግድያ እንዲያወጉኝ ጠየቅኳቸው። እዛውንቱ እንደሌሎቹ ወላጆች ሁሉ እንኳን በአንደበታቸው ሊተርኩት በልባቸው ሲያስቡት እንደሚዘገንናቸው አስረዱኝ።

«… መቼም እግዚአብሔር እያየ የፈሰሰ ደም ስለሆነ የልጆ አወዳደቅ ከንቱ ሆኖ እንደማይቀር አስባለሁ። በቁርጥ ቀኑን አላውቅም እንጂ በነሱም ይፈረዳል። … ጥር 3 ቀን 70 ዓ.ም መጥተው ከዚህ ቤት ወሰዱት። ታሰረ፣ ዋለ፣ አደረ፣ ከረመ፣ በኋላ ይሄንን ቤት ሊፈትሹ መጡ። ቤቱን አመሳቀሉት ፍራሹ፣ ሳጥኑ ምንም የቀራቸው የለ። የተፋቺ ቤት አስመስለው የሚፈልጉትን ቢያጡ አንጡራ ገንዘቤን 300 (ሦስት መቶ ብር) «… የኢሕአፓ ጥይት መግዣ ነው» ብለው ወሰዱብኝ።


በስተርጅና ላቤን አፍስሼ የቋጠርኩትን ጥሪቴን ቀሙኝ ብዬ ለበላይ ይግባኝ እንዳልል ዘመኑ «አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ» ነበርና እስቲ በዚሁ ይለፍልኝ ብዬ አንገቴን ደፋሁኝ። የፈራሁትም አልቀረ። ሚያዝያ 3 ቀን ከ፲/ አለቃ ንጋቱ ወልዴ፣ ፲/አለቃ መኮንን በዳኔ፣ ፲/አለቃ እሣቱ ሻሼ ጋር በቁጥጥር ስር እንድንውል ተደረገ። ለ17 ቀናት ያለምንም ጥያቄ በእስር ካቆዩን በኋላ በመጨረሻ በተናጠል እየጠሩ ልጆቻችን እርምጃ እንደተወሰደባቸውና ምን ሆሣብ እንዳለን ጠየቁን። ደነገጥኩ፣ ነደደኝ፣ አንጀቴ ተቃጠለ… ትሰሙኛላችሁ «አህያ ከሞቴ የባሰኝ መጉተቴ» አለች። ቀን ያወጠልኛል ብዬ በመከራ ያሳደግሁትን የደሀ ልጅን መግደላችሁ አንሶ እኔን በእስር





ማጉላላታችሁ የበደል በደል ነው ብዬ መልስ በመስጠቴ ተቆጡ፤ ደነቁ።

«… ብታንገራግርና ቤቱ ገብቼ እዬዬ እላለሁ ብትል የልጅህ ጽዋ ለአንተም ይቀዳልሀል» ብለው በማስፈራራት ፈቱኝ። ይሄውልህ ልጄ ፈሪ ሆኜ ኖርኩ። እጉንብሼ እለቅሳለሁ። ከዚያ ወዲህ ሕግ አለበት ቀና ብዬ አላይም» አሉኝ በረጅሙ እየተነፈሱና በዓይኖቻቸው ዕንባ ሞልቶ።





## ከረሀብ ጋር ያታግሉኛል

### ወ/ሮ ስንቅነሽ ደስታ (ቀበሌ 03):-

ኩሸና በመሰለች ትንሽ ክፍል ውስጥ እግራቸውን ዘርግተው የተቀመጡ እናት ሊጠፋ በደረሰ ማንደጃ ላይ በጣሳ ውሀ ጥደው ሁለት ራስ ሽንኩርት እየላጡ ተቀምጠዋል:: የሚበተሉትን እያሰናዱ መሆኑ ነው::


መደቡ ላይ ሆነው አሻቅበው ሲመለከቱኝ ዓይናቸው በተስፋ መቁረጥ ደርቆ፣ ሕይወታቸው በብቸኝነት ተወርሮ፣ ከጀርባቸው ጉብጠውና ከአንጀታቸው ታጥፈው በጣም ችግር በገራውና ባለዘበው እንደበት ሰላምታ ሰጡኝ:: ልጃቸው ጓደኛዬ ነበር ታምራት ከበደ የድርጅቱ ስኳድ አባል:: በትምህርት ቤት ሕይወቱ ኮከብ የቀለም ሰው:: በአካል ብቃቱ ድንቅ የቅርጫት ኳስ ተጫዋች:: ተፈጥሮ በመለሎ ቁመት ያጐላችው ጀር.ጋዳ ወጣት:: በመልክ እናቱን ይመስላል::

ታምራት በቀይ ሽብር ግሬደር ተቀብሯል:: ዛሬም እናቱ ከመቃብር ባልተለየ በሚከብድ ባዶ ክፍል የተሰበረ እግራቸውን በደህነኛው ደርበው ከችግርና ከመከራ ጋር ይደባበሳሉ:: አመጣጤን ተረዱ:: የገጻቸው መለዋወጥ ልብ ይቀረድዳል ይህ በደም የተለወሰ ታሪክ በዕምባ ካልራሰ የህሊና ውጋት እንደሚሆን ሁሉ... አድኑኝ... ድረሱልኝ... ፍረዱልኝ... እያለ በሚለምን (በሚማፀን) ሁኔታ ማህፀናቸውን ጨብጠው በሲቃ እየታጀቡ የልጃቸውን ስም ደጋግመው በመጥራት አለቀሱ:: «... ልጄን ታምራትን... አለኝታዬን... ጧሪዬን ቀምተውኝ ጉድ አረጉኝ ታዛቢ አሳጡኝ:: እሱንስ በአንድ ጥይት ገደሉት እጥፍ ብሎ ወደቀላቸው:: እኔን ግን ምን በሚባል ጥይት መትተውኝ እንደሆን አልገልሽ ብሎኝ ከጠኔና ከበሽታ ጋር





ያታግሉኛል:: እነዚህ ጨካኞች ከልጄ ጋር በገደሉኝ:: አባቴንም እትንም አጣሁ ሰርቼም፣ ተቀጥሬም እንዳልበላ አገረ ሰባራ ሆንኩ» በማለት አነቡ:: በእውነት ባይናገሩም ገፃቸውና ቤታቸው ድህነትንና ጉስቁልናን ተቆራኝቷል:: ከዚህ በፊት እንዲጋጠሙኝ ወላጆች ለተረጋጋ ውይይት የሚያበቃ ምንም ሁኔታ ባለመኖሩ በልቤ የእነዚህ አረመኔዎች ጭፍጨፋ ከ17 ዓመታት በኋላም እያመረቀዘ ሕመሙ ዛሬም በየቤቱ እንደጠና ተመልክቼ አጽናንቻቸው ተለያየን::





## ዕጅ ይንሱ

ከነገሌ መቶ ሃያ ኪሎሜትር ርቃ ከምትገኘው ክብረ መንግሥት ከተማ አሥራ ስድስት ወጣቶች መጥተው ሚኢሳ በተባለ ሥፍራ ደማቸው ፈሶ ነበርና ወደዚሁ ከተማ አመራሁ::

ሻ/ባሻ ክፈለው ገዳ ይባላሉ:: የ74 ዓመት አዛውንት ናቸው:: ቀደም ሲል ካነጋገርኳቸው ወላጆች ሁሉ ለየት የሚሉት እሳቸውም እንደልጃቸው በግፈኞቹ የአካል ስቃይ መቀበላቸው ነው::

«... ልጄ እነ ሻለቃ ደስታ መሸሻ (አስተዳዳሪው)፣ ተስፋ መገርሳ (ደህንነቱ)፣ ታደለ ደገፋ (በኋላ የከተማ ሹም የሆነ)፣ ጌታነህ ገብረጻዲቅ፣ ቶሩ ሻመና፣ ጃርሶ ጉዳና፣ ጌታቸው መኩሪያ፣ ብርሃኑ ደበላ፣ በቀለ ቡሳዋ፣ አልዓዛር ጻዲቅና መሰሎቻቸው ምን ያልሰሩብን አለ? አይኔን አስረውኝ አፌን በጨርቅ አፍነውኝ «ልጅህ ኢሕአፓ... አንተ ባለመሣሪያ...» ብለው የሌለኝን ትጥቅ በዱላ ሊያስወልዱኝ ተጫወቱብኝ:: ልጆቻችን ወረቀት ከመበተናቸው ውጪ አንዲት ነፍስ እንኳ ሳያጠፉ በቁማቸው በጥብጠባ ጨርሰዋቸው በቃሬዛ (በሸክም) እንዲሄዱ ከማድረጋቸው በላይ ደማቸውን በበረሃ አፈሰሱ:: እኔንና ልጄን አስሮ ማንገላታቱ አልበቃ ቢላቸው ጌታቸውና ብርሃኑ የሚባሉት እቤቴ መጥተው የገነትን ታናሽ ፀጉሯን ጨምድደው መሬት ለመሬት ጐትተው በሽጉጥ ሰደፍ እራሷን ፈነካክተው ተጫውተውባታል:: እነዚህ አረመኔዎች ዛሬ መምሕራን ተብለው አሉ:: «ለሰው ብርሃን ሊሆኑ¡» ምን ያልፈጸሙብን አለ? የልጄን ስቃይ እንደሴት ቁጭ ብዬ አየሁ:: አልቅሼ አሳለፍኩ በጠቅላላው ለአመት ከመንፈቅ በእነሱ እጅ ተንገላትቼአለሁ:: የሚገርመው በዚያኑ ሰሞን አንድ ኗሪ ይሞትና በቀብሩ ላይ የደራ ሙሾ ይወርዳል:: በዚህ ጊዜ ለልጆቻችሁ አስለቀሳችሁ ብለው እኔንና





ሚስቴን የኑሩን አባት ሐጂ ሐሰን እንደታን አሰሩን:: በእስር ቆይቼ በበረበት የመጨረሻ ወቅት ሻምበል እዮብ መጥተው «አንዱ እንዱ እርስ እዚሁ ተረሱ እዩ ቆይ እስቲ ላስታውሳቸው» ብለውኝ ይዟዱና እንድፈታ አደረጉኝ:: እኙሁ የፖሊስ አዛዥ «ይበሉ ይሂዱና ሻለቃ ደስታን እጅ ይንሱ» አሉኝ:: ጌታዬ የፈታኝ እግዚአብሔር ነው ከፈለገ መጥቶ እንኳን እግዚአብሔር አወጣህ ይበለኝ እንጂ እኔ ወደርሱ የምሄድበት በደል የለብኝም አልኩና ቀረሁ:: ከዚያ ክፉ ጊዜ ጀምሮ ሁለመናዬ ብሶት አዝሏል:: ስንቱን እነግርሀለሁ:: ዛሬም የሚፈነጩት አለማቸውን የሚቀጩት፣ የወለዱትን የሚያሳድጉት፣ የሚድሩት፣ እነሱ ናቸው:: የኛንማ ምን እልሀለሁ::» በማለት ውይይታችን በቁጭትና በሐዘን ቋጨት::

# ምዕራፍ አራት

## ስማዕታት

### የመጀመሪያው ስማዕት

ተማሪው የዘመኑን ተራማጅ አስተሳሰብ የተቀበለው፣ ያዳበረውና ያስራጨው ለተማሪው የትግል ሀሁ መቁጠሪያ ማዕከል ከሆነው ት/ቤት መሆኑ ይታወቃል:: በወቅቱ ከነጌሌ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ይርጋ ዓለም የሄዱ ተማሪዎች ለተሳትፎ ቅርብ የሚያደርጋቸው ደረጃ ላይ ስለነበሩና ሁኔታውም ስለጋበዛቸው ከሲዳማ፣ ከጌዲኦና ከጀምጀም መጥተው ለትም/ ከተገናኙዋቸው ወንድሞቻቸው ጋር የትግል አጋርነት አቋማቸውን አስተባብረው የመንግሥትን ዋልታ ይወዘውዙት ጀመር::

በሲዳማ ዕውቅ የነበሩት ቁጡዎቹ የመኢሶን ሹማምንት እነ አቶ እሸቱ አራርሶ፣ አቶ ወልደ አማኑኤል ዱባለ፣ ቤተና ሆጤሶ፣ ተስፋዬ ሀሚጦ፣ መንክር ግርማ፣ አቶ አፓሎ እና ሌሎችም ግብር አበሮቻቸው የወጣቱን ፀረ-ፋሺስት እንቅስቃሴ ለማፈን በ1969 ተማሪ አጢዎስ ተ/ማርያምን ከሌሎች የሲዳማ ወጣቶች ጋር ወይማ አካባቢ ወስደው ረሸኑ:: መስዋዕትነት ከቃል ሳይሆን ከደም ተደመጠ:: የደም ድምፅ ጥሪው አስተጋባ:: የአጢዎስ አስከሬን ነጌሌ ሲገባ የመጀመሪያ በመሆኑ ልዩና የሚዘገንን ነበር:: ተማሪው ቂም የያዘባቸው ሚሊቴሪ ፖሊሶችና እነ ሻምበል ጳውሎስ «የአጢዎስን አስከሬን አይረከቡም» አለ ጓዶችንን ፋሺስታዊ መንግሥት ገድሎት እንዴት የፋሺስት ወታደሮች ይቀብሩታል በሚል ስሜት ማጉረምረም በረታ:: የቤተ ክርስቲያኒቱ የቀብር ሥፍራ ተጨናነቀ:: ጠቡ ተካረረ በዚያ በምሽት ዱላ ተጀመረ:: ግብግቡ ሲበረታ ተኩሱም ቀጠለ በድንብርብር ተበታተንን:: ወላጆች ሁሉ ተሸማቀቁ::





ከዚህም ሌላ የአጢዎስን አስከሬን ከይርጋዓለም ለማምጣት የተከናተሯት መኪና ሁሉን ለማሳፈር የማትችል በመሆኗ እስከ ከበረ መንግሥት በሌላ መኪና የመጡ ወጣት ተማሪዎች በነበረው የትራንስፖርት ችግር በአጀቢ መኪና ሲመጡ በመገልበጡ እነ ኃይሉ በቀለ፣ ይግለጡ ኪ/ይመር ከፍተኛ አደጋ ሲደርስባቸው ተማሪ እቴቴ በላይ ሀዋዝ በዚሁ አደጋ የደረሰባት ጉዳት ስለጠናባት ሕይወቷ ሊያልፍ በቅቷል:: የሁኔታው አስከፊነት የሁሉንም ልብ ለተጋድሎ አደነደነ:: በቃ! ያለመስዋዕትነት ድል የለም... ወዲያው የፓርቲው የፕሮፓጋንዳ አካል ለመታሰቢያቸው ለአባላቱም ጽናት የተቀኘላቸው ብርታት ሰጪ መዝሙር ተሰራጭ::

«... ምን ልበልህ ጓዴ ምን ልበልህ
በትግል ልከተልህ፣
ኢዳ ከመስኩ ላይ መሲንቾ ከአፋፉ

ቀይ ፈሳሾች አሉ የሚያደናቅፉ» የሚል ተዘመረላቸው ትግል... ትግል... መስዋዕትነት በሕይወት ሙሉ ትርጓሜ እያገኘ መጣ:: አሁንም ወደፊት!

## ሁለተኛ ዙር ሰማዕታት

ምሁሩና ተማሪው በሀገር አቀፍ ደረጃ ዓይኑን ፈፍኖ የመጣበትን ጭፍጨፋ ዓይኑን አፍጥጦ ተቀበለ:: ወጣቱን ሰዶርቶ የነበረው ፍቅር በጠመንጃ ፊት ብርታት ሰጠው የበራሪ ወረቀቶችና ካሴቶች መልዕክት በወጣቱ መንፈስ ሞትን አሳነሱት:: ወታደራዊው ገዳይ ዕጅ በ1969 ወጣት አደን አብዲን ይዞ ካፊን በኋላ በዲዳ ሲበን (አየር ሜዳ) መቀበሪያውን አስቆፍሮ በኤም 14 ጥይት ደብድቦ ከገደለው በኋላ አልባሳቱን በመቃብሩ ላይ አቃጠለ::

በዚሁ ተመሣሣይ ጊዜ በአዲስ አበባ ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ተማሪ የነበረው የ25 ዓመት ወጣት ተማሪ ተስፋዬ ገዛኸኝን ከቃሊቲ ከፍተኛ 2 እስር ቤት ወደ ኢ.አ ከርቸሌ ከወሰዱት በኋላ የግራና ቀኝ ጉያውን በኤሌክትሪክ ጠብሰው በቁሙ እንዲተላና እንዲበሰብስ ካደረጉት በኋላ ረሸኑት:: የደርግና መኢሶን ድብደባ አፈናና ግድያ እየበረታ በሄደ ቁጥር ፓርቲውም ወጣቱን በትግሉ የሚያስተሳስሩትን አንድ የሚያደርጉትን የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ ሥራ ያፋፍም ነበር:: በእስር ክፍል መዘመር... በሞት አደባባይ መዘመር... በየጥናት ክበቡ የትግል ቃል-ኪዳን መግባት...

«...ለዘመናት በጭቆና ማጥ፣ በግፍ ሠንሠለት ታስሬ፣
መብቴን ላስከብር ጨቋኙን ልሽር ተነስቻለሁ ዛሬ፣
ይኸው ታጥቂያለሁ ዛሬ::
ፍፁም ነው ዕምነቴ፣
የትግሉ ነው ሕይወቴ::
ልጓዝ በድል ጉዳና
በወደቁት ጀግኖች ፋና» በማለት አዜመ:: መስዋዕትነቱ ቢከብድም ኢሕአፓን አመነ በኢሕአፓ በእጅጉ ተማመነ::





«ኢሕአፓ ባለድል ፓርቲያችን፣
አለኝታ መሪ ኮከባችን፣
ተበቃይ አለ ከኋላችን፣
እንፈራም ትጥቁን የጠላትን::
ታጋይ... የተወለደው በትግል፣
ትግል... ከደም ሥሩ ተዋህዷል::
ወኔው... የማይሞት ለዘለዓለም፣
ፍፁም... ለፋሺስት ጦር አይገዛም::» በማለት በቅብብል አዜመ::

በየሆዋሱ ደረቅ ርዕዮተ ዓለማዊ ጥናት ብቻ ሳይሆን ኪነ-ጥበባዊ ክንዋኔዎች በውበት በድምቀትና በጥራት በተከታታይ ተሰራጩ:: ሕይወትና ሞት ይፋተጉ፣ ይታገሉ፣ ይሳመጡ ጀመር::

## 3ኛ ዙር ሰማዕታት

በ1969 ኢ.ጋማሽ ከነጌሌ ወደ አዋሣና ኢ.አ ኪ.ዓዘዋቾው ወጣቶች መካከል እነ መም/በሪሁን ገ/ሕይወትን፣ መም/ታምራት ኃይሌን፣ መም/አስረስ ካሣን መም/ሙሉጌታ አሰፋን፣ መም/ ታፈሰ አምሳሉን፣ ተማሪ አለማየሁ አጀብን አቶ ድበትን፣ ሼክ ኢድን፣ ኩሉኔል ይርጋሸዋ ገለታን፣ ሻምበል መኩሪያ ቢራቱን፣ አንድ ስሙ የተዘነጋ ኩሉኔል ከሌሎች የአዋሣ ልጆችና ዳንኤል ታፈሰ (ዘመሚት) ከሚባል የይርጋ ዓለም ልጅ ጋር ነሐሴ 19 ቀን 69/ ዓ.ም ወደ ወንጀ ገነት በመውሰድ ፈጇቸው።

በዚህ ዕለት የተፈፀመው አገዳደል እንዴት እንደነበረ በቦታው በአጃቢነት ሄዶ የነበረ ወ/ር ገመቹ ፉላስ በሰጠው ምስክርነት «... በስፍራው የነበሩ ባለሥልጣናት ሻምበል ባሻ ጌታሁን አበዪ፣ ኃይለየሱስ አባሀሰን፣ ጴጥሮስ ገብሬና ሌሎች ባለሥልጣናት የገበሬ፣ የወጣትና የሴት ማህበራት ተወካዮች ነበሩ። ምሽት ስለሆነ በጀኔሬተር መብራት ፌስቲቫል መሰሉ ዝግጅት ድምቀት እንዲያገኝ ተዳርጐ እየተበላ እየተጠጣ ነበር።

አብዮቱ «ብአናርኪስቶች» ላይ ስለተጐናፀፈው ድል በኃይለየሱስ አባሀሰን ገለጻ ከተደረገ በኋላ በአስረሽ ምቺው ድግስ ፊት መም/ታፈሰ አምሳሉ ዕርቃኑን በፓንት ብቻ ታስሮ ቀረበ። የክ/ሐገሩ አስተዳዳሪ ኃ/የሱስ ሽጉጡን በመምዘዝ ሲደግንበት ሟቹ በሙሉ ድፍረት «ሐፋሺስቶች ጥይት እንጂ ዳቦ አንጠብቅም ኢሕአፓ ያሸንፋል! ፋሺስቶች ትወድማላችሁ!» እንዳለ ተኮሰበት ወደቀ... ደገመው። ተጨበጨበለት። መፈክሩ ወረደ በመቀጠልም መም/በሪሁን ገ/ሕይወት ቀረበ። የክፍለ ሀገሩ የሴቶች ድርጅት ሊ/መንበር





አነጣጥራ ገድለው ተደረገ። ከማጀት ወደ አደባባይ የወጣችው አብዮቱን በደም ልታቀላው እንደሆነ በግብር ተገለፀላት። ተጨበጨበ።

እየተበላ እየተጠጣ መፈክር እየወረደ ሌሎቹና ጀግኖቹ ወታደራዊ መኮንኖችም በጎሊና ቢስ የከተማ አውደልዳዮች እጅ ታስረው ተረሸኑ» በማለት ዘግናኝ ትውስታውን ተረከ። በዚህ መልክ ደርግና መኢሶን «የዝንጀሮ ጉልጓይ፣ የጠጣ ዘር አቀባይ፣» በመሆን የተስማሩበት ያገር ማሣ ፍሬ አልባ ሆነ። በተቃራኒው ግን ወጣቱ፡

እምቢ ለባንዳ እምቢ ለፋሺስት

ክቶ አንገዛም በኃይል በጥይት

ተኘተህ የነበርክ ተጫጭኖህ እንቅልፍ

ጊዜህን ለትግሉ ሰዓትህን ለትግሉ ወስነህ አሳልፍ

ወገን ልብ ግዛ

ወገን ድፍረት ግዛ

በቃኝ በል ጭቆና በቃ በል ብዝበዛ » እያለ በአቋሙ ፀና...

ገድያው ተፋፋመ።

## 4ኛ ዙር ስማዕታት

ሕዝባዊው ወገን ስቅይቱ የበዛ ቢሆንም ከዚህ ሁሉ ግርፋት ስቃትና ሞት በኋላ ግን ኢሕአፓ እንደሚያሸንፍ ታላቅ ተስፋ ስለነበረው ሞትን ያለመጠራጠርና ያለምንም ፍርሀት ተጋፈጡ። የደርግ መኮንኖችና አስር አለቆችም «ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ከእኛ ሌላ ማን አለ?» ብለው በተነሱ የመኢሶን ሰዎች እየተገፉ በእያንዳንዱ የአገራችን ደረቅ ጣቢያ ሁሉ ቀይ ሽብር ያፋፍሙ ነበር። በ1970 ዓ.ም መግቢያ በጀምጀም ተማሪ ሰይፉ ስለሞንን በሬ ላይ ተማሪ ዳንኤል ፈጠነን ተማሪ ምህረተአብ አስገዶምን 20 ከሚደርሱ የሲዳማ ወጣቶች ጋር ረሸኑ በመኢሶንና ደርግ ካምፕ ታላቅ ፈንጠዝያ ተደረገ።





## 5ኛ ዙር ስማዕታት

ደርግና መኢሶን በጭካኔና በፍርሀት ያካሄዱት የነበረው ጭፍጨፋ ተቃዋሚዎቻቸውን ብቻ ቢመስልም በአብዛኛው ግን ግፍና ግድያው በንፁሀን ላይም በርትቶ ነበር። በነጌሌ አካባቢ ፊታቸውን ወደ ጭቆኑ ወታደር ሲያዞሩ ምክንያታቸው እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነበር። በዚያን ወቅት የሶማሌ ጦር ገፍቶ እስከ አጉባ ድረስ (42 ኪሜትር ርቀት) መጥቶ ነበር። የኃይል ሚዛኑ ፈጽሞ የማይጣጣም ስለነበረ የኢትዮጵያ ጦር ማፈግፈግ ግድ ሆኖበት ነበር።...

የካድሬው አካኪ ዘራፍ ሰበካና የጠሩ ስሜት ተዋጠረ። አንዳንድ የሠራዊቱ አባላት በዕልቂቱ አስገዳጅነት ሀቁን በግንባር ማስረዳት ተያያዙ። «... ኮንጐም ዘምተናል በብዙ የውጊያ ቀጠናዎች ውለናል ግን መድፍ በኤም ዋን አልመለስንም። በኮርያም ዘምተናል የአገራችንን ስምና ባንዲራ ከፍ እንዲል አድርገናል ቢሆንም በዛን ሰዓት መድፍ በመትረየስ አልመለስንም... ይህ ለማያስፈልግ መስዋዕትነት የዳረገን ውጊያ በትጥቅ ይስተካከልልን» ብለው ጠየቁ። በዚህ ግዜ ካድሬዎቹ «የኢሕአፓ ጀሌ ናችሁ። ከሱማሌ መንግሥት አገራችሁ አገር ልታስቆርሱ ነው» «ለካ ተዋጊውን ሠራዊት ከኋላ የሚጥለው የእናንተ የኢሕአፓዎች ፀረ-አብዮት ጥይት ነው» «ሳጭ ታንክ መጣብህ ሽሽ እያላችሁ ጦሩን የምታስበረግጉት እናንተ ናችሁ» ብለው በጦሩ ፊት በታወረ ሀሰት ከወነጀሉና ካወገዟቸው በኋላ ታህሣሥ 1 ቀን 1970 ዓ.ም እነ መቶ አለቃ ጌታቸው ገ/መድህን፣ መ/አ አለማየሁ ደምሴን፣ ሻ/አለቃ ቦጋለ መኮንን፣ ወ/ር ገብረየሱስ ጉሳን ወ/ር ተስፋዬ ዳመሳን፣ ወ/ር ተካ መኮንን፣ ወ/ር አብዲ ሰንደሉን፣ ወ/ር አወልን፣ ወ/ር ደምሴ ገ/ሥላሴን፣ ወ/ር ለማ እንግዳወርቅን (ሙሽራውን ከጫጉላ ቤት አውጥተው) ወ/ር በላቸው ከበደን፣ ወ/ር አሰፋ ቢልልኝን ወ/ር ጉሣዬ ሽብሩን ሌላ ስማቸው

የተዘነጋ የሀ/አለቃና በጠቅላላ ቁጥራቸው ከ15 የማይበልጡ ወታደሮችን አጉባ ላይ በመትረየስ ደበደቡ::

በዚያ የፍልሚያ ግንባር ሠራዊቱ ከአገሩ ፍቅር ባሻገር በካድሬዎች ላይ የነበረው ጥላቻ እስከ አልነበረውም:: ተቀላቀል ሲባል ሳንጃውን በአፈሙዝ ወድሮ «ሚሊሺያ ወደፊት ካድሬ ወደኋላ» በማለት ነበር ለብሔራዊ ክብሩ በስሜት ሲዋደቅ የነበረው::... የሁለት ወገን ጦርነት... በአንድ በኩል የሞቃዲሾ ሠራዊት በሌላ ፊት ከጉያው ቀጣፊና ቀሳፊ ካድሬዎች::





# 6ኛ ዙር ስማዕታት

ትውልዱን ለማውደም ፋሺስቶች ደም የሚያስጠጣ አባሌያቸው ቶናቸው... የሰው ሥጋ ተራቡ... ከሰብአዊነት ተራ ወጡ... መትረየስ መዘመር ወደዱ... በስቃይ መደሰት መረጡ... ሰው መብላት አፉቸውን ከፈቱ:: የሁኔታዎች አስከፊነት የእያንዳንዱን ሞር ህልውና እያጣበበው መጣ:: በ70 ዓ.ም አጋማሽ እስከ 100 (ሙት) የሚደርሱ ወጣቶችን በማሰር የበዛ የአካል ሥቃይ እንዲቀበሉ አረጉ:: ምላስ እስከመቆረጥ... አንዳንዶችን ለከፍተኛ የአዕምሮ መቃወስ አደረሱ:: በእውነት በዓለም ላይ እንደ ፋሺስቶች ያለ ፈሪ የለም:: ጭካኔያቸው የሚመነጨው ከድፍረትና ቆራጥነት ሳይሆን ወሰን ከሌለው ጭንቀትና ፍርሀት በመሆኑ ለእርምጃቸው ምርጫ የለውም::

ወጣቱ በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ሆኖ አብዛኛው አባልና ደጋፊ ከክህደት ይልቅ የክብር ሞትን ቢመርጥም ፓርቲው በደረሰበት አገር አቀፍ ጠንካራ ጭፍጭፋ ላይ የሁኔታዎች አስገዳጅነት በመታከሉ በተወሰኑት ዘንድ በሌላ ክፍለ ሀገርና አውራጃዎች ሆነ ተደረገ:: ሲባል የምንሰማው የድርጅቱ የውስጥ መፍረክረክና አንዱ አንዱን አሳልፎ የመስጠት ሁኔታ በነጌሌም ተከሰተ:: ወኔ ፈሰሰ... ቃልኪዳን ተጣሰ ... «... ሆዴን ሆዴ ስለው ቁርጠቱ ገደለኝ» እንዲሉ ፓርቲው ለታላቅ ኃላፊነት ያስቀመጣቸው ጓዶች ምሥጢሩን ይጉለጉሉት ጀመር:: የሚተርፍ እየመሰለው ጓደኛን ቆሞ የማስገረፍ አሳዛኝ ሁኔታ በስቃዩና ውድቀቱ ላይ ተደርቦ ቅስሙን ሰበረው... አንዳንድ ጓዶች የሰው መሰል አውሬዎችን ተራ አታላይነትና አጥማጅነት፣ በመዝረክረክና በፍርሃት ስለተቀበሉ ራሳቸውንና ጓዶቻቸውን ለከፍተኛና ለማያዳግም ምት አጋለጡ::

ለነጌሌ ቦረና ወጣቶች በግፍ መጨፍጨፍ [illegible] ና አቶ ታደሰ ቦጋለ (የሕዝብ ደህንነቱ ኃላፊ)፣ አቶ [illegible] (በሕዝብ ድርጅት የመኢሶን ካድሬ) አሁን ውጪ ያለ [illegible] ብሩክ ሰረ (አሁን ሻለቃ ኢ.አ የሚገኝ)፣ ሻምበል [illegible] ካድሬ)፣ ሻለቃ ከፍያለው አድገህ የፖሊስ አባል (ቀኛ አዛዥ) ጌዲዮን፣ አባቡ ደበሌ (መ/አለቃ)፣ ሰለሞን ዘነበ፣ አበራ (የሕብረት ካድሬ)፣ ወ/ር ተስፋዬ ሮበሌ (መርማሪ)፣ ጌጡ አምበርበር (ከሕዝባዊ ድርጅት) ከጤና ጥ.ተወካይ ዶ/ር ሞላ እንዚህና ሌሎችም የቀበሌ ታጣቂ ተባባሪዎቻቸው የነጌሌ ቦረና «ታጋዮች» እንደ አዲስ አበባው ሬዲዮ... እንኳንና ጥይት ደህና ዱላ ሳያርፍባቸው «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል!» ብለው በአናርኪስቶች ላይ ይፋፋም በማለት ለዘለዓለም በሚጠይቃቸው ደም ለጊዜው «አብዮታዊነታቸውን» አስመሰከሩ።

በሚያዝያ ወር 3ኛው ቀን 70/ዓ.ም በሻምበልባሻ ጌታሁን አቦዬ የሚመራ ቡድን ከአዋሣ በሄሊኮፕተር በመጣ ምሽት ከምሽቱ በ4:00 ሰዓት ወህኒ መጥተው እነ ተማሪ እሸቱ ተሰማን፣ ንጉሢ ወንድሙን፣ ሙሉዓለም ንጋቱን፣ ተስፋዬ ካሰኝን፣ ከንፉ አማቱን፣ አስጨናቂ አማቱን፣ ታምራት ከበደን፣ ሰለሞን በቀለን፣ መሰለ አየናቸውን፣ ምንዳዬ ሢሣይን፣ መም/ ኮርማ ዱግዳን፣ መም/ገዛኸኝ ተገኜን፣ መም/ ተክስተ ገ/መስቀልን፣ መም/ታፈሱ ከበደ፣ መም/ዋሪዮ አዲን ተማሪ ግርምት ዓለም ደገፉን (ነፍሰጡር የነበረች)፣ አበበች ካሣን፣ በሺር ኢድንን፣ ዮናስ ማሞን፣ በኃይሉ ተስፋዬን፣ አለማየሁ ለማን፣ ዘሪሁን አስፋውን፣ ፀጋዬ መኮንንን በጠቅላላ ሃያ አምስት ወጣቶችን ሌሊት ታከለ ዋርካ በሚባል ሥፍራ ወስደው ረሸኗቸው።





7ኛ ዙር ስማዕታት

ዶቹን ሠይጣን ሳያተስ አይተውም» እንዲሉ እየቀዱ ሚጎነጩለት የደም ጉድጓድ ቢጉድልባቸው ለማድያ አገረገሩ። ጆሮ ወቻቸውን በየጓዳው በየጉድጓዳው አሰማሩ... እንኳንስ የተበደለን ዎችን የሚቀሰቅሱ (የሚያነቃንቁ) የእንጉርጉሮ ግጥሞች አጃቸው

ቱ::

«... ወንድሙ ሲገደል፣ ወንድሙን ካልከፋው፣

እምጡሉት ሱሬውን ደሙ እንዲከረፋው።...» ይህ ለበቀል ትግል) ተነሱ የሚል ድምጽ በወጣቱ እጅ... በወጣቱ ልብ... በደም ፈ ሀቅ በመገኘቱ እነ እጅሬ ተደናገጡ። እንዲታፈንም መንግሥቱ ኃ/ማርያም ስም ተማምለው ተነሱ። በሐምሌ አጋማሽ ዓ.ም አሥር ያህል ወጣቶችን ይዘው ኢ-ሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ምርመራ ከአስቃዩዋቸው በኋላ ደም የለመደ ሁለንተናቸው ሜማዊ ኢህአፓን አገኘን» እያሰኘ ያስጓራቸው ጀመር።

ትርዒቱ እንዲህ ነበር ከሌሊቱ 9:30 ሰዓት ሲሆን ከእስር ቤቱ ተጀርባ የወታደር መኪናዎች ድምፅ መሰማት ጀመረ። ወደ ግቢው ቱ። እነ ጌታሁን አቦዬ ለግድያ የሚያዝገዘጉባትና በየደረሱበት ማለጫ ይሰጡባት የነበረችው ባለማይክሮፎን ላንድሮቨር ገብታ ብራቷን በረጂሙ ወደ እስረኞች ክፍል ለቃ ቆመች። ሌሎችም ችና ዋዞች ካድሬዎችንና አጃቢ ወታደሮችን የያዙ በዙ። 10:00 ሰዓት ሲሆን የበረንዳው መብራት በራ ሁሉም ወደ እስር ክፍሉ ጡ የ01፣ የ02፣ የ03፣ የ04፣ የ05፣ የ06፣ ቀበሌ ሊቃነመናብርት አባቢያችን ሕዝብ የሚያውቃቸው ገዳይ ታጣቂዎችና ጥበቃ ኞች፣ የከተማው ሹም፣ የጠሩ አዛዥ፣ ዘርዐይ ብሩክ ሰረ፣ አባቡ

ደበሌ፣ አረጋ፣ ጌዲዮን፣ ሻለቃ ከፍያለው እድገት ... ሌሊ... በርካታ በምሥጢር ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች እጅ... እጅ... በለው ...

ከመካከላቸው አንዱ በርካታ ገመዶች ከመኪና ውስጥ አውጥቶ አመጣ:: ሁሉም ተራ በተራ እየተጠሩ እንዲጠበቡ ተደርጎ እጆቻቸውን የኋልዮሽ ተጠፈሩ:: የከፍለ ጦሩ አዛዥ ኮሎኔል መንግሥቱ ወልደ ገብርኤል ወደ መብራቱ ከቀረበ በኋላ የንግግር ወረቀቱን ዘረጋ:: «አፈር ልሶ የሚነሳ አባብ መርዙ ሃያል እንደመሆኑ የእነዚህም ዳግማውያን በቀይ ሽብር ባፀዳነው ወጣት የህብረተሰብ ክፍል መሀል መገኘት አደገኛ ነው» በማለት ካተተ በኋላ «... መንግሥታችን ባዘዘው፣ ባፀደቀውና ሕዝብ ባመነበት መሠረት በግልጽ ሊታዩ በሚቻልበት ቦታ እየተወሰዱ ከመሬት በላይ እንዲፈጸም» በማለት አዘዘ:: ቀበሌዎች ጭዳዎቻቸውን እየጐተቱ ሄዱ:: በ05 ቀበሌ የተፈፀመው ግድያ ከእስር ክፍሉ ጀርባ ስለነበረ የማለዳውን አስፈሪ ፀጥታ ጥሶ የወጣት ዘነበ ባሕሩ ድምጽ ተሰማ::

«ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከሚያሰቃዩዋቸው ፋሺስቶች እጅ በታጋይ ጀግኖች ልጆቿ ቁርጠኛ ትግል ነፃ ይወጣሉ!» ካለ በኋላ የአውቶማቲክ ተኩስ በአካባቢው አስተጋባ ፀጥታ ሆነ.. ርጭ አለ:: «ኢሕአፓ ያሸንፋል!» የሚል ድምጽ በተዳከመ ትንፋሽ በተደጋጋሚ ተሰማ:: የሌሎችም ሀቅ የሚቃትት ድምፅ እንዲሁ:: ሊታፈን የማይቻል የፍትህ ጠያቂ ድምጽ ለጊዜው ተዘጋ:: ነሐሴ 11 ቀን 70 ዓ.ም. ሌሊት ተማሪ መሰለ ጥላሁንን፣ ዘነበ ባህሩን፣ አደን ዋሪዮን፣ አገሬ ከበደን፣ አልማዝ አለማየሁን፣ አቶ ተካልኝ ሆቴቴን፣ ወ/ር ምንተስኖት ዛፉን አንድ ሚሊሺያ የጉንደር ልጅ በድምሩ 8 (ስምንት) ወጣቶችን ገድለው በላያቸው ላይ መፈክር ከለጠፉባቸው በኋላ በየቀበሌው መንገድ ጥለዋቸው በትዕዛዝ ሕዝብ ከየቤቱ ወጥቶ እንዲያይ አደረጉ::






# 8ኛ ዙር ሰማዕታት

የደርግና መኢሶንን ብርቱ የደም ስካር የወለደውን ታላቅ እውሬነት መግለጽ ያዳግታል:: በኦሽዊትዝ የናዚ ጀርመን ወንጀለኞች ከደርግና መኤሶን መኳንንት የሚለዩት በኬሚካል መፍጀታቸው እንጂ በጭካኔ ድርጊታቸው ሁሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ያህል ነበሩ ነሐሴ 11 ሌሊት በስምንቱ ወጣቶች ላይ በአደባባይ ግድያ ከፈፀሙ በኋላ በነሻለቃ ደስታ መሸሻ (የከ.መንግሥት አስተዳዳሪ)ና ጀርሶ ጎዳና የመኢሶን ካድሬ አጋዥነት በነሻምበል ባሻ ጌታሁን አበዬ በገኝነት ተግዘው መጥተው በነጌሌ ወታደራዊ ካምፕ 27ኛ ሻለቃ ምድር ቤት ውስጥ አፍነዋቸው የነበሩትን:-

እነ መም/ ካሡ መኮንን፣ መም/ በቀለ ኃይሌ ፣ መ/ ብርሃኔ ርዕሶም፣ ተማሪ ሱሌማን ሀጂ ከድርን፣ አድማሱ አንዳርጌን፣ አንተነህ ዕርስቱን፣ መስፍን መሀመድን፣ ሰለሞን ሐይሌን ገነት ከፈለውን፣ ምርዓት አሰግድን፣ መክብብ ዘመድኩንን፣ ኑሩ ሀሰንን፣ አልማዝ ጣፋ፣ እሱ ባለው ሳህሉን ሁሴን ነጋሽን፣ ዋቁማ አባ ቡልጉን፣ በድምሩ 16 ወጣቶችን ነሐሴ 12/1970 ዓ.ም ደማቸውን ሲያፈሱ ከነዚሁ ጋር በአጃቢነት ሄዶ እንዲረሽን የታዘዘው ወታደር መሰለ አይኑ እያየ ለመግደል ስላዛዘኑትና ስለተጨነቀ አንገቱን አዙሮ በመተኮሱ እሱም እዚያው ተደርቦ እንዲገደል አድርገዋል:: የእነዚህ ወጣቶች አስከሬን ሚኤሣ በተባለ ገ/ማህበር አካባቢ ሜዳ ላይ ተፈነጋግሎ ስለነበረ የአካባቢው ገጠሬ በወጣት ሴቶችና ወንዶች ላይ የተፈፀመው የግፍ ግድያ ሳያንስ ለአውሬ መጣላቸው ስለተሰማው ተሰባስቦ ወደከተማ በመምጣት «እንዲያ ያለ ተአምር ምንድነው? ለምንስ በእኛ አካባቢ ተደረገ? ከሆነስ ለምን አይቀበሩም?» ብሎ በመጠየቁ ከ03 ቀበሌ ለአስተዳደሩ ሁኔታው ተገልጾ ዘርዐይ ብሩክ ሰሪ የተባለው ካድሬ በማግሥቱ ግሬደር ይዞ ሄዶ እንዲቀበሩ አድርጓል::





## ስማዕታት መምህራን

መም/ በረሁን ገ/ሕይወት

መም/ አስረስ ካሣ

መም/ ዋሪዬ አዲ

መም/ ካሱ መኮንን

መም/ ተከስተ ገ/መስቀል

መም/ ፀጋዬ መኮንን





## ስማዕታት ወታደሮች

...ጌታቸው ገ/መድህን

፲አለቃ ቦጋለ መኮንን

ወታደር አብዲ ሰንደሎ

ወታደር ተስፋዬ ዳመሳ


ወታደር ተካ መኮንን

ወታደር ገ/የሱስ ጉሳ

ወታደር ደምሴ ገ/ሥላሴ

ወታደር ጉሳዬ ሽብሩ

ወታደር ምንተስኖት ዛፉ





ስማዕታት ተማሪዎች

ንጉሴ ወንድሙ

እሸቱ ተሰማ

በኃይሉ ተስፋዬ

ሙሉአለም ንጋቱ

ዋሲሁን ኃ/ሚካኤል

ዘሪሁን አሰፋው

በሽር ኤደን

ዮናስ ማሞ

ምንዳዬ ሲሳይ





…ለስ ጥላሁን

ገነት ክፈለው

ሰለሞን ኃይሌ

ዘነበ ባህሩ

አንተነህ ርስቱ

አልማዝ አለማየሁ

ከንፉ እሳቱ

ግርምትአለም ደገፉ

አለማየሁ ታደሰ



ዳንኤል ፈጠነ

ሀገሬ ከበደ

ምርትት አስጣው

ዳንኤል ታፈሰ

ተካልኝ ሆቲቲ

አለማየሁ አጅብ

አደን አብዲ

ተስፋዬ ገዛኸኝ

እሱባለው ሳህሉ



ፍቃዱ ሙላት

አበበች ካሣ

አድማሱ አንዳርጌ

ኑሩ ሀሰን

ታምራት ከበደ

ተስፋዬ ካሡኝ

አጢዎስ ተ/ማርያም

አስጨናቂ እሳቱ

መስለ አየናቸው


ኢብራሂም አሊ(የጠፋ)


አልማዝ ጣፋ


ስዩም ወ/መስቀል(የጠፋ)





## እራስህን ጠይቅ

ማወቅ ምን ዋጋ አለው... መልኩን ካልለወጠ?
ዕምነት ምን ያደርጋል ... ፍቅርን ካልገለጠ?
ልሳንስ ምንድነው .... እውነት ካላሼተ፣
ከተንሸራተተ .... ከወሸካከተ።

አንተው ባንተው ዙሪያ፣
ከላይ ታች ግራ ቀኝ ... ከወዲህ ከወዲያ፣
እያየህ ልክህን ... ቁመና ክብደትህን፣
እየመረመርከው ... ሚዛን ቅኝትህን፣
ክሰስ ... እስቲ ዳኘው፣
ባዶ ስብዕናህን ... ኮንነው ሞግተው፣
በል! ... እራስህን ጠይቅ!
በላ! ... ሽፍንፍኑን ፈልቅቅ።

እስቲ አንተው ምርጫ ስጥ፣
ምኞትህን፣ ፍርሃትህን ... ከእውነት ሳታስበልጥ፣
ከወገን ሳታስብ ... ደም ሕይወት ሳትድጥ።
ጠይቅ! ... አንተኑ አንተው ጋ፣
ራሱን የተመታ ... ጉት የተወጋ፣
ሆዱ የቆሰለ፣
በምኑ እፎይ ይላል ... ከሰው ... የሰው ዕዳ ካልተገላገለ?
በለው ልቡናህን፣
ሸሽግ የኋላህን።

የአፍ ልማድ ከሆነ ... ለሰው ልጅ ቃል-ኪዳን፣
ዘላቂ ካልሆነ ... ሥራ ክብረ-ወሰን፣
ሁሉን ካላቀፈ ... አደራ ኃላፊነት፣

ማወቅ ዕኮ ቃል ነው ... የስያሜ ዕውቀት፣
ፍቅርም ሩቅ ተስፋ ናት ... ጽልመት የከበባት።

አንተው ባንተው ዙሪያ...፣
... በውስጠኛው ዓይንህ ... ውጪህን ስታየው...
... ደፍርስ ታውኮ... በጥቅም ብናኝ ትቢያ፣
እውነት እየፈራህ ... ውርደት እየሰራህ፣
ጥቅም ኢያባነነህ ... ውስጥህ በደል አዝሎ ... እየመዘመዘህ፣
ያልከውን ዘንግተህ ... ሳያጣ ባጣ ቤት ... ጠግበህ ኢያገሳህ፣
የአገር የወገን ቅስም... በመርዝ ዕድፍ አሽተህ።

ለምን ትመስላለህ ? ... ራስህ ያልሆንከውን?
የማትፈልገውን ... ፍፁም ማትሰራውን።
ዕውነት ... አፍ-ከልብ ያልሆንካት፣
ባይሆንም ሚመስላት .. ወይ ቀንተህ ሆነህት ... የምትመልስላት፣
በአገር በወገን ስም ትጠይቅሀለች፣
በዕምነት አጉዳይነት ... ትካሰስሀለች።

ሆኔህ ለረሳኸኝ ... አጥግቤህ ላስራብከኝ፣
አክብሬህ ለጣልከኝ ... አምኜህ ለካድከኝ፣
መልኬን ... ስሜን ... ክብሬን ... ምስህ ለቀበርከው፣
ደሜን ለበከልከው ... ምላሽህ ምን ይሆን? ... ካሣዬ ምንድነው ???
ትልሀለች!... እራስህን ጠይቀው ... ውስጠ በላይህን፣
ይፋ ተደራድረን የማንረታውን .... ግን የምናውቀውን፣
የማትሸሽገው ፀፀት ቀላቢህን።





ሚበልጡህን ማትፈቅድ ... ሚስሩትን ማትወድ፣
ሰብዕናህ አጉል ... ቁልቁል ገደል ሚስድ።
የዓይን-ህሊናህ ጥበት፣
የጽንሰ-ግብርህ ክፋት።
የአንደበትህ ቡሬ ወንጭፍ፣
የሚያደማ የሚናደፍ።

ያልሰረፀብህ ያልተካንከውን፣
መሆን ወዳጅ ያልሆንከውን።
መምሰል ሚመስልህ ዕምነት፣
ያለ ዓላማ ሥር መሠረት።
የለመለመ የምታደርቅ፣
የተገኘ የምትደብቅ።
የበደል ስም የምትሰጥ፣
ያለ ቦታው ምታስቀምጥ፣
ያለ ሥራ ምታስበልጥ።

ያለ ሙያህ «ሙያተኛ»፣
ያለ ዕውቀትህ «ጥበበኛ»።
አመቻችተህ ሁሉን አውጋዥ፣
ደነዝ «ጠቢብ» ስውር ተጓዥ።
የጠራውን ኩል አደፍራሽ፣
ታዳጊውን ለጋ በጣሽ።

እስቲ አንተው ምርጫ ስጥ፣
ምኞትህን ፍርሀትህን ... ከእውነት ሳታስበልጥ።
ራሱ የተመታ ... ጐኑ የተወጋ ... ሆዱ የቆሰለ፣
በምኑ እፎይ ይላል? ... ካንተ ቢጤ እሾክ ... ካልተገላገለ።

ጠይቃት ነፍስህን፣
ሽሽግ የኋላህን።

በሌሎች ትከሻ ... ድካም ሳትደበት፣
እንዲሁ ሕዝብ እያልክ ... ያገር ንዋይ ሳትሰርቅ፣
ዞረህ ምትዝልበውን ... የከርስህን ጣጣ፣
የወኔህን ስልበት ... የብክነትህን ዕጣ።
ከማስመሰል ካባህ ... ከመሽፋፈኛህ፣
ተጋልጠህ ተገዛ! ... ለውስጠ ህሊናህ።

ያገር ችግር ምክንያት ... መሆንክን ገድበው፣
ምቾትህን፣ ፍርሀትህን ... ግልቢያህን አስክነው፣
ሕይወት ሲነጥፍ ... ሲረግፍ ... ራስህን አትደብቀው።

ማወቅ ምን ዋጋ አለው ... መልኩን ካልለወጠ፣
ዕምነት ምን ያደርጋል! ... ፍቅርን ካልገለጠ።
ልሳንስ ምንድነው ... እውነት ካላሼተ፣
ከተንሸራተተ ... ከወሸካከተ።

የአፍ ልማድ ከሆነ ... ለሰው ልጅ ቃል ኪዳን፣
ዘላቂ ካልሆነ ... ሥራ ክብረ-ወሰን።
ሁሉን ካላቀፈ ... አደራ ኃላፊነት፣
ማወቅ እኮ ቃል ነው ... የስያሜ ዕውቀት።
ስለዚህ ተመለስ ... እራስህን ጠይቅ፣
ኢትዮጵያዊ ሕዝቧን ... ኖረህ አትደበቅ።

**በወርቅአለማሁ ንጋቱ (መስለው ለሚበድሉ)**





## መደምደሚያ

በጠቅላላው ማለቲያ በሌው የቀይ ሽብር ጥቃት ሕዝብ ቅስሙ በሀዘን ተሰበረ፣ አገር አበባዋ ተቆረጠ፣ ተስፋዋ ደበዘዘ። እነስተኛዋ የጠር ከተማ ነጌሌ የተማሩ፣ አርቆ አሳቢ፣ ለሕዝብ ተቆርቋሪ ትውልድ መሪ ልጆቿን ከሚያዝያ 69 እስከ ነሐሴ 70 ዓ.ም ባለው ጊዜ አጣች ከ70 በላይ የንጹሐን ደም ፈሰሰባት።

ሰው በሌለበት መንደር እንዲህ የሆኑ በሌላውማ ምን ይቀራቸው ይሆን??? አገር በደም ማዕበል ተመታ፣ ታናናሾች የሚከተሉትን አጡ፣ ቤታቸው ዘወትር ልባቸው በሀዘን የተደቀደቀ ወላጆቻቸውን ትካዜ ያውጃል። ዓለምን እንዲያዩበት የሚቀርብላቸው መነጽር ረጂሙ የጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ! የልባቸው ምት ከቀይ ሽብር የ«ግደል» ዘግናኝ ጩኸት ስልቱ ሽብረክ ቢል፣ ዕጣ ፈንታቸው ከፊታቸውም ከኋላቸውም በተዘጋጀው የደም መቃብር መውደቅ። ሂድ ሲሉት የሚሄድ፣ ተነስ ሲሉት የሚነሳ፣ ጩህ ሲሉት የሚጮህ፣ ዝም በል ሲሉት ዝም የሚል ሰብዕናው የደቀቀ፣ ልቦናው የተበረበረ፣ ደጋፊ የለሽ፣ ሰብሳቢ የለሽ፣ ዕድለ ቢስ መሆኑን በውርደት የተቀበለ አሳዛኝ ትውልድ ከስር እንደ አሸን ፈላ። በባዶነት፣ በፍርሃት፣ ዕምነት በማጣት አረም የተዋጠ ምስኪን ትውልድ ተተካ፣ እንኳን አገራዊ ጉዳይን ግላዊ ሕይወቱን የመወሰን አቅም የተነጠቀ (የተነሳ) ወጣት ብቅ አለ። ለሚረግጠው ሁሉ የሚያጐበድድ አዲሱ የኢትዮጵያ ልጅ! የቀይ ሽብር ዶፍ ብዙ ጉጆዎችን አፈረሰ፣ ብዙ ወላጆችን ያለ ልጅ አስቀረ፣ ብዙ ብላቴናዎችን ታላቅ አልባ አደረገ፣ ወላጆች በተፈጸመባቸው ግፍ አበዱ፣ አገር ጥለው ኮበለሉ፣ ባልተመጣጠነ መሪር ሀዘን በሽተኛ ሆኑ፣ ሞቱም። ከቀይ ሽብር ዕልቂት ወዲህ የኢሕአፓ ደጋፊ በነበሩ ሰዎችና የሰማዕታት ቤተሰቦች ደርግና መኢሶን ባለመቻሉ ብቻ

ያልፈፀሙት ነገር ቢኖር ንፁሕ የከባቢ አየርን የመሣብና የተቃጠለውን የመተንፈስ ተፈጥሯዊ መብት ብቻ እንጂ የቀረውን ሁሉ ነስተዋቸዋል:: ሌላው ቀርቶ ማንም ተራ ሰው ሊፈጽመው የሚችለውን ስካር እንኳ መስከር አይችሉም::

ደርግ «ኢሕአፓን አጠፋለሁ» ብሎ አንድ ትውልድ አጥፍቶ እንኳን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ አይተማመንም ነበር:: የኢሕአፓ አባል ወይም ደጋፊ ነበር የተባለን ሰው ግላዊ እርምጃውንና እንቅስቃሴውን ሁሉ በመከታተል የመማር፣ (በ73 ዓመተ ምሕረት ወጣት ኤፍሬም በርሄና አለምፀሐይ ባሕሩ በብሔራዊ የመልቀቂያ ፈተና በዲፕሎም ፕሮግራም ለመሳተፍ የሚያበቃ ነጥብ ቢያመጡም «ፀረ-አብዮተኛ የነበሩ» በሚል መታገዳቸውና ዕድሉ ለሌሎች መፈቀዱ ለድርጊታቸው ማስረጃ ይሆናል::) የመስራት፣ የማደግ፣ የመሻሻል፣ የመንቀሳቀስ፣ የመብላት፣ የመጠጣት፣ የመልበስ፣ መብቱን ሁሉ ለመገደብ የማይፈጥረው ሰበብ፣ የማያጠምደው አሽክላ አልነበረም:: እስኪገረሰሱ ድረስ በመሠረታዊ ድርጅቶቻቸው ያደርጉት የነበረው ውይይት በነዚሁ ባልታደሉ ዜጐች ሕይወት ዙሪያ እንጂ በልማት በማህበራዊና በሀገር ፍቅር ጉዳይ ላይ አልነበረም::

የዚያን «ያልታደለ ትውልድ» ቆራጥነት፣ ብልህነት፣ የዓላማ ጽኑነት፣ ተዐምር ሰሪነት ያውቁ ነበርና ስሙ በተጠራበት ሁሉ ሸንታቸው ይመጣ ነበር:: ለዚህ ጥሩ ምሣሌ የሚሆነን አንድ የደርግ ባለሥልጣን ነበር:: ግለሰቡ ለብዙ ወጣቶች ስቃይና ሞት ምክንያት ሆኖ ነበር ለማዕረግ የበቃው:: ይህ ሰው የሙታን መንፈስ እየመጣ ሌትም ቀንም የኅሊና ሰላም ስለነሳው በጭንቀት ይኖር ነበር::

ከዕለታት በአንድ ቀን በመኪና ሲጓዙ አንድ መንገደኛ ከገጠሩ ወጥቶ ሊፍት ይጠይቅና ሾፌሩን አዞ አቁመው ይጭኑታል:: ጥቂት





እንደተጓዙ ልቡ በፍርሃት ስትቀልጥ ያሳፈረውን ግለሰብ ሸጉጥ ደግኖበት «አንተ ምን ልታደርግ ነው እዚህ መኪና ላይ የወጣኸው?!?» በማለት ይጠይቀዋል:: ሰውዬው ደነገጠ:: «እረ ወደ ከተማ እንድታደርሰኝ ነው» በማለት በተማጽኖ ያስረዳል:: አጅሬው እንደደገነበት ከመኪናው አስወርዶ «ብል ከመኪናዋ ፊት ለፊት በሰምሶማ ቀጽል» በማለት በገቢናው ጐን ሸጉጡን ደግኖበት ጉዞው በሞያሌ መስመር ተጀመረ:: እሱ በመኪና መከረኛው መንገደኛ በሩጫ፣ ከድንጋጤው ጋር ከተወሰነ ሰአት በኋላ ሩጫ ተዝለፈለፈ፣ አልቻለም፣ ጡንቻው ተሳሰረ እንደደገነበት አስቁሞት «ማን አባክን ልትገል ነው? በል አሁን እያየሁህ መንገዱን ለቀህ ቀጥ ብለህ ወደ ጫካው እሩጥ!» በማለት አዘዘው:: ግለሰቡም የነፍስያውን እንደ አውሬ ጫካ ጥሶ በመሮጥ ተረፈ::

ይኸው ግለሰብ በዚሁ ጊዜና አካባቢ ከቢሮው ወደ መኖሪያ ሲያዘግም አንድ በቅርብ የሚያውቀው አብሮት የኖረ ሰው «አካም ሌንጫ ኪያ!» አንበሳዬ እንዴነህ? ቢለው ከመቅጽበት ሸጉጡን መዝዞ «አንተ ማንን ነው እኔ የበላሁት?? እኔ አውሬ ነኝ?? እኔ አንበሳ ነኝ??» ብሎ ካፋጠጠው በኋላ ለሰዓታት አስገድዶ እንዲንከባለል በማድረግ ካንገላታው በኋላ ሸጉጡን በጐኑ ሸጦ ወደ ቤቱ አምርቷል:: ከዚህም ሌላ ለሥራ የሚገለገልበትን መኪና ካላስፈተሸ አይሳፈርም:: ሾፌሩ ከፍቶ «ይግቡ» ሲለው «ስማ ምን እንደተጠመደበት የተረጋገጠ ነገር አለ? በል መቶ ሜትር ወደፊት መቶ ሜትር ወደ ኋላ ሂድ!» ብሎ ያዛል የተጠመደም ካለ ሾፌሩ አብሮ እንዲፈነዳና እሱ እንዲድን:: ይህ ሰው ልዩ ፍጡር ነበር:: በቡና ቤት የተከፈተለትን ያስቀምሳል፤ ትኩር ብለው ካዩት ችግር ይፈጥራል:: ይህ ዕብደት ከምን የመነጨ እንደሚሆን አንባቢ ይገምት::

በተመሣሣይ ሁኔታ በዚሁ ቦረና አውራጃ አንዱ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ሌሊት በውድቅት ከአልጋው ዘሎ እርቃኑን እየተነሳ ለእሱ እንጂ ለባለቤቱ ከማይታያት የሙት መንፈስ ለማምለጥ እየሸሸ እንደሚደናበርና ደም እያስተፋው እንደሚሰቃይ በቅርብ ጐረቤቶቹ ይታወቃል።

በመጨረሻም በፀሐፊው ዕምነት የዚህ ሁሉ በደል ባለቤቶች ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት ዘላቂና መሠረታዊ ነገሮች ይልቅ አላፊ ፍላጐታቸውንና ጥቅማቸውን በማሳደድ የሚሯሯጡ ወገኖች ናቸው። ዛሬም ከስደት፣ ከስቃይና ከሞት በመለስ የብዙ አካሎቻችን ሕይወት የተሰዋበትን፣ ደም የፈሰሰበትንና ተስፋችንን የጣልንበትን የዲሞክራሲ ውጋጋን በተለመደው ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነትና ሥልጣን ፈላጊነት ስሜት የታወሩ ግለሰቦች ከሰብአዊነት ይልቅ ጐሣንና ክልላዊ ይዞታን ሽፋን በማድረግ ከድህውና የዋሁ ሕዝብ የደም ፍሳሽ የሚቀላውጡ መኖራቸውን ፀሐፊው በሀዘን አስተውሏል።

ሁላችንም ጭካኔንና በቀልን የዓላማችን ግብ መምቻ መሣሪያ ሳናደርግ፣ ባሸመቀ አንደበት ሳንዳለልና ለወንጀል በተዘጋጀ ሰውነት ሳንጋደል ለሰው ልጆች አንድነትና ፍቅር እንሰለፍ።

«ያልታለደው ትውልድ» ሰማዕታት ለሚገድሏቸው እንኳን እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሳቸው በታመቀ ፍቅር ስለ ነፃነት ይዘምሩላቸው ነበር። ሰውን በማፍቀር፣ ሰብዕናን በማክበር፣ ለሰው ልጆች እኩልነትና ልዕልና ውድ ሕይወታቸውን በመስጠት፣ በወገን አፍቃሪነታቸው፣ አንፀባራቂ ምሣሌዎቻችን ነበሩ። አሁንም ናቸው። እናፍቅራቸው! እንፋቀር!

**ተፈጸመ**





## ስንባቢያን

«ይህች አነስተኛ ጽሑፍ በተወሰነ አካባቢ የተፈፀመን አሰቃቂ በደልና ግድያ በመተረክ ባሕሪዋ በሀገራችን ሰሜናዊ፣ ደቡባዊ፣ ምሥራቃዊ፣ ምዕራባዊና ማዕከላዊ ክፍሎች ከተፈፀሙ መሰል ድርጊቶች አኳያ ለጭፍጨፋው ሰለባዎች ትንሽ መታሰቢያ ብትሆንም፡-

ጥሪዋ ግን ለነሱና ለዛሬው ትውልድ አንድ ስብስብ የታሪክ ማስታወሻ ይሰራላቸው ዘንድ ማሳሰብ ነውና፡- አንባቢያን፣ ባለታሪኮችና ፀሐፊዎች በሚያሳዝን ዝምታችን ውስጥ የቀበርነውን እውነተኛ ታሪክ በሞት ሳንቀደም ለባለቤቱ (ለሕዝብ) ለማቅረብ እንጣር።

**አብዲ አብዱሳሂ**